የተማሪዎችና ቤተሰቦች ፖሊሲዎች መመሪያ

2021-22

CAMBRIDGE
PUBLIC SCHOOLS

የኬምብሪጅ መንግሥት ትምህርት ቤቶች

2021-2022 ዓ.ም.
የተማሪዎችና ቤተሰቦች ፖሊሲዎች መመሪያ

አብሮ የሚገኘው ዓመታዊ የተማሪ ቅጾች መጽሔት ውስጥ ያሉት ቅጾች በሙሉ ተሞልተው ተማሪዎች ለዋና አስተማሪዎቻቸው የትምህርት ቤት መጀመሪያ ቀን ላይ መመለስ አለባቸው።

የዚህ ኅትመት ትርጉሞች በ CPS ድህረገጽ ላይ ይገኛሉ፦ www.cpsd.us።

ማውጫ

ክፍል	መግለጫ	ገጽ ቁ
1	የተማሪ ግለኝነት	4
2	የተማሪ መዝገቦች	4
3	መደበኛ መገናኛ መረጃ ለጦር ሠራዊት መልማዮች፥ ለወደፊት ቀጣሪዎች፥ ለኮሌጆችና ለዩኒቨርስቲዎች መስጠት	6
4	በFamily Educational Rights and Privacy Act (FERPA) (የቤተሰብ ትምህርታዊ መብሮችና ግለኝነት ሕግ) ሥር ያሉ መብቶች ማስታወቂያ	6
5	የተማሪ መረጃና የኢንተርኔት ትምህርታዊ አፖች	8
6	መገኘት	8
7	እርዳታ የሚያስፈልገው/ጋት ልጅ (CRA)	9
8	ከትምህርት ቤት የሚወጡ ተማሪዎችን በተመለከተ ማስታወቂያ	9
9	የልጅ ጥቃት	9
10	የእንክብካቤና ጥበቃ እርምጃዎች	10
11	ያልተገኘ ወይም የጠፋ ልጅ	10
12	መጓጓዣ	10
13	ደረጃውን የጠበቀ ፈተና	11
14	የጾታዊ ግንኙነት ትምህርት	11
15	የአካል እገታዎች	11
	የምግባር ደንቦች	
16	መግቢያ	15
17	ፍልስፍና	15
	ባሕርይና የቅጣት ፖሊሲዎች	
18	ማጨስ፦ ከትምባ ነጻ የመን ፖሊሲ	16

19 የዕጾች፥ የመሣሪያና የትምህርት ቤት ሠራተኞች ድብደባ ሕጋዊ ክልከላ 16
20 የዕጽ ፖሊሲ 16
21 የመሣሪያዎች ፖሊሲ 16
22 የሠራተኛ ድብደባ 17
23 በከፍተኛ ወንጀል የተከሰሱ ወይም የተፈረደባቸው ተማሪዎች 17
24 የማዋረጃ እንቅስቃሴ 17
25 አውዳሚነት 18
26 መደባደብ/አካላዊ ጥቃት 18
27 ጸረ-አስፈራሪ ተማሪዎች ፖሊሲና የአስፈራሪ ተማሪዎች ማገጃና መፍትሄ ማምጫ ዕቅድ 19
28 የጎረምሶች የፍቅር ጓደኝነት ጥቃት ፖሊሲ 25

የቅጣት ሂደቶች (የሕግ ሂደት)

29 ጊዜያዊ ማባረር 26
30 ማባረር 27
31 የተማሪ ፍተሻዎችና ምርመራ 28
32 የተማሪ ቅሬታ ሂደት 28
33 የትርፍ ሰዓት እንቅስቃሴዎች ውስጥ ተሳትፎ 29

መብቶችና ልዩ ጥቅሞች

34 ተማሪዎች ላይ ጸረ አድሎ 29
35 አግባብ ያለው ማመቻቸት ፖሊሲና ሂደት 29
36 በ1973 ዓ.ም. ተሃድሶ ሕግ ክፍል 504 ሥር ያለ የመብቶች ማስታወቂያ 30
37 ልዩ ትምህርት 30
38 IEP እና 504 ዕቅዶች ያሏቸው ተማሪዎች 30
39 Affirmative Action (አድሎ ማስወገጃ ሕግ)/ጸረ-አድሎ ማስታወቂያ 32
40 የቤት አልባ ትምህርት አገናኝ 32
41 የመሰብሰብ ነጻነት 32
42 ሐሳብን የመግለጽ ነጻነት 32
43 የግለሰብ ነጻነት 33
44 ጸረ-አድሎ ፖሊሲና የጾታ ጉትጎታ ክልከላ 33
45 የተማሪ ጋብቻ፥ እርግዝናና ወላጅነት 34
46 የTitle IX አስተባባሪ 34

47 የኃይማኖት ነጻነት 34
48 በሰንደቅ ዓላማ ፊት ቃለ መሃላ መመሪያዎች 34

GENERAL POLICIES AND ADMINISTRATIVE GUIDELINES

49 ለኮምፕዩተር ኔትወርክ ተቀባይነት ያለው አጠቃቀም ፖሊሲ (AUP) 34
50 የሶፍትዌር ግብረገብ መመሪያ 36
51 ትምህርት ቤት ጎብኚዎች 37
52 የመኪና ሞተር እንደበራ መቆም አይቻልም 37
53 የተማሪ ዕቃ ማስቀመጫ ሳጥኖች 37
54 የወንጀለኛ መዝገብ መረጃ 37
55 ትምህርታዊ ጉዞዎች 37
56 ክትባቶች 39
57 የቤተሰብ ተሳትፎ 39
58 የማሳለፍና የማቆየት ፖሊሲ 39
59 ሐኪም ያዘዘው መድኃኒት አሰጣጥና ለሕይወት አስጊ የኑ አለርጂዎች ጥንቃቄ በትምህርት ቤት ውስጥ 39
60 የጤንነት ፖሊሲ 39
61 ከስፖርት ጋር የተያያዙ የጭንቅላት ጉዳቶችና ግጭቶች 40
62 የኤችአይቪ/ኤድስ ፖሊሲ 41
63 ተማሪዎችን ስለ አደንዛዥ ዕጾች፥ አልኮል መጠጥ፥ ትምባና ዕጽ ማብዛትን መከላከል ማስተማር 42
64 SBIRT (ምርመራ፥ ጊዜያዊ ድጋፍ እና ወደ ሕክምና መላክ) 42
65 የትምህርት ሥርዓት ግምገማዎች 42
66 በትምህርት ቤት ውስጥ ትምባ የመጠቀም ክልከላ 42

የኬምብሪጅ መንግሥት ትምህርት ቤቶች የእኩል ዕድል አሠሪ ሲን ለሁሉም ተማሪዎች ጥራት ያላቸው ትምህርታዊ መርሃ ግብሮች ለማቅረብ ተግቶ ይሠራል። የኬምብሪጅ መንግሥት ትምህርት ቤቶች በዘር፣ ቀለም፣ ዜግነት፣ ዘር ማንዘር፣ ኃይማኖት፣ ዕድሜ፣ አካል ብቃት፣ የሥነ ዘር መረጃ፣ ውትድርና ውስጥ በፊት በማገልገል፣ የጋብቻ ሁኔታ፣ ጾታ፣ መታወቂያ ጾታ፣ የጓደኛ ጾታ ምርጫ፣ ነፍሰ ጡርነት፣ ወይም ከነፍሰ ጡርነት ጋር የተያያዘ ሁኔታ ላይ ተመሥርተው መርሃ ግብሮቻቸውና እንቅስቃሴዎቻቸው ውስጥ አድሎ አያደርጉም፥ ለቦይ ስካውትና ሌሎች የወጣት ማህበሮቻቸው እኩል የመሳተፍ ዕድልም ይሰጣሉ።

ተሞልተው፥ ፊርማ ተደርጎባቸው መመለስ ያለባቸው ዓመታዊ የተማሪ ቅጾች ለብቻ ይገኛሉ

Last Update: July 2021 (በመጨረሻ የተሻሻለው፡- ጁላይ 2021 ዓ.ም.)

1. የተማሪ ግለኝነት

CPS ከፌዴራልና ከስቴት ሕጎች፥ ከ Federal Family Educational Rights and Privacy Act (ፌዴራል የቤተሰብ ትምህርታዊ መብቶችና ግለኝነት ሕግ) እና የማሳቹሴትስ ትምህርት መዝገቦች ደንቦች እንዲሁም ከCambridge School Committee's Student Privacy Policy (ኬምብሪጅ የትምህርት ቤት ኮሚቴ የትምህርት ግለኝነት ፖሊሲ) ጋር ወጥነት ባለው መንገድ በትምህርት ቤቶቹ የሚሄዱትን ተማሪዎች ግለኝነት ለማረጋገጥ ይጥራል። ስለ ተማሪ ግለኝነት ጉዳዮች በይበልጥ መረጃ ለማግኘት የትምህርት ቤትዎን ተቆጣጣሪ/የከፍተኛ ትምህርት ቤት ዋና ኃላፊን ይገናኙ።

የ United States Code (የዩናይትድ ስቴትስ ስነ ምግባር) Protection of Pupil Rights Amendment (PPRA) (የተማሪ መብት ማሻሻያ ጥበቃ) ክፍል1232h ርእስ 20 እንደሚለው የትምህርት ቤት አውራጃው በሚያካሂዳቸው መጠይቆች፥ ለሽያጭ በሚሰበስበውና በሚጠቀመው መረጃ እንዲሁም በተወሰኑ የአካል ምርመራዎችን በተመለከተ ወላጆች/አሳዳጊዎች/ተንከባካቢዎች የተወሰኑ መብቶች አላቸው። እነሱም የሚከተሉትን መብቶች ያካትታሉ፡-

- ተማሪዎች የሚከተሉትን ጥበቃ ያላቸውን ዘርፎች የሚመለከቱ መጠይቆች ከመመለሳቸው በፊትና መጠይቁ በሙሉ ወይም በከፊል ከ U.S. Department of Education (ED) (የአሜሪካ ትምህርት መምሪያ) የገንዘብ ድጋፍ ያለው ከነ፥ ፈቃድ ያስፈልጋል፡- (1) የተማሪው ወይም የተማሪው ወላጆች/አሳዳጊዎች/ተንከባካቢዎች የፖለቲካ ትስስር ወይም እምነቶች፥ (2) የተማሪው ወይም የተማሪው ቤተሰብ የአእምሮ ወይም ስነ ልቦናዊ ችግሮች፥ (3) ጾታዊ ግንኙነት ባሕርይ ወይም አኳኋኖች፥ (4) ሕገወጥ፥ ጸረ ማህበራዊ፥ እራስን ተጠያቂ አድራጊ ወይም አዋራጅ ባሕርይ፥ (5) ቅርብ የቤተሰብ ግንኙነት ካላቸው መላሾች ጋር ሥር ነቀል ዋጋ መስጠት፥ (6) ሕጋዊ እውቅና ያላቸው ባለ ልዩ ጥቅም ግንኙነቶች ለምሳሌ ከጠበቃዎች፥ ዶክተሮች ወይም ሚኒስትሮች፥ (7) የተማሪው ወይም የተማሪው ወላጆች/አሳዳጊዎች/ተንከባካቢዎች ኃይማኖታዊ ልምዶች፥ ትስስሮች ወይም እምነቶች፥ ወይም (8) ገቢ፥ የመርሃ ግብር መስፈርትን ለማሟላት በሕግ ከሚጠየቀው ሌላ።
- አንድ ተማሪ የሚከተሉት ውስጥ እንዳይሳተፍ ዕድል ለመስጠት ማስታወቂያ ማግኘት፡- (1) ማንኛውም ሌላ ጥበቃ የተደረገለት መጠይቅ፥ የገንዘብ ድጋፍ ምንጩ ማንኛውም ቢን፥ (2) ማንኛውም ድንገተኛ ያልነ ለመሳተፍ አስፈላጊ የነ፥ ትምህርት ቤቱ ወይም ተወካዩ የሚያደርገው፥ የተማሪውን ጤንነትና ደህንነት በአስቸኳይ ለመጠበቅ አስፈላጊ ያልነ ጥልቅ የአካል ምርመራ፥ ከማዳመጥ፥ ከእይታ፥ ከአከርካሪ አጥንት ምርመራና ማንኛውም ሌላ በስቴት ሕግ ሥር አስፈላጊ ከነና ከሚፈቀድ ምርመራ ሌላ፥ እና (3) ከተማሪዎች የተገኘ የግል መረጃን ለሽያጭ ለማቅረብ ወይም ለሌሎች ለማስተላለፍ መሰብሰብ፥ አሳልፎ መስጠት ወይም ከመጠቀም ጋር የተያያዙ እንቅስቃሴዎች።
- በተጠየቀ ወቅትና በሥራ ላይ ከማዋል በፊት የሚከተሉትን መመርመር ወይም መጠቀም፡- (1) ጥበቃ ያለው የተማሪዎች የመረጃ መጠይቅ፥ (2) የተማሪዎችን የግል መረጃ ለሽያጭ ወይም ለማሰራጨት ለመሰብሰብ የሚጠቀሙባቸው መሣሪያዎች እና (3) የሥርዓተ ትምህርቱ አካል የነ ማስተማሪያ ቁሳቁስ።

እነዚህ መብቶች ለወላጆች/አሳዳጊዎች/ተንከባካቢዎችና ዕድሜው ከ18 ዓመት በላይ ለነ ተማሪ ወይም በሕጋዊ መንገድ ከ18 በታች ኖ እራሱን ለቻለ ተማሪ ይተላለፋሉ።

CPS ከወላጆች/አሳዳጊዎች/ተንከባካቢዎች ጋር በመመካከር እነዚህን መብቶች በተመለከተ ፖሊሲዎችን አቅፏል፥ እንዲሁም ጥበቃ የተደረገላቸውን የመረጃ መጠይቆችና ለሽያጭና ለሌላ ስርጭት የግል መረጃን መጠቀም በተመለከተ የተማሪን ግለኝነት ለመጠበቅ መሰናዶዎች አድርጓል። CPS ስለነዚህ ፖሊሲዎች ቢያንስ በየዓመቱና ትርጉም ያለው ለውጥ በተደረገ ቁጥር ወላጆች/አሳዳጊዎች/ተንከባካቢዎችን በቀጥታ ያሳውቃቸዋል። በተጨማሪም ተማሪዎችን ከታች ያሉት ልዩ እንቅስቃሴዎች ወይም መጠይቆች ውስጥ የማሳተፍ ዕቅድ ሲኖር CPS ወላጆች/አሳዳጊዎች/ተንከባካቢዎችን በቀጥታ ለምሳሌ በፖስታ ወይም በኢሜል ያሳውቃቸውና ወላጆች/አሳዳጊዎች/ተንከባካቢዎች ከእንቅስቃሴው ወይም ከመጠይቁ ልጃቸው እንዳይሳተፍ/እንዳትሳተፍ የማድረግ ዕድል ይሰጣቸዋል። የትምህርት ቤቱ አውራጃ እንቅስቃሴዎቹ ወይም መጠይቆቹ የሚካሄዱበትን ቀኖች በትክክል ወይም በግምት የትምህርት ዓመቱ መጀመሪያ ላይ ለይቶ ካወቀ፥ CPS በዛን ጊዜ ወላጆች/አሳዳጊዎች/ተንከባካቢዎችን ያሳውቃል። የትምህርት ዓመቱ ከተጀመረ በኋላ ጊዜ ለሚያዝላቸው መጠይቆችና እንቅስቃሴዎች፥ ወላጆች/አሳዳጊዎች/ተንከባካቢዎች ከታች ስለታቀዱት እንቅስቃሴዎችና መጠይቆች አግባብ ያለው ማስታወቂያ ይሰጣቸውና ልጃቸው እነዚህ እንቅስቃሴና መጠይቆች እንዳይሳተፍ ከፈለጉ የመውጫ ዕድል ይሰጣቸዋል። በተጨማሪም ወላጆች/አሳዳጊዎች/ተንከባካቢዎች የሚመለከታቸውን መጠይቆች እንዲያገኙ ዕድል ይሰጣቸዋል። በትምህርት ቤት አውራጃው Student Privacy Policy (የተማሪ ግለኝነት ፖሊሲ) መሠረት የልጅዎ ትምህርት ቤት ተቆጣጣሪ/የከፍተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ዋና ኃላፊ በትምህርት ዓመት ውስጥ ስለሚኖሩ ስለ ማንኛቸውም የወላጅ/አሳዳጊ/ተንከባካቢ ማስታወቂያና ፈቃድ ወይም አለመሳተፊያ ስለሚያስፈልጋቸው እንቅስቃሴዎች ያሳውቅዎታል። ይሄ መስፈርት የሚመለከታቸው ልዩ እንቅስቃሴዎችና መጠይቆች የሚከተሉት ናቸው፡- (1) የግል መረጃን ለማስታወቂያ፥ ለሽያጭና ለሌላ ስርጭት መሰብሰብ፥ ማሳወቅ ወይም መጠቀም፥ (2) ሙሉ ለሙሉ ወይም በከፊል የED ገንዘብ ድጋፍ ያልተደረገለት ጥበቃ ያለው መረጃ መጠይቅ መስጠት፥ እና (3) አስቸኳይ ያልነ ከላይ በተገለጸው መሠረት ጥልቅ አካላዊ ምርመራ።

የመብት ጥሰት ደርሶብናል ብለው የሚያምኑ ወላጆች/አሳዳጊዎች/ተንከባካቢዎች ወደሚከተለው ቅሬታ ማቅረብ ይችላሉ፡-

Family Policy Compliance Office
U.S. Department of Education
400 Maryland Avenue, S.W.
Washington, D.C. 20202-5920
Phone: 800.USA.LEARN (800.872.5327)

2. የተማሪ መዝገቦች

በማሳቹሴትስ ሕግ መሠረት የማንኛውም ተማሪ ወላጆች/አሳዳጊዎች/ተንከባካቢዎች ወይም ዘጠነኛ ክፍል የገባ

ተማሪ ወይም ዕድሜው/ዋ ቢያንስ 14 ዓመት የነ /የነች ተማሪ ጥያቄ አቅርቦ/ባ የተማሪውን መዝገብ መቃኘት ይችላል/ትችላለች። ወላጆች/አሳዳጊዎች/ተንከባካቢዎች ወይም ብቃት ያለው/ያላት ተማሪ ጥያቄውን ባስገባ/ች አሥር ቀን ውስጥ የተማሪው መዝገብ ሊደርሰው/ሊደርሳት ይገባል፣ ብቃት ያለው ባለሙያም እንዲተረጉምለት ወይም ተቆጣጣሪው/የከፍተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ዋና ኃላፊ እንዲያስተካክልለት ጥያቄ ማቅረብ ይችላል። በተጨማሪም የተማሪ መዝገብ መረጃ ጠባቂ ላልኑ ወላጆች ከመቅረቡ በፊት የመንግሥት ትምህርት ቤቶች መከተል ያለባቸው የስቴት ሕጎች ያወጧቸው ሂደቶች አሉ። ሁሉም የተማሪን መዝገብ ለማየት የሚቀርቡ ጥያቄዎች የተማሪው ትምህርት ቤት ተቆጣጣሪ/የከፍተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ዋና ኃላፊ ፊት መቅረብ አለባቸው። በተጨማሪም አንድ ተማሪ መሄድ ወይም መዛወር የሚፈልግበት ትምህርት ቤት ውስጥ የሚሠራ ፈቃድ ያለው ሠራተኛ ያለተማሪው እና/ወይም ያለ ወላጅ/አሳዳጊ/ተንከባካቢ ፈቃድ የተማሪውን መዝገብ ማየት ይችላል፣ እንዲሁም ተማሪ መሄድ ወይም መመዝገብ የሚፈልግበት/የምትፈልግበት ትምህርት ቤት ጋር CPS የተማሪ መዝገብ ይልካል።

አንድ/ዲት ተማሪ ከኬምብሪጅ መንግሥት ትምህርት ቤት ከተመረቀ/ች፣ ከተዛወረ/ች ወይም ከወጣ/ች በኋላ ከሰባት (7) ዓመት ባልበለጠ ጊዜ ውስጥ ጊዜያዊ መዝገቡ/ቧ ይደመሰሳል። ተማሪው/ዋ ከኬምብሪጅ መንግሥት ትምህርት ቤት በሚመረቅበት/በምትመረቅበት፣ በሚዛወርበት/በምትዛወርበት ወይም በሚወጣበት/በምትወጣበት ወቅት የተማሪው/ዋ ጊዜያዊ መዝገብ የሚደመስሰበትን ቀን የያዘ የጽሑፍ ማስታወቂያ ለተማሪው/ዋ እና ለተማሪው/ዋ ወላጅ/አሳዳጊ/ተንከባካቢ ይሰጣቸዋል። የአንድ ተማሪ የትምህርት ማስረጃን የትምህርት ቤቱ መምሪያ ያቆየውና ተማሪው/ዋ ከኬምብሪጅ መንግሥት ትምህርት ቤት ከተመረቀ/ች፣ ከትዛወረ/ች ወይም ከወጣ/ች ከስልሳ (60) ዓመት በኋላ ይደመሰሳል።

የየፌዴራል ሕግ የነው የFamily Educational Rights and Privacy Act (FERPA) (የቤተሰብ ትምህርታዊ መብቶችና ግለኝነት ሕግ) እና የማሳቹሴትስ የተማሪ መዝገብ ሕግ፣ የትምህርት ቤት አውራጃው ከልጅዎ የትምህርት መዝገቦች ውስጥ ማንነትን የሚገልጽ መረጃ ከማስተላለፉ በፊት፣ ባንዳንድ ልዩ ምክንያቶች ካልነ በስተቀር፣ በጽሑፍ ፈቃድዎን የማግኘት ግዴታ እንዳለበት ይገልጻል። ኖም "የማውጫ መረጃ" ተብሎ ባግባቡ የተሰየመ መረጃን፣ እርስዎ CPS በሂደቶቹ መሠረት እንዳያስተላልፍ ካላሳወቁ በስተቀር፣ CPS ያለጽሑፍ ፈቃድ ሊያስተላልፍ ይችላል። የማውጫ መረጃው ዋና ዓላማ CPS ይህን ዓይነት መረጃ ከልጅዎ የትምህርት መዝገቦች ውስጥ ወስዶ አንዳንድ የትምህርት ቤት ኅትመቶች ውስጥ፣ ለምሳሌ ልጅዎ አንድ ድራማ ውስጥ የተጫወተውን ሚና ለማሳየት፣ ዓመታዊ መጽሐፍ ውስጥ፣ የኅበዝ ተማሪዎች ወይም የሌላ እውቅና መስጫ ስም ዝርዝር ውስጥ፣ የምርቃት ፕሮግራሞች ውስጥና የስፖርት እንቅስቃሴ ዝርዝር ውስጥ ማካተት እንዲችል ነው።

የማውጫ መረጃ ቢወጣ ባጠቃላይ ጎጂ አይደለም ወይም የግለኝነት መተላለፍ አይደለም ተብሎ ስለሚታሰብ፣ አስቀድሞ የወላጅ/አሳዳጊ/ተንከባካቢ የጽሑፍ ፈቃድ ሳይገኝ ለውጪ ድርጅቶች ሊሰጥ ይችላል። CPS የአንድ ተማሪን ስም፣ አድራሻ ወይም ኢሜል ለውጪ ድርጅቶች እንዲሁም የክፍል ቀለበት ለሚሠሩ ወይም ዓመታዊ መጽሐፍ ለሚያትሙ፣ እንደነዚህ አገልግሎቶችን በተለይ ለተማሪዎች ለሚሰጡ ድርጅቶች ሊሰጥ ይችላል። በተጨማሪም በ Elementary and Secondary Education Act of 1965 (ESEA) (የ1965 ዓ.ም. አንደኛ ደረጃና ሁለተኛ ደረጃ ትምህርታዊ ሕግ) ሥር እርዳታ የሚያገኙ የአካባቢው ትምህርታዊ ድርጅቶች (LEAዎች) ከጦር ሠራዊት መልማዮች ጥያቄ በቀረበ ጊዜ፣ ወላጆች/አሳዳጊዎች/ተንከባካቢዎች አስቀድመው በጽሑፍ ፈቃድ ካልሰጡ በስተቀር የልጃቸው መረጃ እንዲሰጥ እንደማይፈልጉ LEAን አስታውቀው ካላነበረ በስተቀር፣ ከማውጫ መረጃ ውስጥ ሶስት ምድቦችን ማለትም ስም፣ አድራሻና ስልክ ቁጥርን እንዲያቀርቡ ሁለት የፌዴራል ሕጎች ያስገድዳሉ።

CPS ያለ ወላጅ/አሳዳጊ/ተንከባካቢ ፈቃድ የሚከተለውን መረጃ ይሰጣል፦ የተማሪ ስም፣ የተገኘበት ቀኖች፣ ክፍል፣ ኦፊሲዬላዊ እውቅና ያላቸው እንቅስቃሴዎችና ስፖርቶች፣ ፎቶዎች/ቪዲዮዎች፣ የስፖርት ቡድኖች ውስጥ አባልነት፣ ማዕረጎችና ሽልማቶች፣ የጥናት ዘርፍና ከሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ብኋላ ያሉ ዕቅዶች።

በተጨማሪምAdditionally, pursuant to በ M.G.L.c. 71፣ §89(g) መሠረት ከኮመንዌልዝ ቻርተር ትምህርት ቤት ጥያቄ በደረሰው ጊዜ፣ የኮመንዌልዝ ቻርተር ትምህርት ቤት ውስጥ ለመመዝገብ መስፈርት ለሚያሟሉ ተማሪዎች የምልመላ መረጃ መላክ እንዲችል፣ CPS የመንግሥት ትምህርት ቤት ተማሪዎችን ስምና አድራሻ የማሳቹሴትስ አንደኛና ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት መምሪያ ላጸደቀው ሶስተኛ አካል ይሰጣል።

ይህ መረጃ ያለፈቃድዎ እንዳይሰጥ ከፈለጉ፣ የትምህርት ቤትዎን ተቆጣጣሪ/የከፍተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ዋና ኃላፊ በየትምህርት ዓመቱ ከኦክቶበር በፊት በጽሑፍ ማሳወቅ አለብዎት። ይህ መረጃ እንዲሰጥ ለማይፈልጉ ተማሪዎችና ወላጆቻቸው/አሳዳጊዎቻቸው/ተንከባካዎቻቸው የጽሑፍ አለመሳተፊያ ቅጽ ከዚህ መጽሔት ጋር ተያይዞ ይገኛል።

የተማሪ መዝገቦችንና የወላጆች/አሳዳጊዎች/ተንከባካቢዎች መብቶችን እንዲሁም የተማሪዎች መብቶችን የሚመለከቱ የስቴት ደንቦች ቅጂዎች በየትምህርት ቤቱ ይገኛሉ።

በተጨማሪም የትምህርት ቤቱ ኮሚቴ የተማሪና የወላጆች/አሳዳጊዎች/ተንከባካቢዎች አድራሻ(ዎች)ን፣ ስልክ ቁጥር(ሮች)ንና ኢሜል አድራሻን(ዎች) እንዲሁም የተማሪ ስምን "የማውጫ መረጃ" ብሎ ስለመደበው ሊሰጥ የሚችለው ለአንድ ልዩ ትምህርት ቤት ውስጥ ላሉ የወላጅ/አሳዳጊ/ተንከባካቢ ቡድኖች፣ የትምህርት ቤት ቤተሰብ ማውጫ መጽሐፍ ለማዘጋጀት ብቻ እና ለትምህርት ቤት ምሩቃን ቡድኖች የምሩቃን ማውጫ ማዘጋጀት እንዲችሉ ብቻ ይሰጣል፣ ይህ ዓይነት መረጃ የሚሰጠውም የተማሪው ወላጆች/አሳዳጊዎች/ተንከባካቢዎች ይህ መረጃ የትምህርት ቤቱ የቤተሰብ ማውጫ መጽሐፍ ውስጥ ወይም የትምህርት ቤቱ የምሩቃን ማውጫ ውስጥ እንዲካተት በተለይ በጽሑፍ ፈቃድ ከሰጡ ብቻ ነው። አንድ ወላጅ/አሳዳጊ/ተንከባካቢ ከነዚህ ኅትመቶች አንዱ ወይም ሁለቱም ውስጥ መሳተፍ ከፈለገ የትምህርት ዓመቱ መጀመሪያ ላይ "እሳተፋለሁ" ብሎ ማሳወቅ አለበት።

የትምህርት ቤት ኮሚቴው በተጨማሪም የተማሪን ስም፣ ስልክ ቁጥር(ሮች)፣ የቤት አድራሻና የትውልድ ቀን "የማውጫ መረጃ" ብሎ ስለሰየመው ይህ መረጃ ለኬምብሪጅ መንግሥት ቤተ መጽሐፍት የሚሰጠው ለኬምብሪጅ መንግሥት ትምህርት ቤት አጸደ ሕጻናት ተማሪዎች የቤተ መጽሐፍት ካርድ ማግኘት እንዲችሉ ብቻ ነው። የቤተ መጽሐፍት ካርዶች የሚሰጡት የትምህርት ዓመት መጀመሪያ ላይ ዕድሜያቸው አምስትና ከዛ በላይ ለኑ ለአጸደ ሕጻናት ተማሪዎች በሙሉ ሲን በተጨማሪም ተማሪዎች በትምህርት ዓመት ወቅት ዕድሜያቸው አምስት ሲን የቤተ መጽሐፍት ካርድ ይሰጣቸዋል። አንድ ወላጅ/አሳዳጊ/ተንከባካቢ ይህ መረጃ ለኬምብሪጅ መንግሥት መጽሐፍት ቤት እንዲሰጥ ካልፈለገ የትምህርት ዓመት መጀመሪያው ላይ "አለመሳተፍ" ይችላል/ትችላለች።

በተጨማሪም ተማሪዎች የሚጠቀሙባቸው የኢንተርኔት በክላውድ ላይ የተመሠረቱ ትምህርታዊ አፖች ለሚያቀርቡ ሻጮች CPS የተማሪ መረጃን ሊሰጥ ይችላል፥ ይህ የተቋም ተግባር ወይም አገልግሎት ሲን   ይህ መረጃ የሚሰጠው ሻጩ የተማሪ መረጃ ግለኝነት ስምምነት ከትምህርት ቤት አውራጃው ጋር ከተፈራረመ ብቻ ኖ   ሻጩ እነዚህን በክላውድ ላይ የተመሠረቱ የኢንተርኔት ትምህርታዊ አፖች ሲያቀርብ እንደ ትምህርት ቤት ባለ ሥልጣን ተቆጥሮ ይናል   ወይም የተማሪው ወላጆች/አሳዳጊዎች/ተንከባካቢዎች በግልጽ በጽሑፍ ፈቃድ ሰጥተው መን   አለበት። ፈቃድ የተሰጣቸው በክላውድ ላይ የተመሠረቱ ትምህርታዊ ግልጋሎቶች በሚከተለው ድህረገጽ ይገኛሉ፡- bit.ly/CPSDigRes

ማንኛውም ተማሪ የሚፈጥረውና የትምህርት ቤት መምሪያ ኮምፒዩተሮች/ሰርቨሮች ላይ የሚያኖረው የተማሪ ሥራ ተማሪው የኬምብሪጅ መንግሥት ትምህርት ቤቶችን ከለቀቀ በኋላ እስከ ሰባት ዓመት ድረስ ይያዛል፥ የኬምብሪጅ መንግሥት ትምህርት ቤቶች በሚጠቀመው በኢንተርኔት ትምህርታዊ አገልግሎት ሰጪ በኩል የሚያኖረው የተማሪ ሥራ ደግሞ በአገልግሎት ሰጪው ማቆያና መደምሰሻ መስፈርቶች መሠረት ይቆያል። አብዛኛውን ጊዜ የኢንተርኔት አገልግሎት ሰጪ ማቆያ ጊዜ ከኬምብሪጅ መንግሥት ትምህርት ቤቶች ጋር ካለው ውል ጋር ተመሳሳይ ሲን፥   የኬምብሪጅ መንግሥት ትምህርት ቤቶች ግን ጥያቄ ካቀረበ ሊያጥር ይችላል።
በስቴቱ ሕግ መሠረት አንድ ተማሪ አንድ ትምህርት ቤት ውስጥ ተመዝግቦ በቆየበት ጊዜ የትምህርት ቤት ተቆጣጣሪው/የከፍተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ዋና ኃላፊው ወይም ተወካዩ በየጊዜው የተማሪውን/ዋን መዝገብ እየቃኘ ስህተት፥ ቀን ያለፈበት ወይም ከርእስ ውጪ የነ   መረጃን በመጀመሪያ ለተማሪው/ዋና እና ለወላጆች/አሳዳጊዎች/ተንከባካቢዎች በጽሑፍ ካሳወቀና ቅጂው እንዲደርሳቸው ዕድል ከሰጠ በኋላ ያስወግዳል። በተጨማሪም በስቴት ሕግ መሠረት፥ ጊዜያዊ መዝገቡ ተማሪው/ዋ ከኬምብሪጅ መንግሥት ትምህርት ቤት ከተዛወረ/ች፥ ከተመረቀ/ች ወይም ከወጣ/ች በኋላ ሰባት ዓመት ባልበለጠ ጊዜ ውስጥ፥ ለተማሪው/ዋና ለወላጅ/አሳዳጊ/ተንከባካቢ የሚደመሰስበት ቀንና መረጃውን በሙሉ ወይም በከፊል የማግኘት መብታቸውን በተመለከተ በዝውውሩ፥ በምረቃው ወይም በመውጫው ጊዜ ይነገራቸውና ይደመሰሳል።

በስቴት ሕግ መሠረት የተማሪው/ዋ የትምህርት ማስረጃ ተማሪው/ዋ ከኬምብሪጅ መንግሥት ትምህርት ቤቶች ከተመረቀ/ች፥ ከተዛወረ/ች ወይም ከወጣ/ች ከስልሳ (60) ዓመት በኋላ ይደመሰሳል።

3. መደበኛ መገናኛ መረጃ ለጦር ሠራዊት መልማዮች፥ ለወደፊት ቀጣሪዎች፥ ለኮሌጆችና ለዩኒቨርስቲዎች መስጠት

በ2001ዓ.ም. የ No Child Left Behind Act (ማንም ልጅ ወደ ኋላ አይቀርም ሕግ) ፌዴራል ሕግ አንድ አቅራቦት መሠረት ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች ከአሜሪካ ጦር ሠራዊት መልማዮች፥ ኮሌጆች፥ ዩኒቨርስቲዎችና ሌሎች የትምህርት ተቋሞችና ቀጣሪዎች ጥያቄ በቀረበላቸው ጊዜ የሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ተማሪዎች ስሞች፥ አድራሻዎች፥ የኢሜል አድራሻዎችና ስልክ ቁጥሮች የመስጠት ግዴታ አለባቸው። የሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ተማሪዎችና ወላጆች/አሳዳጊዎች/ተንከባካቢዎች ጥያቄ በቀረበ ጊዜ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች መደበኛ መረጃቸውን እንዳይሰጡ የመጠየቅ አማራጭ አላቸው። ኖም   የሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ተማሪዎች እና/ወይም ወላጆቻቸው/አሳዳጊዎቻቸው/ተንከባካቢዎቻቸው መረጃ እንዳይሰጥ ይህንን እርምጃ ካልወሰዱ ጥያቄ በቀረበ ጊዜ የመገናኛ መረጃው እንዲሰጥ ሕጉ ያስገድዳል። የመገናኛ መረጃቸው እንዳይሰጥ የሚፈልጉ የሁለተኛ ደረጃ ተማሪዎችና ወላጆቻቸው/አሳዳጊዎቻቸው/ተንከባካቢዎቻቸው የሚሞሉት የጽሑፍ አለመሳተፊያ ቅጽ አብሮ ተያይዞ ይገኛል።

4. በFamily Educational Rights and Privacy Act (FERPA) (የቤተሰብ ትምህርታዊ መብሮችና ግለኝነት ሕግ) ሥር ያሉ መብቶች ማስታወቂያ

FERPA ለወላጆች/አሳዳጊዎች/ተንከባካቢዎችና ዕድሜያቸው ከአሥራ ስምንት (18) ዓመት በላይ ለኑ   ተማሪዎች (“መስፈርት ያሟሉ ተማሪዎች”) የተማሪውን/ዋን ትምህርታዊ መዝገብ በተመለከተ የተወሰኑ መብቶች ይሰጣል። እነዚህ መብቶች እንደሚከተለው ናቸው፡-

- ትምህርት ቤቱ የተማሪውን ትምህርታዊ መዝገቦች ለማየት ጥያቄ በደረሰው በአርባ አምስት (45) ቀን ውስጥ የመመርመርና የመቃኘት መብት። ወላጆች/አሳዳጊዎች ወይም መስፈርት ያሟሉ ተማሪዎች ማየት የሚፈልጉትን መዝገብ(ቦች) በግልጽ የሚጠቅስ የጽሑፍ ጥያቄ ለትምህርት ቤቱ ተቆጣጣሪ/የከፍተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ዋና ኃላፊ ማቅረብ አለባቸው። የትምህርት ቤት ባለሥልጣኑ መረጃውን ለሳማየት መሰናዶ ያደርግና ወላጅ/አሳዳጊ/ተንከባካቢን ወይም መስፈርት ያሟላ ተማሪን መዝገቦቹን መቼና የት ማየት እንደሚችሉ ያሳውቃቸዋል።

- ወላጅ/አሳዳጊ/ተንከባካቢ ወይም መስፈርት ያሟላ ተማሪ ትክክል አይደለም፥ አሳሳች ነው ወይም በ FERPA መሠረት የተማሪውን መብቶች ተላልፏል ብለው የሚያምኑትን የተማሪውን/ዋን ትምህርታዊ መዝገቦች እንዲስተካከልላቸው የመጠየቅ መብት። መዝገብ እንዲስተካከልላቸው ትምህርት ቤቱን መጠየቅ የሚፈልጉ ወላጆች/አሳዳጊዎች ወይም መስፈርት ያሟሉ ተማሪዎች ለትምህርት ቤቱ ተቆጣጣሪ/የከፍተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ዋና ኃላፊ ጽፈው እንዲስተካከል የሚፈልጉትን የመዝገብ ክፍልና ለምን መቀየር እንዳለበት ገልጸው ማሳወቅ አለባቸው። ትምህርት ቤቱ ወላጅ/አሳዳጊ/ተንከባካቢ ወይም መስፈርት ያሟላ ተማሪ ባቀረበው ጥያቄ መሠረት መዝገቡን ላለማስተካከል ከወሰነ፥ ወላጅ/አሳዳጊ/ተንከባካቢውን ወይም መስፈርት ያሟላ ተማሪውን ያሳውቀውና መዝገቡ እንዲሻሻል ይግባኝ የማለት መብት እንዳለው ያሳውቀዋል። የይግባኝ መብት እንዳለ በሚነገርበት ጊዜ የይግባኝ ሂደቶቹን በይበልጥ የሚያብራራ ተጨማሪ መረጃ ለወላጅ/አሳዳጊ/ተንከባካቢ ወይም መስፈርት ያሟላ ተማሪ ይቀርባል።

- ትምህርት ቤቱ ማንነትን የሚያሳውቅ መረጃ (PII) ከተማሪ ትምህርታዊ ምዝገቦች ውስጥ ከማሳየቱ በፊት በጽሑፍ ፈቃድ የመስጠት መብት፥ FERPA ያለ ፈቃድ ለመስጠት የሚፈቅደው ካልነ   በስተቀር።

  አንድ ልዩነት ያለው ሁኔታ ቢኖር፥ ሕጋዊነት ላለው ትምህርታዊ ምክንያት ለትምህርት ቤት ባለሥልጣኖች ያለ ፈቃድ መስጠት ይፈቀዳል። የትምህርት ቤት ባለ ሥልጣን ማለት ትምህርት ቤት ውስጥ እንደ አስተዳዳሪ፥ አለቃ፥ አስተማሪ ወይም ድጋፍ ሰጪ ሠራተኛ (የጤና ወይም የሕክምና ሠራተኛንና የሕግ አስከባሪ ክፍል ሠራተኛን ጨምሮ) ተቀጥሮ የሚሠራ፥ ወይም የትምህርት

ቤት ኮሚቴ ውስጥ የሚያገለግል ሰው ማለት ነው። የትምህርት ቤት ባለሥልጣን ማለት በጎ አድራጊ ወይም ከትምህርት ቤቱ ውጪ ኖ ውል ተዋውሎ እሱ ባይኖር ኖሮ ትምህርት ቤቱ የራሱን ሠራተኛ የሚያስሠራው የተቋም አገልግሎት ወይም ሥራ የሚሠራና ትምህርታዊ መዝገቦች ውስጥ ያለ PIIን ማስተናበርና መጠቀምን በተመለከተ ትምህርት ቤቱ በቀጥታ የሚቆጣጠረው ሰው ለምሳሌ እንደ ጠበቃ፣ ኦዲተር፣ የሕክምና አማካሪ ወይም የቴራፒ ባለሙያ፣ ለምሳሌ የአቤቱታ ወይም የቅጣት ዓይነት ኦፊሲዬላዊ ኮሚቴ ላይ የሚያገለግል ወላጅ/አሳዳጊ/ተንከባካቢ ወይም ተማሪ፣ ወይም ሌላ የትምህርት ቤት ባለሥልጣንን በሥራው ላይ የሚረዳ በጎ አድራጊ ወላጅ/አሳዳጊ/ተንከባካቢ ወይም ተማሪ። አንድ የትምህርት ቤት ባለ ሥልጣን ሕጋዊ ትምህርታዊ ፍላጎት አለው የሚባለው ባለ ሥልጣኑ ትምህርታዊ መዝገብ መቃኘት ያለበት የሙያ ኃላፊነቱን ለመወጣት ከነ ነው።

አንድ ተማሪ ለመመዝገብ ከሚፈልግበት ወይም ከተመዘገበበት ትምህርት ቤት ጥያቄ በቀረበ ጊዜ፣ ጥያቄው ከተማሪው ምዝገባ ወይም ዝውውር ጋር የተያያዘ እስከነ ድረስ፣ ትምህርት ቤቱ ያለፈቃድ ለባለሥልጣኖች ትምህርታዊ መዝገቦችን ያሳያል።

- ትምህርት ቤቱ የ FERPAን መስፈርቶች አልተከተለም የሚል ክስ የ United States Department of Education (አሜሪካ ትምህርት መምሪያ) ጋር አቤቱታ ማስገባት። FERPAን የሚያስተዳድረው ቢሮ ስምና አድራሻ የሚከተለው ነው፡-

  Family Policy Compliance Office
  U.S. Department of Education
  400 Maryland Avenue, SW
  Washington, D.C. 20202-5920
  ስልክ፡- 800.USA.LEARN (800.872.5327)

በFERPA ደንቦች §99.31 ያሉትን ሁኔታዎች እስካሟላ ደረስ፣ የተማሪዎች ትምህርታዊ መዝገቦች ውስጥ ያለ PIIን ያለ ወላጅ/አሳዳጊ/ተንከባካቢ ወይም ያለ መስፈርት ያሟላ ተማሪ ፈቃድ ማሳየትን FERPA ይፈቅዳል። ለትምህርት ቤት ባለ ሥልጣኖች፣ ከፍትህ ትእዛዝ ጋር በተያያዘ ወይም በሕጋዊ መንገድ ከቀረቡ መጥሪያዎች ጋር በተያያዘ ጉዳይ፣ የማውጫ መረጃና ለወላጅ/አሳዳጊ/ተንከባካቢ ወይም መስፈርት ላሟላ ተማሪ መረጃ ሲሰጥ ካልነ በስተቀር የ FERPA ደንቦች ክፍል §99.32 እንደሚለው ትምህርት ቤቱ ያሳየውን መረጃ መመዝገብ አለበት። ወላጆች/አሳዳጊዎች/ተንከባካቢዎችና መስፈርት ያሟሉ ተማሪዎች የሚሰጠውን መረጃ የመመርመርና የመቃኘት መብት አለቸው። አንድ ትምህርት ቤት አስቀድሞ ከወላጆች/አሳዳጊዎች/ተንከባካቢዎች ወይም መስፈርት ካሟላ/ች ተማሪ አስቀድሞ የጽሑፍ ፈቃድ ሳያገኝ ከተማሪው/ዋ ትምህርታዊ መዝገቦች PII የያዘ መረጃ ለሚከተሉት መስጠት ይችላል፡-

- ትምህርት ቤቱ ሕጋዊ ትምህርታዊ ፍላጎቶች አሉት ብሎ ለወሰነው ትምህርታዊ ድርጅት ወይም ተቋም ውስጥ ላሉ ለሌሎች የትምህርት ቤት ባለሥልጣኖች፣ አስተማሪዎችን ጨምሮ። ይህም በ §99.31(a)(1)(i)(B)(1) – (a)(1)(i)(B)(2) ውስጥ የተጠቀሱት ቅድመ ሁኔታዎች እስከተሟሉ ደረስ፣ ኮንትራክተሮችን፣ አማካሪዎችን፣ በጎ አድራጊዎችን፣ በኢንተርኔት ላይና በክላውድ ላይ የተመሠረቱ ተማሪዎች የሚጠቀሙባቸው ትምህርታዊ አፖች የሚያቀርቡ ሻጮችን ወይም ትምህርት ቤቱ የተቋም አገልግሎቶችን ወይም ሥራዎችን የሚያሠሯቸው ሌሎች ወገኖችን ያካትታል። (§99.31(a)(1))
- ተማሪው/ዋ ለመመዝገብ የሚፈልገው ወይም አሁን የተመዘገበበት ሌላ ትምህርት ቤት ላሉ ባለ ሥልጣኖች፣ የትምህርት ሥርዓት ወይም የከፍተኛ ደረጃ ትምህርት ተቋም፣ መረጃው በ§99.34 መስፈርቶች መሠረት ከተማሪው ምዝገባ ወይም ዝውውር ጋር እስከተያያዘ ድረስ። (§99.31(a)(2))
- ፈቃድ ላላቸው የአሜሪካ የመንግሥት ተጠያቂነት ቢሮ ኃላፊ፣ የአሜሪካ አጠቃላይ ጠበቃ፣ የአሜሪካ ትምህርት ሚኒስትር፣ ወይም የስቴቱና የአካባቢው ትምህርታዊ ሥልጣኖች ተወካዮች፣ ለምሳሌ የወላጅ/አሳዳጊ/ተንከባካቢ የስቴት ትምህርታዊ ድርጅት ወይም መስፈርት ያሟላ/ች ተማሪ ስቴት ትምህርታዊ ድርጅት (SEA)። ከኦዲት ጋር ወይም የፌዴራል ወይም የስቴት ድጋፍ ካላቸው ትምህርታዊ መርሃ ግብሮች ግምገማ ጋር ወይም ከእነዚህ መርሃ ግብሮች ጋር በተያያዘ ከፌዴራል መስፈርቶች ማስከበር ወይም ሥራ ላይ ማዋል ጋር በተያያዘ፣ §99.35 ውስጥ ባሉት መስፈርቶች መሠረት መረጃ ማሳየት ይቻላል። እነዚህ አካሎች በተራቸው ፈቃድ ለሰጧቸው ኦዲት፣ ግምገማ ወይም የደንብ ማስከበር ሥራ በነሱ ስም ለሚሠሩ ወይ ተወካዮቻቸው የ PII መረጃ ሊያስተላልፉ ይችላሉ (§§99.31(a)(3) እና 99.35)።
- ተማሪው/ዋ የገንዘብ እርዳታ ማመልከቻ ካስገባበት/ካስገባችበት ጋር በተያያዘ፣ መረጃው ለማመልከቻ ብቃት መኖሩን፣ የእርዳታ መጠኑን ለመወሰን፣ የእርዳታውን ሁኔታ ለመወሰን ወይም የእርዳታውን ደንብና መስፈርቶች ለመወሰንና ሥራ ላይ ለማዋል አስፈላጊ ከነ። (§99.31(a)(4))
- የወጣቶች እሥር ቤትንና ሥርዓቱ መረጃው የተገለጸውን ተማሪ ማገልገል እንዲችል መረጃ ለማግኘት በተለይ በስቴት ደንብ ፈቃድ ላላቸው ከፍርድ በፊት በ§99.38 መሠረት ለስቴትና ለአካባቢው ባለሥልጣኖች። (§99.31(a)(5))
- ለሚከተሉት ምክንያቶች ለትምህርት ቤቱ ወይም ትምህርት ቤቱን ወክለው ጥናት ለሚያካሂዱ ድርጅቶች፡- (ሀ)አስቀድመው ገማች የኑ ፈተናዎች ለማጎልበት፣ ለማረጋገጥ ወይም ለመስጠት፣ (ለ) የተማሪ እርዳታ መርሃ ግብሮች ለማካሄድ፣ ወይም (ሐ) ትምህርት ለማሻሻል። (§99.31(a)(6))
- እሙን አድራጊ ድርጅቶ ሥራቸውን ማካሄድ እንዲችሉ። (§99.31(a)(7))
- ከ IRS ቀረጥ አኳያ ጥገኛ የነ መስፈርት ያሟላ ተማሪ ወላጆች/አሳዳጊዎች/ተንከባካቢዎች። (99.31(a)(8))
- የፍትህ ትእዛዝን ወይም በሕጋዊ መንገድ የተሰጠ መጥሪያን ለማክበር። (99.31(a)(9))
- በ§99.36 መሠረት ከጤና ወይም ከደህንነት ድንገተኛ ሁኔታ ጋር በተያያዘ ለተገቢው ባለሥልጣኖች. (§99.31(a)(10))
  - በ§99.37 ሥር ትምህርት ቤቱ "የማውጫ መረጃ" ብሎ የመደበው መረጃ ነው. (§99.31(a)(11))
- በስቴት ወይም በአሜሪካ ህንዶች ሕግ መሠረት አንድ ተማሪን ለጉዲፈቻ ምደባ የመስጠት ሕጋዊ ኃላፊነት ላለበት የደህንነት

ድርጅት ወይም የስቴት ድርጅት ለሚሠራ ሰው ወይም ለሌላ ተወካይ።(20 U.S.C. §1232g(b)(1)(L))

- የመርሃ ግብር ክትትል፥ በRichard B. Russell National School Lunch Act (ሪቻርድ ቢ ራሰል ብሔራዊ የትምህርት ቤት ምሳ ሕግ) ወይም በChild Nutrition Act of 1966 (የ1966 ዓ.ም. የተማሪ አመጋገብ ሕግ) ሥር ፈቃድ ያላቸው መርሃ ግብሮችን ለመገምገምና የክንውን መለኪያ ለማካሄድ እንዲችሉ ለ Food and Nutrition Service ተወካዮች ወይም ለግብርና ሚኒስትር፥ በተወሰኑ ሁኔታዎች ሥር። (20 U.S.C. § 1232g(b)(1)(K))

5. የተማሪ መረጃና የኢንተርኔት ትምህርታዊ አፖች

ተማሪዎች የሚጠቀሟቸው ትምህርታዊ የኢንተርኔት አፖች ለሚያቀርቡ ሻጮች CPS የተማሪ መረጃ ሊያካፍል ይችላል፥ ይህም የማስተማሪያ ተቋም ወይም አገልግሎት ሲን፥ ሻጮች መረጃውን የሚያገኙት ከትምህርት ቤት አውራጃው ጋር የተማሪ መረጃ ግለኝነት ስምምነት ከፈረሙ በኋላ ብቻ ወይም የተማሪው ወላጆች/ተወካዮች/ተንከባካቢዎች በጽሑፍ ፈቃድ ፈርመው ከሰጡ በኋላ ብቻ ነው። ፈቃድ የተሰጣቸው የኢንተርኔት ትምህርታዊ ግልጋሎቶች ዝርዝር በሚከተለው ድህረገጽ ይገኛሉ፡- bit.ly/CPSDigRes

6. መገኘት

ልጆች ወጥ በነ መንገድ ትምህርት ቤት ሲሄዱ የተሻለ መማር ይችላሉ፥ ከፍተኛ ስኬታማነትም ይኖራቸዋል። በመደበኛነትና በሰዓቱ ትምህርት ቤት ሲገኙ የትምህርት መቋረጥን ስለሚቀንስ የሁሉም ተማሪዎች ደህንነት የተጠበቀ እንዲን አስተዋጽኦ ያድርጋል። ለልጁ/ጅቷ የወደፊት ትምህርትና ሥራ ስኬታማነት በየቀኑና በሰዓቱ መገኘት ወሳኝ ናቸው። ተማሪዎች በሙሉ በትምህርት ቤት ውስጥና እያንዳንዱ ክፍል ውስጥ ቢያንስ ዘጠና አምስት በመቶውን (95%) ጊዜ እንዲገኙ ይጠበቅባቸዋል። እንደሚያውቁት በማሳቹሴትስ አጠቃላይ ሕጎች መሠረት፡- ዕድሜያቸው ከ6 እስከ 16 ዓመት ያሉ ልጆች ሁሉ ትምህርት ቤት የመሄድ ግዴታ አለባቸው።

ስኬታማ በነ መንገድ ትምህርት ቤት መገኘትና ትምህርታዊ ስኬት የሚቀረጸው ከአጸደ ሕጻናትና ከአንደኛ ክፍል ጀምሮ መኑን መገንዘብ ለሁሉም አስፈላጊ ነው። አለመገኘት በጊዜ ከተጀመረ፥ ልምዱ በልጁ/በልጅቷ የትምህርት ሕይወት በሙሉ ቀጥሎ ከትምህርት ቤት ወድቆ/ቃ እንዲወጣ/እንድትወጣ አደጋ ላይ ሊጥለው/ሊጥላት ይችላል። ልጅዎ ትምህርት ቤት በየቀኑና በሰዓት እንዲገኝ/እንድትገኝ ትብብርዎንና እርዳታዎን እንጠይቃለን። ማንኛውም ልጅ ሲቀር/ስትቀር ወላጅ/አሳዳጊ/ተንከባካቢ ትምህርት ቤቱ ጋር ደውሎ ያንኑ ጠዋት ሳይረፍድ ልጁ እንደሚቀር/እንደምትቀር ማሳወቅ አለበት። ስልክ ካልተደወለ፥ ተማሪው/ዋ ወደ ትምህርት ቤት ሲመለስ/ስትመለስ ከወላጅ/አሳዳጊ/ተንከባካቢ በጽሑፍ የቀረበትን/የቀረችበትን ምክንያት የሚያስረዳ ማስታወሻ ይዞ/ይዛ መምጣት አለበት/አለባት። እነዚህ ማስታወሻዎችን ዋና አስተማሪው ለትምህርት ዓመቱ ሙሉ በፋይል ውስጥ ማስቀመጥ አለበት/አለባት።

አንድ ልጅ በጥሩ ምክንያት አምስት (5) ወይም ከዛ በላይ ከቀረ/ች በቤት የትምህርት ቤት ሥራውን/ዋን መሥራት እንዲችል/እንድትችል ወላጅ/አሳዳጊ ትምህርት ቤቱን ማሳወቅ አለበት፥ ተማሪው/ዋ በሕመም ወይም በጉዳት ምክንያት ሁለት (2) ሳምንት ወይም ከዛ በላይ መቅረት ካለበት/ካለባት ትምህርት ቤቱ በቤት ውስጥ ትምህርት ለመስጠት አስፈላጊውን መሰናዶ ማድረግ እንዲችል ወላጅ/አሳዳጊ/ተንከባካቢ ትምህርት ቤቱን ማሳወቅ አለበት።

በጥሩ ምክንያት የተባለቱ መቅረቶች ተጠርጣሪ ከኑና በየጊዜው የሚከሰቱ ከነ ትምህርት ቤቱ የዶክተር ማስታወሻ እንዲቀርብ ይጠይቅና በቤት ውስጥ ጉብኝት በማድረግ ምክንያቱን ለማረጋገጥ እርምጃዎች ይወስዳል።

ተቆጣጣሪው/የከፈተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ዋና ኃላፊው መዝገብ ይይዝና አንድ ተማሪ በሕመም ምክንያት ነው ተብሎ በተደጋጋሚ ሲቀር ወይም ሲያረፍድ ተቆጣጣሪው/የከፈተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ዋና ኃላፊው ወይም የትምህርት ቤት ነርሷ ማስረጃ ከሐኪም እንዲመጣ ሊጠይቁ ይችላሉ። አንድ/አንዲት ልጅ ትምህርት ቤት የማይሄድ/የማትሄድ ከነ ወይም ዕድሜው/ዋ ከ6 እስከ 18 የነ ተማሪ ዘወትር ያለምክንያት ከትምህርት ቤት ከቀረ/ች ወይም የትምህርት ቤት ደንቦችን ሁልጊዜ የማያከብር/የማታከበር ከነ የትምህርት ቤት አውራጃው የ Child Requiring Assistance (CRA) (እርዳታ ፈላጊ ተማሪ) አቤቱታ ለፍርድ ቤት ሊያቀርብ ይችላል።

Cambridge Rindge and Latin School (ኬምብሪጅ ሪንጅ እና ላቲን ትምህርት ቤት) እንዲሁም High School Extension Program (የሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ቅጣይ መርሃ ግብር) ከማንኛውም ክፍል አራት (4) ጊዜ ሲቀር እንደ Attendance Violation (AV) (የመገኘት ጥሰት) ይቆጥረዋል። ከሚከተሉት ውስጥ የሚመደብ ጥሩ ምክንያት ኖሮ ሲቀር፥ የተረጋገጠ ሕመምን ጨምሮ፥ ተማሪ ላይ አይያዝም፥ Attendance Violation (AV) አያስከትልም፡- (ሀ) ከከባድ የግል ችግር ጋር የተያያዙ እንደ ሃዘን፥ የቤተሰብ ሞት፥ (ለ) የኃይማኖት በዓል ለማክበር፥ (ሐ) ከትምህርት ሰዓት ውጪ በጭራሽ ሊደረግ የማይችል የሐኪም ወይም የአማካሪ ቀጠሮ፥ (መ) በግል መገኘት የሚያሰፈልጋቸው ሕጋዊ ጉዳዮች፥ (ሠ) በትምህርት ቤት ውስጥና ውጪ የሚደረጉ ጊዜያዊ ማስወጣቶች፥ (ረ) የትምህርት ጉዞዎች ወይም ስብሰባዎች፥ (ሰ)ኮሌጅ መጎብኛ ቀኖች (11ኛ ክፍል ኖ ሁለት ቀኖች፥ 12ኛ ክፍል ኖ ሶስት ቀኖች)፥ እና (ሸ) ሁለተኛ ደረጃ ያለ ተማሪ ከአምስት ቀን ያልበለጠ ጉዞ ወይም ትምህርታዊ ልምድ።

ኖም በማንኛውም ክፍል ውስጥ ያለ ጥሩ ምክንያት አራት (4) ጊዜ ከተቀረ Attendance Violation (የመገኘት ጥሰት) ያስገኛል። ይህ ሲን የተማሪዎች ዲን ለተማሪው ለተርሙ የAV ነጥብ ይሰጠዋል። በተጨማሪም ሶስት (3) ጊዜ ያለ ጥሩ ምክንያት ካረፈዱ እንደ አንድ (1) ያለ ጥሩ ምክንያት መቅረት ይቆጠራል። ጥሩ ምክንያት የሌላቸው መቅረቶች የሚከተሉትን ያካትታሉ፡- (ሀ) ከትምህርት ቤት ወይም ከክፍሎች ያለ ጥሩ ምክንያት ዘወትር መቅረት፥ (ለ) ተቆጣጣሪው አስቀድሞ ፈቃድ ያልሰጠበት ጉዞዎች፥ (ሐ) ያለ ተቆጣጣሪ ፈቃድ ሥራ መፈለግ፥ (መ) ፈተና ላለመፈተን ወይም ለፈተና ለመዘጋጀት ቤት መቅረት፥ (ሠ) በትምህርት ቀን የተማሪዎች ዲን ጋር ሳይፈርሙ የትምህርት ሕንጻውን ለቅቆ መሄድ (ክፍል አለመግባት)፥ (ረ) ተኝቶ ማርፈድ ወይም በሌላ ምክንያት ትምህርት ቤት አርፍዶ መድረስ፥ (ሰ) ትምህርት ቤት ውስጥ ወይም በትምህርት ቤት አካባቢ ቆይቶ የተመደቡ ክፍሎች አለመሄድ (ክፍል አለመግባት)፥ እና (ሸ)ማንኛውም ሌላ ጥሩ ምክንያት የሌለው መቅረት ወይም ማንኛውም ጥሩ ምክንያት ኖሮ ወላጅ/አሳዳጊ/ተንከባካቢ ግን ደውሎ ወይም በጽሑፍ ያላሳወቀው

ወይም ተማሪው/ዋ ወደ ትምህርት ቤት ሲመለስ/ስትመለስ የዶክተር ማስታወሻ ይዞ/ዛ ያልተመለሰበት/ያልተመለሰችበት ሁኔታ። በተጨማሪም ማንኛውም በአንድ ክፍል ውስጥ አሥራ ሁለት (12) ጊዜ ያረፈደ/ች ተማሪ ለክፍሉ AV ይሰጠዋል/ይሰጣታል።

በትምህርት ቤት አውራጃው ፖሊሲ መሠረት፥ ተማሪው/ዋ በቀረ/ች እና/ወይም ባረፈደ/ች ቁጥር ትምህርት ቤቱ ወላጅ/አሳዳጊን ይሳውቃል፥ በጥሩ ምክንያት አራት ጊዜ ተማሪው/ዋ ሲቀርም ትምህርት ቤቱ ወላጅ/አሳዳጊን ያሳውቃል። ሥር የሰደደ ወይም ተደጋጋሚ ወይም ከአራት (4) ቀን በላይ የሚቆይ ሕመም ሲኖር፥ ወላጆች/አሳዳጊዎች/ተንከባካቢዎች የሕክምና ይለፈኝ ለማግኘት መሞከር ይችላሉ። ወላጆች/አሳዳጊዎች ማንኛውንም AV በተሰጠ በአሥር (10) ቀን ውስጥ በኬምብሪጅ ሪንጅና ላቲን ትምህርት ቤት ወይም የሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ቅጣይ መርሃ ግብር የግምገማ ኮሚቴ ፊት ይግባኝ ማለት ይችላሉ፥ ይግባኙ ተቀባይነት ካላገኘም በአሥር (10) ቀን ውስጥ ወላጆች/አሳዳጊዎች/ተንከባካቢዎች የትምህርት ቤቶች ዋና ተቆጣጣሪ ጉዳዩን እንዲያይላቸው በጽሑፍ ጥያቄ ማቅረብ ይችላሉ። የትምህርት ቤቶች ዋና ተቆጣጣሪው ውሳኔ የመጨረሻው ይናል።

የትምህርት ማህበረሰብ ቡድኖች AV ከተሰጣቸው ተማሪዎች ጋር አብሮ በመሥራት ከሚከተሉት ሶስት (3) ድጋፎች ውስጥ አንዱን ሥራ ላይ ያውላሉ፡-

ሀ. መልሶ የመግዛት ውል/ስምምነት መፈጸም (ለሁሉም ተማሪዎች የቀረበ)

ለ. የተማሪ ወርክሾፖች ውስጥ ተማሪን ማስመዝገብ (ተጨማር የጊዜ አስተዳደርና የተማሪ ድጋፍ ለሚፈልጉ ተማሪዎች)

ሐ. ከ LC ቡድን ጋር አብሮ የተፈጠረ የግል ድጋፍ ዕቅድ (ልዩ ድጋፍ ለሚያስፈልጋቸው ከባድ ችግር ላጋጠማቸው ተማሪዎች የሚውል)

ተማሪው/ዋ የድጋፍ ዕቅዱን ስኬታማ በነ መንገድ ካላጠናቀቀ/ች 10 ነጥብ ሊቀነስበት/ባት ይችላል።

7. እርዳታ የሚያስፈልገው/ጋት ልጅ (CRA)

እነዚህን አጥፊዎች በተመለከተ የፍርድ ቤቶችና የትምህርት መምሪያ ትኩረት ዕድሜን ከግምት ሳያስገቡ ቀዳማዊ መፍትሄ ማግኘት ነው። የማሳቹሴትስ አጠቃላይ ሕጎች በሚሰጡት ፍቺ መሠረት ዘወትር ያለምክንያት የሚቀር ተማሪና ተደጋጋሚ የትምህርት ቤት አጥፊ ማለት ከትምህርት ቤት አውቆ ሁልጊዜ የሚቀር ልጅ፥ ያለምክንያት የሚቀር ወይም የትምህርት ቤታቸውን ሕጋዊ ደንቦች የሚጥስ ልጅ ነው። በ M.G.L. c.76, §2 መሠረት፥ ወላጆች/አሳዳጊዎች/ተንከባካቢዎች ልጅን ትምህርት ቤት እንዲሄድ/እንድትሄድ ማስደረግ አለባቸው፥ ኖም ልጁ በስድስት ወር ውስጥ ከሰባት ቀኖች በላይ ወይም ከአሥራ አራት ግማሽ ቀኖች በላይ ከቀረ/ች የመገኘት ተቆጣጣሪ ወላጅ/አሳዳጊ/ተንከባካቢ ላይ አቤቱታ ያስገባና የገንዘብ መቀጮ ይደርስበታል። ,

በተጨማሪም ማንኛውም ዕድሜው/ዋ ከ6 እስከ 18 ለነ /ች ዘወትር ያለ ጥሩ ምክንያት ለሚቀር/ለምትቀር ልጅ በአንድ ተርም ውስጥ ከስምንት ጊዜ በላይ ያለ ጥሩ ምክንያት ለቀረ/ች ልጅና በተደጋጋሚ የትምህርት ቤት ደንቦችን ላላከበረ/ች ልጅ፥ ትምህርት ቤቶች የ CRA ማመልከቻ ሊፈልግ ይችላል።

ዘወትር መቅረትን ወይም ማርፈድን፥ ወይም ሁልጊዜ ያለ ጥሩ ምክንያት መቅረትን ወይም በተደጋጋሚ የትምህርት ቤት ደንቦችን መጣስን ውስጣዊ የትምህርት ቤት ቀዳማዊ መፍትሄዎች መጠቀም ስኬታማ ካልኑ የትምህርት ቤት መምሪያው ከፍርድ ቤት ጋር የ CRA እርምጃ ሊጀምር ይችላል። በሕጉ መሠረት የወጣቶች ፍርድ ቤት ከእነዚህ ጉዳዮች ጋር የተያያዘ የትምህርት ቤት መረጃን በሙሉ ማግኘት ይችላል።

8. ከትምህርት ቤት የሚወጡ ተማሪዎችን በተመለከተ ማስታወቂያ

የኬምብሪጅ መንግሥት ትምህርት ቤቶች ተማሪዎች አንደኛና ሁለተኛ ደረጃ ትምህርታቸውን ለማስጨረስ ተግቶ ይሞክራል። ዕድሜው አሥራ ስድስት ዓመት ወይም ከዛ በላይ የነ /ች ተማሪ ከትምህርት ቤት መውጣት ከፈለገ/ች፥ CPS በ M.G.L.c. 76, §18 ውስጥ የሚገኙትን መስፈርቶች ይከተልና ከዚህ በታች የሚገኙትን ሂደቶች በሥራ ላይ ያውላል፡-

1. ተቆጣጣሪው ወይም ተወካዩ ለተማሪው/ዋ ወላጅ/አሳዳጊ/ተንከባካቢ ተማሪው/ዋ ከሚከተሉት አንዱን እንዳረገ/ች የሚያሳውቅ ደብዳቤ ይሰጣል፡- (ሀ) ከትምህርት ቤት ላይመለስ/ላትመለስ ለመውጣት ዕቅድ እንዳለው/እንዳላት እንዳሳወቀ/ች፥ ወይም (ለ) ከትምህርት ቤት ለአሥራ አምስት (15) ቀን በተከታታይ እንደቀረ/ችና በመጨረሻ ትምህርት ቤት የተገኘበትን/የተገኘችበትን ቀን መጥቀስ።

   ተማሪው/ዋ ላይመለስ/ላትመለስ ከትምህርት ቤት መውጣቱን/መውጣቷን ለመገምገም፥ ተማሪው/ዋ በመደበኛነት ከትምህርት ቤት ከመውጣቱ/ቷ በፊት ትምህርት ቤቱ ከተማሪው/ዋና ከወላጆች/አሳዳጊዎች/ተንከባካቢዎች ጋር ስብሰባ ለማድረግ ቀጠሮ ይይዝና ተማሪው/ዋ ከትምህርት ቤት መውጣት የሚፈልግበትን/የምትፈልግበትን ምክንያቶችና ሌሎች አማራጭ ትምህርታዊ ሁኔታዎችና ሌሎች ምደባዎችን ለመወያየት ይሞክራል። ወላጅ/አሳዳጊ/ተንከባካቢ የስብሰባው ቀንና ሰዓት እንዲቀየርላቸው መጠየቅ ይችላሉ፥ ይህም ቀን ሲራዘም መጀመሪያ ተቆጣጣሪው ወይም ተወካዩ ደብዳቤውን ከሰጠበት ቀን ጀምሮ ከአሥራ አራት (14) ቀን በላይ መን የለበትም።

2. ስብሰባው ከወላጅ/አሳዳጊ/ተንከባካቢና ከተማሪው/ዋ ጋር ከተደረገ በኋላ፥ ተቆጣጣሪው የተወያዩበትን ጉዳይ፥ ማንኛውም በስብሰባው ላይ የተደረሰበትን ውሳኔ፥ ተማሪው/ዋ ወደ ትምህርት ቤት ይመለስ/ትመለስ እንደነ፥ አማራጭ ትምህርታዊ ምደባ ይቀጥል/ትቀጥል እንደነ፥ ሌሎች የድጋፍ አገልግሎቶች ይከተል/ትከተል እንደነ ወይም ከትምህርት ቤት እስከመጨረሻው ይለቅ/ትለቅ እንደነ የሚገልጽ ድብዳቤ ለተማሪው/ዋ ወላጅ/አሳዳጊ/ተንከባካቢ ይሰጣል።

3. በ M.G.L.c. 76, §18 ውስጥ ባሉት አቅራቦቶች መሠረት ማንኛውም እስከመጨረሻው የሚለቅ ተማሪ ትምህርቱን/ቷን መቀጠል ቢፈልግ/ብትፈልግ እንደ መባረር አይቆጠርበትም/አይቆጠርባትም ስለዚህ።

9. የልጅ ጥቃት

ዕድሜው/ዋ ከአሥራ ስምንት (18) ዓመት በታች የነ /ች ልጅ በጥቃት፥ ወሲባዊ ጥቃትን ጨምሮ፥ በቸልተኝነት፥ በምግብ እጥረት ምክንያት ከፍተኛ አካላዊ ወይም ስሜታዊ ስቃይ እየደረሰበት/እየደረሰባት ነው ብሎ በሙያው አንግ ግለሰብ ለመገመት በቂ ምክንያት ካለው ይህንን ለ Department of Children and Families ("DCF") (የልጆችና የቤተሰቦች መምሪያ) እንዲያሳውቅ የማሳቹሴትስ አጠቃላይ ሕጎች አንቀጽ 119 ክፍል 51A ያስገድደዋል። የልጆች ጥቃትን ወይም ቸልተኝነትን ለDCF የማሳወቅ ግዴታ ያለባቸው ባለሙያዎች የሚከተሉትን ያካትታል፦ ዶክተሮች፥ ተለማማጅ ሐኪሞች፥ ነርሶች፥ አስተማሪዎች፥ ትምህርታዊ አስተዳዳሪዎች፥ አማካሪዎች፥ የአመክሮ ሰዎች ተቆጣጣሪ መኮንን፥ የትምህርት ቤት መገኘት መኮንን፥ ማህበራዊ ሠራተኞች፥ የስነ ልቦና ባለሙያዎችና ፖሊሶች። ማሳወቅ ያለባቸው ለተገቢው ያካባቢው ቢሮ ወይም 24 ሰዓት መደወል በሚቻልበት ስልክ ቁጥር ነው፦-1-800-792-5200። እነዚህ ባለሙያዎች በአርባ ስምንት (48) ሰዓት ውስጥ መደበኛ የ DCF ማሳወቂያ ቅጽ ተጠቅመው የማሳወቅ ግዴታ በማሳቹሴትስ ሕግ መሠረት አለባቸው። ለእያንዳንዱ አዲስ ጉዳት ወይም ዳግም ጉዳት አዲስ ማሳወቂያ ቅጽ መሞላት አለበት።

ዕድሜው ከአሥራ ስምንት ዓመት በታች የነ ልጅ በጥቃት፥ ወሲባዊ ጥቃትን ጨምሮ፥ በቸልተኝነት፥ በምግብ እጥረት ምክንያት ከፍተኛ አካላዊ ወይም ስሜታዊ ስቃይ እየደረሰበት/እየደረሰባት ነው ብሎ የሚያምን ሠራተኛ 51A ማስታወቂያ እንዲሞላ ለተቆጣጣሪው/ለከፍተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ዋና ኃላፊው ባስቸኳይ ማሳወቅ አለበት።

የልጅ ጥቃት እና ቸልተኝነት አንድ ልጅ የጤንነቱና የደህንነቱ ኃላፊነት ባለበት ሰው (ወይም ሰዎች)፥ የመንግሥት ትምህርት ቤት ሠራተኞችን ጨምሮ፥ አካላዊ ወይም የአእምሮ ጤንነት ወይም ደህንነት የሚጎዳ ወይም አደጋ ላይ የሚጥል ማንኛውም ክስተት ሲደርስበት እንዲታወቅ መደረግ አለበት። ያለ ጥሩ ምክንያት ከትምህርት ቤት መቅረት በራሱ ሪፖርት የሚደረግ ጉዳይ አይደለም።

ጥቃት የሚከተሉትን ያካትታል፦

- ከድንገተኛ አደጋ ሁኔታ ውጪ ለምሳሌ በድብደባ፥ በመቁረጥ፥ በማቃጠል፥ በአጥንት ስብራት፥ በብዙ ቁስሎች ምክንያት አካላዊ፥ የአእምሮ ወይም የስሜት ጉዳት ሲከሰት፥
- ሱስ የሚያሲዝ ዕጽ ላይ ሲወለዱ አካላዊ ጥገኝነት ሲኖር፥
- አንድን ሰው አስገድዶ፥ አስፈራርቶ ወይም ጎድቶ ወሲብ መፈጸም። ይህም በጊዜያዊም ነ በቋሚ የአእምሮ ወይም የአካል ጉዳት ምክንያት ወይም ለአካለ መጠን ያልደረሰ ልጅን ጨምሮ ፈቃድ መስጠት የሚሳነው ሰው ላይ ወሲብ መፈጸምን ይጨምራል። እንደነዚህ ዓይነት ተገቢ ያልኑ ጥቃቶችና ድብደባዎች፥ አስገድዶ መድፈር፥ በከፍተኛ ኃይል አስገድዶ መድፈር፥ አስገድዶ መድፈርና ጥቃት፥ አስገድዶ ለመድፈር ጥቃትና ተፈጥሯዊ ያልኑና ብልሹ ድርጊቶች እንደ ወሲባዊ ጥቃት ይቆጠራሉ።
- ተገቢ ያልነ ጥቃትና ድብደባ የግል የኑ የሰውነት ክፍሎችን አግባብ በሌለው መንገድና ሳይፈለግ መንካትን ይጨምራል። ዕድሜው ከ14 ዓመት በታች የነ ሰው ለእንደዚህ ዓይነት ወሲባዊ ተግባር በሕግ አኳያ ፈቃድ መስጠት አይችልም።
- ቸልተኝነት አለ የሚባለው አንድን ልጅ ለመንከባከብ አንድ ሰው ወይም ሰዎች የገንዘብ አቅሙ እያለው/እያላቸው የሚከተሉትን ሳያቀርብ/ቡ ሲቀር/ሩ ነው፦-
    - በቂ ምግብ፥ ልብስ፥ መጠለያ፥ ትምህርት ወይም ሕክምና እና/ወይም
    - አግባብ ያለው ቁጥጥር እና/ወይም አሳዳጊነት።

10. የእንክብካቤና ጥበቃ እርምጃዎች

ልጆችን ትምህርት ቤት አለመላኩ ይበልጥ ከከፉ የጥቃትና የቸልተኝነት ችግሮች ጋር አብሮ ከነ የሚከሰተው፥ M.G.L. c.119, §24 ውስጥ ባሉት አቅራቦቶች መሠረት የእንክብካቤና ጥበቃ እርምጃ ሊጀመር ይችላል። በእንክብካቤና ጥበቃ እርምጃ ላይ ፍርድ ቤቱ "ልጁ/ልጅቷ በከፍተኛ ጥቃት ወይም ቸልተኝነት ምክንያት እየተሰቃየ/ች ነው ወይም አደጋ ላይ የመውደቅ ዕድሉ/ሏ ከፍተኛ ነው ብሎ በበቂ ምክንያት ካመነ" የልጁ/ልጅቷ እንክብካቤ ባስቸኳይ ወደ ሌላ እንዲዛወር ሊያዝ ይችላል።

11. ያልተገኘ ወይም የጠፋ ልጅ

ያልተገኘ ወይም የጠፋ ልጅ ሁኔታ በተለያዩ ሁኔታዎች ሊገለጽ ይችላል። አንዳንድ ምሳሌዎች እንደሚከተሉት ናቸው፦-

- አንድ ልጅ ወደ ክፍል ተመልሶ አልመጣም እንዲሁም በሕንጻ ውስጥ ወይም በትምህርት ቤት ቅጥር ግቢ ውስጥ አልተገኘም፥
- ልጁ/ልጅቷ ከክፍል ሲለቀቅ/ስትለቀቅ ከወላጁ/ጇ ጋር ወይም ከተወካዩ ጋር መሄዱን/መሄዷን የክፍል አስተማሪው ማረጋገጥ አልቻለም፥
- ልጁ/ልጅቷ አውቶቡስ ላይ መሳፈሩን/ሯን የክፍል አስተማሪው ማረጋገጥ አልቻለም፥ እና
- ወላጅ/አሳዳጊ/ተንከባካቢ ትምህርት ቤት ደውሎ/ላ ልጁ/ልጅቷ በተለመደው ሰዓት ቤት እንዳልደረሰ/ች አሳውቋል/አሳውቃለች።

በትምህርት ቤት አውቶቡስ ለሚመላለሱ ልጆች ሁሉ የመጓጓዣ ቢሮን መገናኘት።

ዋና ተቆጣጣሪውንና የደህንነትና ጥበቃ ቢሮን ማሳወቅ።

ወላጅ/አሳዳጊ/ተንከባካቢን መገናኘት።

በአደጋ ጊዜ በቀጥታ ፖሊስ መጥራት። አለበለዚያ የደህንነትና ጥበቃ ቢሮ ከእርስዎ ጋር ከተወያየ በኋላ ተገቢውን ዝርዝር ይዞ ፖሊስ ጋር ይደውላል።

ሂደት

የመጀመሪያ ሪፖርት ያቀረቡ ከወላጆች/አሳዳጊዎች/ተንከባካቢዎች ጋር ቃለ ምልልስ ማድረግ።

ልጁ/ልጅቷ በርግጥ አለመገኘቱን/ቷን ወይም መጥፋቱን/ቷን ማረጋገጥ።

ከመጥፋቱ ጋር የተያያዙትን ሁኔታዎች መለየት።

የጠፋው/የጠፋችው ልጅ መቼ፥ የትና ማን መጨረሻ እንዳያት መገምገም።

የልጁ/የልጅቷን ፋይል ማገላበጥ፥ የሚመለከተውን መረጃ ሁሉና ድንገተኛ ስልክ ቁጥሮች ዝግጁ አድርጎ ማስቀመጥ እንዲሁም የልጁ/ልጅቷ አሳዳጊ ሁኔታን ማረጋገጥ። (ከተቻለ ፎቶ)

የልጁን/የልጅቷን የተሟላ መግለጫ ልብሱን/ሷን፥ ቁመት፥ ክብደት፥ ቀለም፥ ልዩ ምልክቶችን ጨምሮ ዝግጁ መን ለለበት።

የጓደኞች/የሚውቃቸው ሰዎች ዝርዝር መቀነባበር አለበት።

ባለው መረጃ ላይ ተመሥርቶ ስለ ክስተቱ የመጀመሪያ ግምገማ ማድረግ፦ ከቤተሰብ ውጪ ጠለፋ፥ የቤተሰብ ጠለፋ፥ ሽሽት፥ መንገድ አለማወቅ፥ መጎዳት፥ አለመገኘት ወይም መጥፋት። ተቆጣጣሪው/የከፍተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ዋና ኃላፊው ተወካዩ በሂደቱ መሠረት ከላይ የተዘረዘረውን መረጃ ሁሉ ጠብቆ ልጁ/ልጅቷ እስከሚገኝ/እስከሚገኝ ድረስ መረጃው እንዲገኝ ያደርጋል።

12. መጓጓዣ

ትምህርት ቤት ሁሉ የአንደኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ልጆች ትክክለኛው አውቶቡስ ላይ መሳፈራቸውን ማረጋገጫ ውስጣዊ የራሱ ሥርዓት ሊኖረው ይገባል። መጓጓዣ ለሚጠቀሙ ላልተገኙ ልጆች የመጓጓዣ መምሪያ ጋር በስልክ ቁጥር 617-349-6862 ይደውሉ።

ወላጅ/አሳዳጊ/ተንከባካቢ ወይም ተወካይ የጊዜ ሰሌዳ ያለው ማቆሚያ ጋር ከሶስት ጊዜ በላይ ልጁን/ልጅቷን ሳይጠብቁ ከቀሩ በአውቶቡስ የመመላለስ መብታቸውን ያጣሉ።

13. ደረጃውን የጠበቀ ፈተና

በየዓመቱ ማሳቹሴትስ ትምህርት መምሪያ በወሰነው መሠረት በየክፍል ደረጃዎች CPS የ MCAS 2.0 ፈተና ይሰጣል። በተጨማሪም CPS በየዓመቱ ለእንግሊዝኛ ቋንቋ ተማሪዎች በማሳቹሴትስ የትምህርት መምሪያ መስፈርቶች መሠረት እንዳግባቡ የ ACCESS ፈተና ይሰጣል።

14. የጾታዊ ግንኙነት ትምህርት

ትምህርት ቤቶች በዋናነት የሰው ጾታዊ ግንኙነት ትምህርት ወይም የሰው ጾታዊ ጉዳዮች የትምህርት ሥርዓትን በተመለመከተ ወላጆች/አሳዳጊዎች/ተንከባካቢዎችን አስቀድመው ማሳወቅ በሕግ ይጠበቅባቸዋል። ሁልጊዜ በልግ ላይ የጤና ትምህርት ሥርዓትን በተመለከተ ድብዳቤ ወደ ቤት ይላካል፥ ይህም በየክፍል ደረጃ የሚሰጡትን ጾታዊ ትምህርቶች ይገልጻል። ወላጆች/አሳዳጊዎች/ተንከባካቢዎች ልጆቻቸው እነዚህን ትምህርቶች እንዲወስዱ ፈቃድ መስጠት የለባቸውም፥ ልጆቻቸው እነዚህ ትምህርቶች ላይ እንዳይካፈሉ የማድረግ መብትም አለቸው። ወላጆች/አሳዳጊዎች/ተንከባካቢዎች ይህን ለማድረግ ለተቆጣጣሪው/ለከፍተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ዋና ኃላፊው ልጃቸው ከትምህርቱ እንዲወጣ/እንድትወጣ የሚጠይቅ ደብዳቤ መላክ ይችላሉ። ማንኛውም ትምህርቱን መቃኘት የሚፈልግ ወላጅ/አሳዳጊ የልጃቸው አስተማሪን ወይም የጤና ትምህርት መርሃ ግብር ኃላፊን በስልክ ቁጥር 617-349-6851 ደውለው ማነጋገር ይችላሉ።

15. የአካል እገታዎች

የኬምብሪጅ ትምህርት ቤት ኮሚቴ ለሠራተኞቹና ለተማሪዎቹ ደህንነቱ የተጠበቀና ምርታማ የሥራና የትምህርት ቦታ የመፍጠር ፖሊሲ አለው፣ እንዲሁም በ CPS ውስጥ ያለ እያንዳንዱ ተማሪም ከማሳቹሴትስ የአንደኛ ደረጃና ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት መምሪያ ደንቦች ጋር የማይጣጣም የአካል እገታ ነጻ መሆኑን ማረጋገጥና የአካል እገታን የሚጠቀሙት በከፍተኛ ጥንቃቄ፣ በድንገተኛ ሁኔታዎች ላይ ሌሎች ሕጋዊና ጫና የማይፈጥሩ መንገዶችን መጠቀም ካልቻሉ ወይም አግባብ ከሌላቸው ብቻ ነው። የትምህርት ቤት ሠራተኞች የአካል እገታ መጠቀም የሚችሉት ሌላ ምንም ዓይነት መንገድ መጠቀም ካልቻሉና አንድ ተማሪን እና/ወይም የትምህርት ቤት ማህበረሰብ አባልን ከአስቸኳይ፣ አደገኛ አካላዊ ጉዳት ለመጠበቅ ሲያስፈልግ ብቻ ነው። የአካል እገታ መጠቀም አስፈላጊ ከነ፣ የትምህርት ቤት ሠራተኞች ተማሪው ላይ በአካል እገታው ምክንያት ጉዳት እንዳይደርስ ጥንቃቄ ማድረግ አለባቸው። ይህ ፖሊሲ በመንግሥት የገንዘብ ድጋፍ የሚማሩ ተማሪዎች፣ ልዩ ትምህርት ለማግኘት ብቃት ኖሯቸው የተገኙ ተማሪዎችን ጨምሮ፣ የሚጠብቋቸው ፌዴራልና ስቴት ሕጎች ላይ ውስንነት አይፈጥርም። በተጨማሪም ይህ ፖሊሲ ማንኛውንም አስተማሪ፣ ሠራተኛ ወይም የመንግሥት ትምህርት መርሃ ግብር ተወካይ ተማሪዎችን፣ ሌሎችን ወይም እራሳቸውን ከአስቸኳይ፣ አደገኛ አካላዊ ጉዳት ለመጠበቅ አግባብ ያለውና አስፈላጊ ኃይል ከመጠቀም አያግዳቸውም።

የ CPS የትምህርት ቤት አውራጃው ድህረ ገጽ ላይ ተለጥፈው የሚገኙ እንዲሁም ከከፍተኛ ትምህርት ቤት ዋና ኃላፊው ቢሮ ሊገኙ የሚችሉ ከዚህ ፖሊስ ጋር የተያያዙ የጽሑፍ ሂደቶችና መመሪያዎች አሏቸው፣ እነሱም የሚከተሉትን ይገልጻሉ፦ (1) ወዲያውኑ እርምጃ ሊያስወስዱ የሚችሉ አግባብ ያላቸው ለተማሪ ምግባር አጸፋ ምላሾች፣ እና (2) አንድ ኃይለኛ፣ እራሱን ሊጎዳ ያለ ተማሪን ለማስታገስ እና/ወይም በተማሪ ቡድኖች መካከል ወይም አንድ ተማሪ ላይ አደገኛ ሁኔታ ሲፈጠር ለማብረድ በመጀመሪያ ሊጠቀሟቸው የሚችሏቸው ሌሎች አማራጮች፣ እንዲሁም በአደገኛ ሁኔታዎች ላይ የአካል እገታን ላለመጠቀም ሌሎች መንገዶችን መጠቀም።

የአካል እገታ ሂደቶች

<u>ፍቺዎች</u>

"ፈቃድ" ማለት ስምምነት የሚፈለግበት ጉዳይን በተመለከተ አንድ ወላጅ/አሳዳጊ/ተንከባካቢ ሙሉ መረጃ በትውልድ ቋንቋው ወይም በሌላ ወላጁ/አሳዳጊው/ተንከባካቢው በሚገባው መንገድ ቀርቦለት ጉዳዩ እንዲፈጸም መስማማቱን በጽሑፍ ሲያሳውቅና ስምምነቱ በፈቃደኝነት ኖ በማንኛውም ጊዜ ሊሰረዝ እንደሚችል ሲረዳ ነው። ስምምነቱ ጉዳዩን ማናቸውንም ተላልፈው የሚሰጡ መዝገቦችን (ካሉ) በዝርዝርና ለማን እንደሚተላለፉ የሚያገልጽ ነው።

"እገታ" ማለት የተማሪ አካላዊ እንቅስቃሴን በሚታገልበት ጊዜ ኃይል ተጠቅሞ መገደብ።

"አካላዊ እገታ" ማለት የአንድ ተማሪን የመንቀሳቀስ ነጻነት የሚከለክል ወይም በከፍተኛ ሁኔታ የሚገድብ ቀጥተኛ የአካል ንክኪ። አካላዊ እገታ ማለት ፊትን ወደ መሬት አድርጎ መያዝን፣ በቁሳቁስ ማሰርን ወይም በመድሃኒት ማገትን አይጨምርም። በተጨማሪም የአካል እገታ የሚከተሉትን አይጨምርም፦ ኃይል ሳይጠቀሙ የተማሪን ደህንነት ለመጠበቅ ወይም ራሱን እንዳይጎዳ ማገድ፣ አንድ ሙያ ለማስተማር፣ ትኩረትን ወደ ሌላ ለመሳብ፣

ለማጽናናት ወይም በአካል ሲያጅቡ የአካል መምሪያ መስጠት ወይም አጭር አካላዊ ንክኪ መፍጠር።

“በአካል ማጀብ” ማለት አንድ ሁከተኛ ተማሪ ደህንነቱ ወደተጠበቀ ቦት እንዲያመራ እጁን፣ የእጅ አንጓውን፣ ክንዱን፣ ትከሻውን ወይም ጀርባውን ለአጭር ጊዜ መንካት ወይም መያዝ ነው።

“በቁሳቁስ ማገት” ማለት የአንድ ተማሪን እንቅስቃሴ ወይም የተማሪን አንድ የሰውነት ክፍል መደበኛ እንቅስቃሴ ለማገት አንድ መሳሪያ መጠቀም ነው። ዶክተር ያዘዘው መከላከያ ወይም ማረጋጊያ መሳሪያ በቁሳቁስ እንደማገት አይቆጠርም። **ዶክተር ያዘዘውና የተማሪው ወላጆች/አሳዳጊዎች/ተንከባካቢዎች ፈቃድ ሰጥተውበት ካልነ በስተቀር የቁሳቁስ ማገቻ መጠቀም በጥብቅ የተከለከለ ነው።**

“ማግለል” ማለት አንድ ተማሪ እንዳይሄድ አድርጎ አንድ ክፍል ውስጥ ወይም አንድ አካባቢ ሳይፈልግ ብቻውን ማቆየት። ማግለል በ 603 CMR 46.02 ውስጥ እንደተጠቀሰው ዓይነት የተማሪ ቅጣት አይደለም። **የማግለል ኢጋታ በጥብቅ የተከለከለ ነው።**

“የተማሪ ቅጣት” ማለት የባሕርይ ድጋፍ ማድረጊያ ስልት ሲን አንድ ተማሪ እራሱ ፈልጎ ወይም አስተማሪ አዝዞት ለአጭር ጊዜ ከክፍል ትምህርቱ ተለይቶ እራሱን እንዲያረጋጋ ሲወጣ። በተማሪ ቅጣት ወቅት ተማሪው ያለፍላጎቱ አንድ ቦታ ብቻ እንዲን መወሰን የለበትም፣ ሁልጊዜ አንድ የትምህርት ቤት ሠራተኛ ሊከታተለውም ይገባል። በማንኛውም ጊዜ ሠራተኛ ከተማሪው ጋር ሊን ወይም በቀላሉ እንዲገኝ ኖ መገኘት አለበት። የተማሪ ቅጣት ጊዜ የሚያበቃው ተማሪው እንደተረጋጋ ወይም ሰላሳ (30) ደቂቃ እንዳላፈ መን አለበት። የተማሪ ቅጣት በክፍሉ ውስጥ ቢን ይመረጣል። ማንኛውም ከክፍሉ ውጪ ለተማሪ ቅጣት ሊጠቀሙት ያሰቡት ቦታ ጥቅም ላይ ከመዋሉ በፊት የተማሪ አገልግሎቶች ቢሮ ያጸደቀው መን አለበት።

“መድሃኒት” ማለት አንድ ባሕርይን ጊዜያዊ በነ መልኩ ለመቆጣጠር መድሃኒት መስጠት ነው። **ዶክተር በግልጽ ያዘዘውና የተማሪው ወላጆች/አሳዳጊዎች/ተንከባካቢዎች በጽሑፍ ፈቃድ የሰጡበት ካልነ በስተቀር መድሃኒት መጠቀም በጥብቅ የተከለከለ ነው።**

“ፊት ወደታች እገታ” ማለት አንድ ተማሪን በአንድ ቦታ ይዞ ለማቆየት ፊቱን መሬት ላይ ወይም ሌላ ቦታ ላይ አድርጎ፣ ጫን አድርጎ መያዝ ማለት ነው። **ፊት ወደታች እገታ መጠቀም በጥብቅ የተከለከለ ነው።**

“የከፍተኛ ደርጃ ትምህርት ቤት ዋና ኃላፊ” ማለት የመንግሥት ትምህርት ቤት መርሃ ግብር የማስተማር ሂደት አለቃ ወይም ተወካይ ነው።

<u>የእገታ አጠቃቀም</u>

ሌሎች ሁሉ ሕጋዊና ብዙ ተጽዕኖ የማያደርጉ አማራጮች ካልተሳኩ ወይም የተማሪውን ኃይለኝነትና ጥቃት፣ እራስን የሚጎዳ ባሕርይ እና/ወይም በተማሪዎች መካከል ወይም አንድ ተማሪ ላይ የሚከሰት አደገኛ ባሕርይን ለማስወገድ አግባብ የሌላቸው ነው ከተገኙና ሌላ አማራጭ ከጠፋ የአካል እገታን መጠቀም ይቻላል። ማለትም **የአካል እገታን መጠቀም የሚቻለው በአደገኛ ሁኔታ ውስጥ ሌላ ምንም ዓይነት አማራጭ ከጠፋና የተማሪው ባሕርይ ለራሱ ወይም ለሌሎች ድንገተኛና ከፍተኛ ጉዳት የሚያደርስ ከነና ተማሪው በአፍ የሚነገረውን መመሪያ ካልተከተለ ወይም ሌሎች ብዙ ተጽዕኖ የማያደርጉ አማራጮች ተሞክረው ካልሰሩ ወይም አማራጮቹ ለሁኔታው ተገቢ ነው ካልተገኙ ብቻ ነው።** ማንኛውም አካላዊ እገታ በእንደዚህ ዓይነት አግባብ ባለው ኃይል መወሰንና ለአጭር ጊዜ የሚጠቀሙት ኖ አንድ ተማሪን ወይም ሌላ የትምህርት ቤት ማህበረሰብ አባልን ከድንገተኛና ከፍተኛ አካላዊ ጉዳት ለመጠበቅ መን አለበት። አካላዊ እገታ ሊደረግ የሚችለው ስለ አካላዊ እገታ በአግባቡ ሥልጠና ባገኙ የትምህርት ቤት ሠራተኞች ብቻ ነው።

<u>ሌሎች የእገታ አጠቃቀም ውስንነቶች</u>

የሚከተሉት አሠራሮች በጥብቅ የተከለከሉ ናቸው፦ (1) ከላይ በተጠቀሱት አቅራቦቶች ጋር የማይጣጣም የእገታ አጠቃቀም፣ (2) እገታን እንደ ሥርዓት ማስያዣ ወይም እንደ ቅጣት መጠቀም፣ ንብረት ሲወድም ወይም የትምህርት ቤት ሥርዓትን ሲረብሹ እንደ አጸፋ መልስ መጠቀም ወይም ተማሪ አንድ የትምህርት ቤት ደንብን ላላከብርም ሲል ወይም የትምህርት ቤት ሠራተኛ የነገረውን መመሪያ አልከተልም ሲል፣ ወይም ድርጊቶቹ ድንገተኛና ከፍተኛ አካላዊ ጉዳት የሚያስከትሉ ሳይኑ በቃል ማስፈራራት በጥብቅ የተከለከለ ነው፣ (3)የፊት ወደታች እገታ መጠቀም፣ (4)የቁሳቁስ እገታ መጠቀም፣ (5)ዶክተር ያላዘዘውና የተማሪው ወላጆች/አሳዳጊዎች/ተንከባካቢዎች በጽሑፍ ፈቃድ ያልሰጡበት መድኃኒት መጠቀም፣ (6) ተማሪዎች መተንፈስ እንዳልቻሉ ምልክት ሲያደርጉ ወይም ከፍተኛ አደጋ ላይ ያሉ ሲመስሉ (ትንፋሽ እጥረትን፣ እጅግ በጣም ለተራዘመ ጊዜ ማልቀስ ወይም ማሳልን ጨምሮ) እገታን መጠቀም።

እገታ ከምላሾች አንዱ ኖ የግል ትምህርት መርሃ ግብር (IEP) ውስጥ መካተት አይችልም። ኖም በተደጋጋሚ እራሳቸውን የሚጐዱ ባሕርይ የሚያሳዩ ተማሪዎችን በተመለከተ በድንገተኛ ሁኔታ ላይና ለተወሰነ ጊዜ እገታ መጠቀምን እንደ ሐሳብ አድርገው የከፍተኛ ትምህርት ቤት ዋና ኃላፊዎች ለወላጆች/አሳዳጊዎች/ተንከባካቢዎች ለብቻው በጽሑፍ ሊያቀርቡ ይችላሉ። በእንደዚህ ዓይነት ሁኔታ ላይ ለምን ያክል ጊዜ እንደነ እገታውን ተጠቅመው፣ እየቀነሱ ሄደው እንደሚያቆሙ ዕቅዱ ለወላጆች/አሳዳጊዎች/ተንከባካቢዎች በዝርዝር ማሳወቅ አለበት። የከፍተኛ ትምህርት ቤት ዋና ኃላፊው ይህን በሥራ ላይ ከማዋሉ በፊት ከለወላጆች/አሳዳጊዎች/ተንከባካቢዎች በጽሑፍ ፈቃድ ማግኘት አለበት።

<u>አካላዊ እገታን ባግባቡ መጠቀም</u>

አካላዊ እገታን መጠቀም የሚችሉት ተገቢውን ሥልጠና ያገኙ የትምህርት ቤት ሠራተኞች ብቻ ናቸው። ሥልጠና ያገኙ የትምህርት ቤት ሠራተኞች ማለት ወይ ጥልቀት ያለው ሥልጠና ያገኙ ግለሰቦች ወይም ከዚህ በታች የተገለጸውን አስፈላጊ መደበኛ ሥልጠና ያገኙ ግለሰቦች ናቸው። ሲቻል፣ አካላዊ እገታ የሚጠቀመው ሰው ቢያንስ በአንድ የእገታው ተሳታፊ ባልነ አዋቂ ምስክርነት ፊት መን አለበት። የትምህርት ቤት ሠራተኞች አካላዊ እገታ ሲጠቀሙ የሚጠቀሙት ኃይል ተማሪውን ወይም ሌሎችን ከአካላዊ ጉዳት ለመከላከል የሚበቃ መጠን ብቻ መን

አለበት። በተጨማሪም የትምህርት ቤት ሠራተኞች አካላዊ እገታ ሲጠቀሙ ከዚህ በታች በተዘረዘሩት የደህንነት መስፈርቶች መሠረት ኖ ከሁሉም በላይ ደህንነት የሚጠብቀውን ዓይነትና ከሁኔታው ጋር የሚጣጣም ዓይነት መንገድ ተጠቅመው መን አለበት፣ እንዲሁም እገታ መጠቀሙን በተቻለ ፍጥነት ቶሎ ማቆም አለባቸው። ተማሪው እራሱም ነ ሌሎች ላይ አደጋ እንደማያደርስ እንደታወቀ፣ ወይም ተማሪው መተንፈስ እንዳልቻለ እንዳሳወቀ፣ ወይም ተማሪው ከፍተኛ ውጥርት ውስጥ እንደነ እንደታወቀ ለምሳሌ መተንፈስ ቢያቅተው ወይም ያለማቋረጥ ቢይለቅስ ወይም ቢያስል ወዲያውኑ አካላዊ እገታው መቆም አለበት። ኖም እነዚህ የሥልጠና መስፈርቶች አንድ አስተማሪን፣ ሠራተኛን ወይም የትምህርት ቤት ተወካይን ተማሪዎችን፣ ሌሎች ሰዎችን ወይም እራሳቸውን ከጥቃት፣ ወይም ከፈጣን፣ ኃይለኛ አካላዊ ጉዳት ለመከላከል ተገቢና አስፈላጊ የነ ኃይል ከመጠቀም አያግዳቸውም።

<u>የደህንነት መስፈርቶች</u>

አንድ ተማሪን ከመተንፈስ ወይም ከመናገር በሚያግድ ሁኔታ እገታ መጠቀም ክልክል ነው። የትምህርት ቤት ሠራተኞች እገታ በሚጠቀሙ ጊዜ ያለማቋረጥ የተማሪውን ሁኔታ፣ የቆዳ ቀለሙን፣ የሰውነት ሙቀቱንና አተነፋፈሱን ጨምሮ መከታተል አለባቸው። ተማሪው እራሱ ላይ ወይም ሌሎች ላይ አደጋ እንደማያደርስ የትምህርት ቤት ሠራተኛው ካረጋገጠ በኋላ ወዲያውኑ እገታውን ማቆም አለበት። በተጨማሪም እገታዎችን ሲጠቀሙ አካል ላይ ጉዳት በማያመጡ መንገድ መን አለበት። **ተማሪው አካላዊ እገታ ላይ ኖ መተንፈስ እንዳልቻለ ካሳወቀ፣ ወይም ከፍተኛ ውጥርት ውስጥ እንደነ እንደታወቀ ለምሳሌ መተንፈስ ቢያቅተው ወይም ያለማቋረጥ ቢይለቅስ ወይም ቢያስል አካላዊ እገታው ወዲያውኑ መቆም አለበት፣ የትምህርት ቤት ሠራተኞችም ሕክምና እንዲያገኝ አስፈላጊውን እርምጃ መውሰድ አለባቸው።** አካላዊ እገታ መጠቀምን በተመለከተ የሚታወቅ የጤና ወይም የስነልቦና ውስንነት መኖሩን እና/ወይም የባሕርይ እርዳታ ዕቅዶች እንዳሉ፣ እንዲሁም በተማሪው የሕይወት ታሪክ ውስጥ የሚታወቅ ወይም አለ ተብሎ የሚገመት የስቃይ ገጠመኝ መኖሩን የትምህርት ቤት ሠራተኞች በመጀመሪያ አይተው ከግምት ውስጥ ማስገባት አለባቸው። አካላዊ እገታ በሚያደርጉ ወቅት በማንኛውም ጊዜ የትምህርት ቤት ሠራተኞቹ የ Office of Student Services (ተማሪ አገልግሎቶች ቢሮ) ጋር ደውለው የባሕርይ ባለሙያዎችን ማግኘት ወይም የ Crisis Intervention Team (የውጥረት ማስወገጃ ቡድን)ን መገናኘት ወይም ተማሪው ከፍተኛ አካላዊ ጥንቀት ላይ ከነ የሕክምና እርዳታ ለማግኘት ሌላ እርምጃ መውሰድ ይችላሉ።

<u>መከታተያ ሂደቶችና ማሳወቂያ መስፈርቶች</u>

ተማሪው ከእገታ ከተለቀቀ በኋላ በተገቢው ጊዜ የከፍተኛ ትምህርት ቤት ዋና ኃላፊው ወይም ተወካዩ የሚቀጥሉትን መከታተያ ሂደቶች በሥራ ላይ ማዋል አለበት:-

ሀ. እገታውን ያስከተለውን ባሕርይ በተመለከተ ለመወያየት ከተማሪው ጋር እገታውን መቃኘት፣

ለ. እገታውን ከተጠቀሙት የትምህርት ቤት ሠራተኞች ጋር ትክክለኛ የእገታ ሂደቶች መከተላቸውን ለማወቅ ስለ ጉዳዩ ውይይት ማካሄድ፣ እና

ሐ. ጉዳዩን ካዩ የዓይን ምስክር ተማሪዎች ጋር ክትትል ማድረግ፣ ከአስተማሪና ከአማካሪ ጋር ውይይትን ወይም የመልሶ አዳሽ አሠራሮችን ጠቀሜታ ጨምሮ፣ እና

መ. የእገታው ማስታወቂያ በጽሑፍ ወደ ተማሪ አገልግሎቶች ቢሮና ወደ ከፍተኛ ትምህርት ቤት ዋና ኃላፊ ቀጥተኛ አለቃ መላክ አለበት።

ትምህርት ቤቱ የሚከተላቸው ማሳወቂያ መስፈርቶች የሚከተሉት ናቸው:-

ሀ. አካላዊ እገታ በተጠቀሙት ቁጥር፣ የተማሪውን ስም ጨምሮ፣ የተማሪ አገልግሎቶች ቢሮና የከፍተኛ ትምህርት ቤት ዋና ኃላፊ ቀጥተኛ አለቃ በጽሑፍ ማሳወቅ አስፈላጊ ነው።

ለ. አንድ የትምህርት ቤት ሠራተኛ አካላዊ እገታ በሚጠቀምበት ጊዜ ተማሪው ላይ ጉዳት ካስከተለ በተቻለ መጠን በፍጥነት እገታ የተደረገበት የትምህርት ቀን ሳይገባደድ የከፍተኛ ትምህርት ቤት ዋና ኃላፊውን ወይም ተወካዩን በቃል ማሳወቅ አለበት። የእገታውን መገምገሚያ የሚን በጽሑፍ የቀረበ ማሳወቂያ ለትምህርት ቤት ዋና ኃላፊው ተቆጣጣሪ እገታው ከተፈጸመ ቢበዛ ከአንድ ቀን ሳያልፍ መቅረብ አለበት። እገታውን የተጠቀመው የከፍተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ዋና ኃላፊ ከነ የከፍተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ዋና ኃላፊው ማሳወቂያውን አዘጋጅቶ ለተቆጣጣሪው ካስረከበ በኋላ ተቆጣጣሪው የሰየመው አንድ ቡድን ግምገማውን ያካሂዳል።

ሐ. የከፍተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ተቆጣጣሪ አካላዊ እገታ የተከሰተባቸውን ሁኔታዎች በሙሉ በመዝገብ ይይዛል።

መ. የከፍተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ዋና ኃላፊ ወይም ተወካይ እገታው ጥቅም ላይ በዋል በሃያ ዓራት (24) ሰዓት ውስጥ የተማሪውን ወላጆች/አሳዳጊዎች/ተንከባካቢዎች በተቻለ መጠን በፍጥነት በቃል ያሳውቃቸውና በሶስት (3) የትምህርት ቀን ውስጥ ደግሞ የጽሑፍ ደብዳቤ መላክ አለበት፡፡ የከፍተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ዋና ኃላፊው እገታውንና ማሳወቂያው ውስጥ ስለተጻፈው መረጃ ምላሽ ለመስጠጥ ለተማሪውና ለወላጆች/አሳዳጊዎች/ተንከባካቢዎች ዕድል ይሰጣል።

ሠ. አካላዊ እገታ ተማሪ ላይ ጉዳት በሚያስከትልበት ጊዜ የከፍተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ዋና ኃላፊ የጽሑፍ ማሳወቂያውን ግልባጭና አካላዊ ጉዳቱ ከመከሰቱ ከሰላሳ (30) ቀን በፊት ተከስተው የነበሩ ሌሎች ተመሳሳይ ጉዳዮች የያዘውን የትምህርት ቤቱን መዝገብ ግልባጭ ለOffice of the Superintendent (የዋና ተቆጣጣሪ ቢሮ) ያቀርባል። **ይህ ሰነድ ለዋና ተቆጣጣሪ ቢሮ መቅረብ ያለበት የጽሑፍ ማሳወቂያው የከፍተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ዋና ኃላፊው ጋር በደረሰ በአንድ (1) ቀን ውስጥ መን አለበት።** አንድ ተማሪ በሰባት (7) ዓመት ውስጥ ሁለት (2) የተለያየ ጊዜ ወይም በሰላሳ

(30) ቀን ውስጥ ሶስት (3) የተለያየ ጊዜ እገታ ከተደረገበት የከፈተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ዋና ኃላፊ ተማሪው የሚያስፈልገው ምን እንደነ ግምገማ የሚያደርግ የተማሪ ድጋፍ ቡድን ይሰበስባል። ግምገማው ላይ የክፍሉ ቡድን አባሎች እና ሌሎች የመርሃ ግብሩ ሠራተኞች መሳተፍ ካለባቸው የከፍተኛ ትምህርት ቤት ዋና ኃላፊ እንዳስፈላጊነቱ ይወስናል። እያንዳንዱ የተማሪ ድጋፍ ቡድን አባል በጽሑፍ የቀረቡትን የእገታ ማሳወቂያዎችና ተማሪውና ወላጆች/አሳዳጊዎች/ተንከባካቢዎች የሰጡትን ማንኛውንም አስተያየቶችና የእገታ አጠቃቀሙን በተመለከተ ያነባል። የተማሪ ድጋፍ ቡድኑ ግምገማውን ሲያደርግ እንደነዚህ ዓይነት ማሳወቂያዎችን ከመቃኘትና ከመወያየት በተጨማሪ እያንዳንዱን እገታ ያስከተለውን ሁኔታ፣ ሰዓቱን፣ ቀኑን፣ አስቀድሞ የተፈጠሩ ክስተቶችና የሚመለከታቸውን ግለሰቦች ያጤናል። ግምገማው ማገባደጃው ላይ ሁኔታዎች እንዲባባሱ ያደረጉ ነገሮች ካሉ ለእነሱ መፍትሄ በማቅረብ፣ ከእገታ ሌላ አማራጭ መጠቀም ይቻል እንደነ፣ ሁኔታዎችን ለማብረድ መጠቀም የሚችሉት መንገዶች ካሉና ወደፊት እገታን ላለመጠቀም የሚያስችሉ ሌሎች ስልቶችንና ውሳኔዎችን ያቀርባል። የከፍተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ኃላፊ የእገታው ተሳታፊ ከነበረ የተማሪ ድጋፍ ቡድን ውይይቱን የሚመራው ዋና ተቆጣጣሪው የሰየመው ብቃት ያለው ግለሰብ ይናል። የከፍተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ኃላፊ የተማሪ ድጋፍ ቡድኑ ያደረገው እያንዳንዱ ግምገማ በመዝገብ መቀመጡንና የ Massachusetts Department of Elementary and Secondary Education (የማሳቹሴትስ አንደኛና ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት መምሪያ) በጠየቀ ጊዜ ለማቅረብ ዝግጁ መን አለበት።

ረ. የከፍተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ኃላፊው ባጠቃላይ የትምህርት ቤቱን የእገታ አጠቃቀም መረጃ ወርሃዊ ቅኝት ያካሂዳል። ይህ ቅኝት በእገታዎች መካከል ያለውን ተመሳሳይነት ለምሳሌ የተከሰቱበትን ሰዓት፣ ቀን ወይም የሚመለከታቸውን ግለሰቦች፣ ባጠቃላይ በትምህርት ቤቱ ውስጥና በየተማሪው ላይ የተከሰቱት የእገታዎች ቁጥርና ርዝመት እንዲሁም ከእገታ የመጡ ጉዳቶች ካሉ ብዛታቸውንና ዓይነታቸውን ከግምት ያስገባ ይናል። የከፍተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ኃላፊው የትምህርት ቤቱ የእገታ መከላከያና አስተዳደር አሠራሮችና ሂደቶች ማሻሻል ያስፈልጋቸው ወይም ይገባቸው እንደነ፣ ለሠራተኞች ተጨማሪ የእገታ መቀነሻ/ማስወገጃ ሥልጠና ለምሳሌ አዎንታዊ የባሕርይ ማሻሻያና ድጋፍ ያስፈልግ እንደነና ሌሎች ተመሳሳይ እገታ መቀነሻ ወይም ማስወገጃ እርምጃም እንዳግባቡ ያስፈልግ እንደነ ይወስናል።

<u>የአውራጃው የሥልጠና መስፈርቶች</u>

ሀ. ለሁሉም መርሃ ግብር ሠራተኞች

የትምህርት ዓመቱ በተጀመረ በመጀመሪያው ወር ውስጥ የከፍተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ኃላፊው የእገታ ማስወገጃና የባሕርት ድጋፍ ሥልጠና፣ እገታ መጠቀም ሲያስፈልግ መስፈርቶቹ ምን እንደኑና ይህንን ፖሊሲ ለሁሉም የመርሃ ግብሩ ሠራተኞች ማቅረብ አለበት። በተጨማሪም ሁሉም ከትምህርት ዓመቱ መጀመሪያ በኋላ ለተቀጠሩ ሠራተኞች፣ በተቀጠሩ በመጀመሪያ ወር ውስጥ የከፍተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ኃላፊው በዚህ ፖሊሲ ላይ ሥልጠና ማቅረብ አለበት። ሥልጠናው የሚከተሉትን ያካተተ ይናል፡- (ሀ) ይህ ፖሊሲና የተያያዙ ዋና ተቆጣጣሪው ያጎለበታቸው ሂደቶችና መመሪያዎች፣ (ለ) እገታ ከማስፈለጉ በፊት መፍትሔዎች፣ ችግር ያላቸው ባሕርዮችን ማብረድና በድንገተኛ ሁኔታዎች ላይ ከእገታ ሌላ ሊጠቀሟቸው የሚችሏቸው አማራጮች፣ ከማግለል ሌላ ዓይነት ቅጣት መጠቀም ጨምሮ፣ (ሐ) ድንገተኛ እገታ የሚያስፈልገው ባሕርይ ሲኖር መጠቀም የሚችሏቸውን የእገታ ዓይነቶችና ተያያዥ የደህንነት መስፈርቶች፣ እገታ ሲጠቀሙ በተለይ የተወሰነ እገታን ለረጅም ጊዜ ሲጠቀሙ ተማሪ ላይ ጉዳት የመድረስ ዕድሉ እንደሚጨምር የሚገልጽ መረጃን ጨምሮ፣ (መ) የታወቀ የጤና ወይም የስነ ልቦና ችግር ያለበት ተማሪ ላይ አካላዊ እገታ መጠቀም እና/ወይም ለአንድ ተማሪ የግል የባሕርይ እርዳታ ዕቅዶች፣ የታወቀ ከፍተኛ ውጥረት በሕይወት ታሪኩ ላይ ሲኖር፣ እና (ሠ) እገታውን መጠቀም እንዳያስፈልግ ተማሪው፣ ሠራተኛውና ቤተሰብ ያላቸው ሚና፣ እና (ረ) በ603 C.M.R. 46.03(3) መሠረት አካላዊ እገታን ስለመጠቀም ጥልቀት ያለው ሥልጠና ያገኙ የመርሃ ግብር ሠራተኞችን ለይቶ ማወቅ። 603 C.M.R. 46.03(2)ን ይመልከቱ።

ለ. አካላዊ እገታዎችን ባግባቡ ስለመጠቀም በትምህርት ቤቱ ውስጥ ሁሉ ትክክለኛ መረጃ ለመስጠት ፈቃድ ላላቸው ሠራተኞች

የትምህርት ዓመቱ መጀመሪያ ላይ የእያንዳንዱ ትምህርት ቤት የከፍተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ኃላፊ አካላዊ እገታዎችን ባግባቡ ስለመጠቀም በትምህርት ቤቱ ውስጥ ሁሉ ትክክለኛ መረጃ ለመስጠት ፈቃድ ያላቸው ሠራተኞች እነማን እንደኑ ይለያል። ጥልቀት ያለው የሥልጠናው ይዘታ በብቃት ላይ የተመሠረተ ይንና ርዝመቱ ቢያንስ አሥራ ስድስት (16) ሰዓት ይናል። እነዚህ ግለሰቦች በሚቀጥሉት የትምህርት ዓመታት ውስጥ ርዝመቱ ከስምንት (8) ሰዓት ያላነሰ ቢያንስ አንድ የከለሳ ሥልጠና መውሰድ አለባቸው። ሥልጠናው ቢያንስ የሚከተሉትን ማካተት አለበት፡- (ሀ) አካላዊ እገታን ከመጠቀም ለመቆጠብ አግባብ ያላቸው ሂደቶች፣ ችግር ያለውን ባሕርይ ማብረድን ጨምሮ፣ ግንኙነት ማጎልበትና ከእገታ ይልቅ ሌሎች አማራጮችን መጠቀም፣ (ለ) ወደ አካላዊ እገታ ሊያመሩ የሚችሉ ተማሪ ላይ የሚታዩ ልዩ አደገኛ ባሕርዮችን መለየትና መግለጽ እንዲሁም እገታ መጠቀም አስፍላጊ መኑን ለማወቅ ክስተቶች ጉዳት የማስከተል ዕድላቸው ምን ያክል እንደነ ለመወሰን የሚያስችሉ ዘዴዎች፣ (ሐ) አካላዊ እገታን ሰው ላይ የመጠቀምና እራስ ላይ የማድረስ አስመስሎ ሙከራ፣ እገታ የሚደረግበት ሰው/ዎች ላይ ያለውን ተጽዕኖ በተመለከተ ትምህርት መስጠት፣ በእገታ ላይ ውጥረት መፈጠሩን በቅርብ መከታተልና የሕክምና እርዳታ ማግኘት፣ (መ) የመመዝገብና የማሳወቂያ መስፈርቶችን በተመለከተ ትምህርትና የጉዳቶችና የአቤቱታዎች ምርመራ፣ (ሠ) አካላዊ እገታ ተማሪውና ቤተሰቡ ላይ ያለውን ተጽዕኖ፣ እገታ ማድረግ አካላዊና ስነ ልቦናዊ ተጽዕኖ እንዳለው መገንዘብ፣ እና (ረ) ተሳታፊዎች አካላዊ እገታ የማድረግ ብቃት እንዳላቸው በተግባር ማሳየት። 603 C.M.R. 46.03(3) and 46.03(4)ን ይመልከቱ።

<u>አቤቱታ ማቅረቢያ ሂደቶች</u>

ሀ. አካላዊ እገታ አጠቃቀምን በተመለከተ ያለ ቅሬታን ኢፈሲዬላዊ ባልነ መንገድ መፍታት

ስለ አንድ እገታ አጠቃቀም ቅሬታ ያለው ተማሪ ወይም የተማሪው ወላጆች/አሳዳጊዎች/ተንከባካቢዎች መደበኛ *ሥርዓትን* ተከትለው አቤቱታ ከማስገባታቸው በፊት የከፍተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ዋና ኃላፊውን ተገናኝተው ችግሩን ለመፍታት መሞከር ይችላሉ። ወላጆች/አሳዳጊዎች/ተንከባካቢዎች ከላይ እንደተጠቀሰው የአካል እገታ እንደተከሰተ የሚገልጸው የጽሑፍ ማሳወቂያው በደረሳቸው በአሥር (10) ቀን ውስጥ ተማሪው ወይም የተማሪው ወላጆች/አሳዳጊዎች/ተንከባካቢዎች ያላቸውን ቅሬታ የከፍተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ዋና ኃላፊው ጋር ይዘው መቅረብ ይችላሉ። የከፍተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ዋና ኃላፊው የተሰጠው ሥልጣን እስከሚፈቅደው ድረስ አቤቱታውን ትክክለኛ በነ መንገድና በፍጥነት ለመፍታት ይሞክራል። ተማሪው እና/ወይም ወላጆች/አሳዳጊዎች/ተንከባካቢዎች መፍትሄውን አጥጋቢ ኖ ካላገኙት ወይም ተማሪው እና/ወይም ወላጆች/አሳዳጊዎች/ተንከባካቢዎች ኦፊሲዬላዊ ባልነ መንገድ ችግሩን መፍታት የማይፈልጉ ከነ፣ ተማሪው እና/ወይም ወላጆች/አሳዳጊዎች/ተንከባካቢዎች ከዚህ በታች በተገለጸው መደበኛ *ሥርዓት* መሠረት አቤቱታ ማስገባት ይችላሉ።

ለ. አካላዊ እገታ አጠቃቀምን በተመለከተ ያለ ቅሬታን መደበኛ ሥርዓት ተከትሎ መፍታት

ስለ አንድ እገታ አጠቃቀም ቅሬታ ያለው ተማሪ ወይም የተማሪው ወላጆች/አሳዳጊዎች/ተንከባካቢዎች Office of the Superintendent (የዋና ተቆጣጣሪ ቢሮ) ጋር በጽሑፍ አቤቱታ በማስገባት ቅሬታውን ለመፍታት መሞከር ይችላሉ። ተማሪው እና/ወይም የተማሪው ወላጆች/አሳዳጊዎች/ተንከባካቢዎች ከላይ እንደተጠቀሰው ከትምህርት ቤቱ የአካል እገታ እንደተከሰተ የሚገልጸው የጽሑፍ ማሳወቂያው በደረሳቸው በሃያ (20) ቀን ውስጥ ይህንን ደብዳቤ Office of the Superintendent ጋር ማስገባት አለባቸው። በጽሑፍ የቀረበው አቤቱቷ የሚከተሉትን መያዝ አለበት፦ (ሀ) የተማሪውን ስም፣ (ለ) አካላዊ እገታው ተከስቷል የተባለበትን ትምህርት ቤት ስም፣ (ሐ) አካላዊ እገታው ላይ የተሳተፉትን የግለሰቦች ስም፣ (መ) የአቤቱታው ምክንያት፣ (ሠ) የተፈለገው እርማት።

የዋና ተቆጣጣሪው ቢሮ አቤቱታው ከደረሰው በኋላ ወዲያውኑ በተወካዮቹ አማካኝነት አቤቱታውን በተመለከተ ምርመራ ያካሂዳል። በምርመራው ወቅት የዋና ተቆጣጣሪው ቢሮ እና/ወይም ተወካዮቹ አቤቱታውን በተመለከተ መረጃ አላቸው የተባሉትን ግለሰቦች ይገናኛል። እያንዳንዱ ክስተት ስለሚለያይ ምርመራውን ለማካሄድ ጥብቅ የኑ የጊዜ ገደቦች ማስቀመጥ አይቻልም። የዋና ተቆጣጣሪው ቢሮ እና/ወይም ተወካዮቹ አቤቱታው በተቻለ መጠን በፍጥነት መስተናገዱን ያረጋግጣሉ። የዋና ተቆጣጣሪ ቢሮ መደበኛ ምርመራውን ካጠናቀቀ በኋላ አቤቱታውን ያስገባውን ሰው ይገናኝና የምርመራውን ውጤትና የእርማት እርምጃ ያስፈልግ እንደነ የደረሰበትን ውሳኔ ያሳውቃል።

<u>ሌሎች አቤቱታ ማቅረቢያ ሂደቶች</u>

አንድ ተማሪ በሕግ በተጠበቁት ልዩ ምልክቶች ማለትም በዘር፣ ቀለም፣ ዜግነት፣ ዘር ማንዘር፣ ኃይማኖት፣ ዕድሜ፣ አካል ብቃት፣ የሥነ ዘር መረጃ፣ ውትድርና ውስጥ በፊት በማገልገል፣ የጋብቻ ሁኔታ፣ ጾታ፣ መታወቂያ ጾታ፣ የጓደኛ ጾታ ምርጫ፣ ነፍሰ ጡርነት፣ ወይም ከነፍሰ ጡርነት ጋር የተያያዘ ሁኔታ ላይ የተመሠረተ አቤቱታ ካለው የ CPS Non-Discrimination Policy and Prohibition Against Sexual Harassmentን (የኬምብሪጅ *መንግሥት ትምህርት ቤቶች "ጸረ-አድሎ ፖሊሲና የጾታ ጉትጎታ* ክልከላ") የአቤቱታ ሂደት ከመከተል እዚህ ክፍል ላይ የቀረቡት ደንቦች አያግዱትም። በተጨማሪም በዚህ *የመብቶችና ኃላፊነቶች መመሪያ* መሠረት የመብት መንፈግን በተመለከተ ያለ አቤቱታን ለመፍታት እዚህ ክፍል ላይ ያሉት አቅራቦቶች *የመብቶችና ኃላፊነቶች መመሪያው* ክፍል 23.0 ላይ ያለውን የአቤቱታ ሂደት ከመከተል አያግዱትም።

የምግባር ደንቦች (*ፖሊሲዎች*)

16. *መግቢያ*

እያንዳንዱ ትምህርት ቤት ተማሪዎች እንዲያከብሯቸው የሚጠበቅባቸው ትምህርት ቤት ላይ የተመሠረቱ ደንቦች ተብለው የሚታወቁ የራሱ ደንቦች አሉት። አንድ ተማሪ በትምህርት ቤት ላይ የተመሠረተ ደንብ ከጣሰ ቅጣት ሊደርስበት ይችላል። የትምህርት ቤት ደንቦች የተጻፉት እያንዳንዱ ትምህርት ቤት በሚገኙ አስተዳዳሪዎች፣ አስተማሪዎች፣ ወላጆች/አሳዳጊዎች/ተንከባካቢዎችና የአንደኛ ደረጃ ተማሪዎች የተውጣጣ ኮሚቴ ሲን ሁልጊዜ ጸደይ ላይ ድጋሚ ይቃኛል። የትምህርት ቤት ደንቦች በየክፍሉ ተለጥፈው ይገኛሉ፣ በየሴፕቴምበር ወር ላይም በተማሪዎች በኩል ወደቤት ይላካሉ። የራሱን ደንቦች ከመከተል በተጨማሪ፣ እያንዳንዱ ትምህርት ቤት *በመብቶችና ኃላፊነቶች መመሪያ* ውስጥ ያሉትን የምግባር ደንቦች መከተል አለበት። *የመብቶችና ኃላፊነቶች መመሪያ* ተማሪዎች እንዲከተሉ የሚጠበቅባቸውን ደንቦች ሁሉ ይዘረዝራል። እነዚህን ደንቦች የሚጥስ ተማሪ ከትምህርት ቤት ለጊዜው እንዲወጣ ሊደረግ ወይም ሊባረር ይችላል። የትምህርት ቤት ደንቦችና *የመብቶችና ኃላፊነቶች መመሪያ* ውስጥ ያሉ ደንቦች በትምህርት ቤት ውስጥ፣ በትምህርት ቤት ድጋፍ የተዘጋጀ ዝግጅት ላይ እንዲሁም ወደ ትምህርት ቤት በሚሄዱበትና ከትምህርት ቤት በሚመለሱበት ጊዜ መከበር አለባቸው።

የመብቶችና ኃላፊነቶች መመሪያ ደንቦች ባጭሩ ከዚህ በታች ይገኛል። ልጅዎ የሚሄድበት/የምትሄድበት የትምህርት ቤት ደንቦች ቅጂን ከተቆጣጣሪው/ከከፈተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ዋና ኃላፊ ማግኘት ይችላሉ። እንዲሁም *የመብቶችና ኃላፊነቶች መመሪያ* ቅጂን ከትምህርት ቤቱ ተቆጣጣሪ/ከፈተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ዋና ኃላፊ ማግኘት ይችላሉ። የትምህርት ቤት አውራጃው ድህረ ገጽ ላይም ተለጥፎ ይገኛል።

በተጨማሪም የ CPS የተለያዩ ፖሊሲዎች አጭር መግለጫና ጸረ አድሎ ፖሊሲዎች ከዚህ በታች ይገኛሉ። እነዚህን ፖሊሲዎች የሚጥሱ ሠራተኞች ወይም ተማሪዎች ቅጣት ሊደርስባቸው ይችላል። የነዚህን ፖሊሲዎች ሙሉ ቅጂ ለማግኘት ተቆጣጣሪውን/የከፈተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ዋና ኃላፊውን ይጠይቁ።

17. ፍልስፍና

የኬምብሪጅ ትምህርት ቤት ኮሚቴ የቅጣት ፖሊሲዎች ሁሉም የትምህርት ቤት ሠራተኞች ተማሪዎች ላይ ከፍተኛ የቅጣት እርምጃ ከመውሰዳቸው በፊት የምግባር ችግሮችን ለመፍታት እንዲሞክሩ ይገፋፋሉ። ተማሪ የተሳሳተ ሥነ ምግባር ሲያሳይ ከሥር ከትምህርት ቤቱ ጋር ወይም ከሕብረተሰቡ ጋር ይበልጥ የተወሳሰቡ ችግሮች ስላሉት ሊን ስለሚችል የአንደኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች ተማሪዎቹንና ወላጆቻቸውን ወይም አሳዳጊዎቻቸውን ለመርዳትና

ችግሩን ለመቅረፍ የተቻላቸውን ሁሉ ማደረግ አለባቸው። ለጊዜው ከትምህርት ቤት ማስወጣትና እስከመጨረሻው ማባረር የመጨረሻ መፍትሄዎች መን አለባቸው። ተማሪን ከማባረር በፊት የትምህርት ቤት ሠራተኞች የተማሪውን ትምህርትና ጥሩ ምግባር ለማበረታታት ሌሎች አግባብ ያላቸውን አማራጮችና ቅጣቶች ሁሉ መጀመሪያ መሞከር አለባቸው።

ትምህርት ቤቶች ችግር ላይ የመውደቅ ዕድል ካለው ተማሪ ጋር አንድ ላንድ ለመሥራትና የችግሩን ምንጭ አግኝቶ አማራጭ ለማቅረብ መሞከር አለባቸው። አልፎ አልፎ ከወላጅ/አሳዳጊ/ተንከባካቢ ጋር ስብሰባ ማድረግ ወይም በቤቱ ሄዶ መጎብኘት አስፈላጊ ሊን ይችላል። ስኬታማ ለመን በቤትና በትምህርት ቤት መካከል ያለው ግንኙነት ወሳኝ ነው። የትምህርት ቤት አማካሪዎችና የስነ ልቦና ባለሙያዎች ሐሳብ ለመስጠትና መፍትሄ ለማግኘት ጠቃሚ ናቸው። የእኩዮች ሽምግልና፥ የአስተማሪ መካሪ፥ Big Brothers and Sisters (ታላላቅ ወንድሞችና እህቶች)ም ጠቃሚ ምንጮች ናቸው። ኬምብሪጅ የተቸገሩ ተማሪዎችን የሚረዱ የማህበራዊ ጉልበታ ቡድኖች ስላሉት በጣም ዕድለኛ ነው። የእነዚህ ቡድኖች አንዳንድ ምሳሌዎች እንደሚከተሉት ናቸው፡- Student Support Teams (SSTs) (የተማሪ ድጋፍ ቡድኖች)፥ Teacher Assistance Teams (TATs) (የአስተማሪ እርዳታ ቡድኖች)፥ እና Administrative Response Teams (ARTs) (አስተዳደራዊ መልስ ሰጪ ቡድኖች)። የማህበረሰብ ድርጅቶች ከፍተኛ ዋጋ ያላቸው የድጋፍ አገልግሎቶች መስጠት ላይ ወሳኝ አጋሮች ናቸው። እነዚህ ድርጅቶች ለትምህርት ቤት ቡድኖች ጠቃሚ ምክር የሚሰጡና ከተማሪዎች ጋር በግል ወይም በቡድን አብረው ይሠራሉ። እንደነዚህ ዓይነት መከላከያ አገልግሎቶች አግባብ የሌለውን ባሕርይ ለማስወገድና መባረርን ለመከላከል፥ ከዛም አልፎ ትምህርት አቋርጠው እንዳይወጡ ይረዳሉ።

ባሕርይና የቅጣት ፖሊሲዎች

18. ማጨስ፡- ከትምባ ነጻ የመን ፖሊሲ

የማሳቹሴትስ አጠቃላይ ሕጎች፥ አንቀጽ 71፥ ክፍል 37H እንደሚለው በትምህርት ቤት ሕንጻዎች ውስጥ፣ በትምህርት ቤት መገልገያዎች ላይ፣ በትምርህት ቤት ቅጥር ግቢ ውስጥ ወይም በትምህርት ቤት አውቶቡሶች ላይ ማንም ሰው፣ የትምህርት ቤት ሠራተኞችን ጨምሮ ትምባ መጠቀም አይችልም። ፖሊሲው የሚመለከተው ሁሉን በትምህርት ቤት ድጋፍ እና/ወይም ከትምህርት ቤት ጋር የተያያዙ ዝግጅቶችንና የስፖርት ጨዋታዎችን ነው። እነዚህን ሕጎች የሚተላለፉ ሠራተኞችና ተማሪዎች ቅጣት ይደርስባቸዋል። ማንኛውም ሠራተኛ በትምህርት ቤት ቅጥር ግቢ ውስጥ አንድ ተማሪ ሲያጨስ ካየ፥ የተማሪውን ስም ጠይቆ በትምህርት ቤት ውስጥ ማጨስ የተከለከለ መኑን መንገር አለበት። የተማሪው ስም ለተቆጣጣሪው/የከፈተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ዋና ኃላፊ ወይም ለረዳት ተቆጣጣሪ ይሰጥና እሱም በተራው ለትምህርት ቤት ነርስና ለወላጅ ወይም ለአሳዳጊ ያሳውቃል። Tobacco Assistance Program (TAP) (የትምባ እርዳታ መርሃ ግብር) በመንግሥት ትምህርት ቤቶቻችን የሚገኝ ሲን የትምባ ሱስ መተው የሚፈልጉትን ይረዳል።

19. የዕጾች፥ የመሣሪያና የትምህርት ቤት ሠራተኞች ድብደባ ሕጋዊ ክልከላ

የማሳቹሴትስ አጠቃላይ ሕጎች አንቀጽ 71፥ ክፍል 37H የሚከተሉትን አቅራቦቶች ይዟል፡-

(ሀ) ማንኛውም በትምህርት ቤት ቅጥር ግቢ ውስጥ፣ በትምህርት ቤት ድጋፍ ወይም ከትምህርት ቤት ጋር በተያያዘ ዝግጅት ላይ፣ የስፖርት ዝግጅትንም ጨምሮ አደገኛ መሳሪያ ወይም በ Chapter ዘጠና አራት C ሥር በተሰጠው ፍቺ መሠረት በቁጥጥር ሥር ያለ ዕጽ፣ አልኮል፣ ማሪዋና፣ ኮኬይን፣ ኦፒኦይድስና ሄሮይንን ጨምሮ ይዞ የተገኘ ተማሪ፣ የከፍተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ዋና ኃላፊው ከትምህርት ቤቱ ወይም ከትምህርት ቤት አውራጃው ሊያባርረው ይችላል።

(ለ) በተጨማሪም ማንኛውም የከፍተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ዋና ኃላፊውን፣ ረዳት ተቆጣጣሪውን፣ አስተማሪውን፣ ወይም ሌላ የትምህርት ቤት ሠራተኛ በትምህርት ቤት ቅጥር ግቢ ውስጥ፡ ወይም ሌሎች ከትምህርት ቤት ጋር የተያያዙ ዝግጅቶች ላይ የስፖርት ዝግጅቶችን ጨምሮ፣ የሚደበድብ ተማሪን የከፍተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ዋና ኃላፊው ከትምህርት ቤቱ ወይም ከትምህርት ቤት አውራጃው ሊያባርረው ይችላል።

(ሐ) ማንኛውም በአንቀጽ (ሀ) ወይም በአንቀጽ (ለ) ጥሰት የተከሰሰ ተማሪ የይግባኝ ዕድል እንደሚኖረው በጽሑፍ ይነገረዋል፥ ኖም ተማሪው ውክልና ካለውና ተቆጣጣሪ/የከፍተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ዋና ኃላፊ ፊት ማስረጃና ምስክሮች የማቅረብ ዕድል ይኖረዋል።

ይግባኙ ከተካሄደ በኋላ ተቆጣጣሪው/የከፍተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ዋና ኃላፊው አንቀጽ (ሀ)ን ወይም (ለ)ን የተላለፈን ተማሪ ከማባረር ይልቅ ለጊዜው ሊያስወጣው ይችላል።

(መ) ማንኛውም በነዚህ አቅራቦቶች ምክንያት ከትምህርት ቤት አውራጃ የተባረረ ተማሪ ዋና ተቆጣጣሪው ጋር ይግባኝ የማለት መብት አለው። የተባረረው ተማሪ ከተባረረበት ቀን ጀምሮ ዋና ተቆጣጣሪውን ይግባኝ እንደሚል ለማዋወቅ አሥር ቀን ይኖረዋል። ተማሪው ዋና ተቆጣጣሪው ፊት ሲቀርብ ጠበቃ የመያዝ መብት አለው። የይግባኙ ርእስ ተማሪው የዚህን ክፍል አቅራቦቶች መጣሱን በጭብጥ ጉዳዮች ላይ የተመሠረተ ግምገማ ላይ ብቻ የተወሰነ አይንም።

(ሠ) አንድ ተማሪ እዚህ ክፍል ውስጥ ባሉት አቅራቦቶች መሠረት ከነ የተባረረው በኮመንዌልዝ ውስጥ ያለ ማንኛውም ሌላ ትምህርት ቤት ወይም የትምህርት ቤት አውራጃ ተማሪውን የመቀበል ወይም ትምህርታዊ አገልግሎቶች ለተማሪው የመስጠት ግዴታ አይኖርበትም። ተማሪው ሌላ ትምህርት ቤት ወይም ሌላ የትምህርት ቤት አውራጃ ጋር ማመልከቻ ካስገባ የትምህርት ቤት አውራጃው ዋና ተቆጣጣሪ ከአባራሪው ትምህርት ቤት ዋና ተቆጣጣሪ ተማሪው የተባረረበትን ምክንያቶች በጽሑፍ መጠየቅ ይችላል።

20. የዕጽ ፖሊሲ

አንድ ተማሪ የዕጽ ፖሊሲ ተላልፏል የሚባለው በትምህርት ቤት ቅጥር ግቢ ውስጥ፣ በአውቶቡስ ላይ፥ በትምህርት ቤት ድጋፍ ወይም ከትምህርት ቤት ጋር በተያያዘ ዝግጅት ላይ፣ የስፖርት ዝግጅትንም ጨምሮ በ Chapter 94C ሥር በተሰጠው ፍቺ መሠረት በቁጥጥር ሥር ያለ ዕጽ ተይዞ ከተገኘ ነው፥ ይህ ማሪዋናን፥ ኮኬይንን ወይም ሄሮይንንም ይጨምራል። ይህ ከነ ተቆጣጣሪው/የከፍተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ዋና ኃላፊው ተማሪዎን ሊያባርረው ይችላል።

21. የመሣሪያዎች ፖሊሲ

አንድ ተማሪ የመሣሪያ ፖሊሲ ተላልፏል የሚባለው፡- ትምህርት ቤት መሣሪያ ይዞ ከመጣ፣ በትምህርት ቤት ውስጥ ወይም የትምህርት ቤት እንቅስቃሴ ላይ መሣሪያ ከተጠቀመ ወይም ዕቃ ማስቀመጫ ሳጥን ውስጥ፣ ኪስ ውስጥ፣ በትምህርት ቤት ሳሉ፣ በአውቶቡስ ላይ ወይም ከትምህርት ሰዓት ውጪ የሚደረግ እንቅስቃሴ ላይ መሣሪያ ይዞ ከመጣ ነው።

በሕግ አደገኛ የኑ መሣሪያዎች ሌላ ሰውን ለማስፈራራት ወይም ለመጉዳት የሚጠቀሟቸው ማናቸውም ሕገወጥ መሣሪያዎች አደገኛ መሣሪያ ይባላሉ። እንደነዚህ ዓይነት መሣሪያዎች የሚከተሉትን ያካትታሉ፡-

- ማንኛውም ዓይነት የጦር መሣሪያዎች፣ ጠብ መንጃን ጨምሮ፣
- ባለ ሁለት ስለት ጩቤ፣ ሰንጢ ወይም ምንም ዓይነት አውቶማቲክ ስፕሪንግ ያለው እጀታውን በመጫን የሚዘረጋ ቢላዋ፣
- የጣት መጋጠሚያ ብረት፣ ወይም ሌላ ማንኛውም ዓይነት ተወርዋሪ ወይም ሹል ኮከብ በሳይ ሰው መጉጃ ብረታብረት፣
- አጭር ዱላ፣ ቀስት ማስፈንጠሪያ ቱቦ ዱላ፣
- ከቆዳ የተሠራና ሹል ብረቶች ያሉት እጅ ላይ የሚታሠር ነገር፣ ምንም ዓይነት ተመሳሳይ በሌላ ነገር የተሠራ መሳሪያ፣
- ፊት ላይ መርጫ መሳሪያ፣ አስለቃሽ ጋዝ ወይም ሌላ ማንኛውም ሰውን አቅም ማሳጫ መሳሪያ፣
- ርችት ወይም ምንም ዓይነት ፈንጂ፣
- ማናቸውም በ Massachusetts General Laws (የማሳቹሴትስ አጠቃላይ ሕጎች) አንቀጽ 269፣ ክፍል 10 ውስጥ የተጠቀሱ መሳሪያዎች።

ሌሎች የተከለከሉ በ Massachusetts General Laws (የማሳቹሴትስ አጠቃላይ ሕጎች) አንቀጽ 269፣ ክፍል 10 ውስጥ መሳሪያ ተብለው ባይጠቀሱም በትምህርት ቤት ቅጥር ግቢ ውስጥ፣ በትምህርት ቤት ድጋፍ የተዘጋጁ ዝግጅቶች ላይ እና/ወይም ከትምህርት ቤት ጋር የተያያዙ ዝግጅቶች ላይ፣ የስፖርት ዝግጅቶችን ጨምሮ ማምጣት ክልክል ነው። እነዚህን ክልክል የኑ ቁሳቁሶች መጠቀም ከትምህርት ቤት ማባረርን ሊያስከትሉ ይችላሉ። እነሱም የሚከተሉትን ያካትታሉ፡-

- ምንም ዓይነት ረጅምም ነ አጭር ቢላዋዎች፣ የቁልፍ ማንጠልጠያ ሰንጢዎችና መቅረጫ ቢላዋን ጨምሮ፣
- ምንም ዓይነት ርዝመት ያለው ስለት፣
- ምላጮች፣ ካርቶን መቁረጫዎች፣ እና
- ሰንሰለቶች፣ ጅራፎች ወይም ሌላ ለትምህርት ምንም ጥቅም የሌለው የብረት መሣሪያ።

በአደገኛ መንገድ ከተጠቀሟቸው ከትምህርት ቤት ለጊዜው ወይም እስከመጨረሻው ለመባረር የሚዳርጉ ሌሎች ተራ ቁሳቁሶችም አሉ። እነሱም የሚከተሉትን ያካትታሉ፡-

- እርሳሶች፥ መቀሶች፥ መርፌዎችና ስፒሎች፥ ሚስማሮች፥ የእንጨት ሥራ መሣሪያዎች፥ ወዘተ
- በተጨማሪ የአንድ ግለሰብን ጤናና ደህንነት አደጋ ላይ የሚጥል አግባብ የሌለው አደገኛ የስፖርት ቴክኒክ መጠቀም፣ ለምሳሌ የራስ ቁርን ወይም ሌላ የስፖርት መሳሪያን እንደ አጥቂ መሳሪያ መጠቀም።

ልብ ይበሉ፡- በትምህርት ቤት ቅጥር ግቢ ውስጥ፣ በትምህርት ቤት ድጋፍ ወይም ከትምህርት ቤት ጋር በተያያዘ ዝግጅት ላይ፣ የስፖርት ዝግጅትንም ጨምሮ ዓይነት የመጫወቻም ነ ኮፒ መሣሪያ፥ ሽጉጥንና ቢላዋን ጨምሮ፥ ይዞ መምጣት የተከለከለ ነው። እንደነዚህ ዓይነት መሣሪያዎች ይወሰዱና ተቆጣጣሪው/የከፍተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ዋና ኃላፊው ይህን ፖሊሲ ጥሷል ብለው ከደመደሙ ተማሪው ለጊዜው እንዲወጣ ሊደረግ ወይም ከትምህርት ቤት ሊባረር ይችላል።

22. የሠራተኛ ድብደባ

ማንኛውም በትምህርት ቤት ቅጥር ግቢ ውስጥ፥ በትምህርት ቤት ድጋፍ ወይም ከትምህርት ቤት ጋር በተያያዘ ዝግጅት ላይ፣ የስፖርት ዝግጅት ላይም ጨምሮ ተቆጣጣሪውን/የከፈተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ዋና ኃላፊውን፥ ረዳት ተቆጣጣሪውን፥ አስተማሪን፥ የአስተማሪ ረዳትን ወይም ሌላ የትምህርት ቤት ሠራተኛን የደበደበን ተማሪ ተቆጣጣሪው/የከፈተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ዋና ኃላፊው ሊያባርረው ይችላል። አንድ ተማሪ የሚከተሉትን ካደረገ ድብደባ ተብሎ ይቆጠራል፡-

- ን ብሎ፥ እያወቀ ወይም በግድ የለሽነት ሌላ ሰው ላይ አካላዊ ጉዳት ማድረስ፥
- ን ብሎ ወይም እያወቀ ሌላን ሰው በአካል እጎዳለሁ ብሎ ማስፈራራት፥ ወይም
- ን ብሎ ወይም እያወቀ ሌላን አካላዊ ኃይል እጠቀማለሁ ብሎ ማስፈራራት ወይም መጠቀምና ካላስቆሙት የሚቀጥል ዓይነት ከነ።

23. በከፍተኛ ወንጀል የተከሰሱ ወይም የተፈረደባቸው ተማሪዎች

እንዲሁም አንድ ተማሪ በከፍተኛ ወንጀል ከተከሰሰና በትምህርት ቤት ውስጥ መቆየቱ ለትምህርት ቤቱ አጠቃላይ ደህንነት አስጊ ነው ብሎ ከተደመደመ፥ ጉዳዩ በፍርድ ቤት ውሳኔ እስከሚሰጠው ድረስ ተማሪው ከትምህርት ቤት ሌጊዜው እንዲወጣ ሊደረግ ይችላል። ተማሪው ከተፈረደበትና በትምህርት ቤት ውስጥ መቆየቱ ለትምህርት ቤቱ አጠቃላይ ደህንነት አስጊ ነው ብሎ ተቆጣጣሪው/የከፍተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ዋና ኃላፊው ከደመደመ እስከመጨረሻው ሊያባርረው ይችላል።

የከፍተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ዋና ኃላፊው ተማሪውንና ወላጆች/አሳዳጊዎች/ተንከባካቢዎችን ትምህርት ቤት ውስጥ ይግባኝ እንደሚደረግ ያሳውቃቸዋል። በሁለቱም ሁኔታ ቅጣቱ ከመሰጠቱ በፊት ተማሪውና ወላጅ/አሳዳጊ/ተንከባካቢ ክሱንና የቅጣቱን ምክንያቶች የሚያብራራ ደብዳቤ በጽሑፍ ይደርሳቸውና የይግባኝ ዕድል ይሰጣቸዋል። ቅጣት ከተሰጠ ተማሪው ይግባኝ የማለት መብት እንዳለውና የይግባኙን ሂደት የሚገልጽ የጽሑፍ ማስታወቂያ ይሰጠዋል፥ ኖም ዋና ተቆጣጣሪው ወይም ተወካዩ ምንም ዓይነት ይግባኝ እስከሚያካሂድ ድረስ ቅጣቱ እንዳለ ይቆያል።

24. የማዋረጃ እንቅስቃሴ

የማዋረጃ እንቅስቃሴ ማለት ማንኛውም ዓይነት የተማሪ ክፍል ወይም ቡድን ውስጥ መግቢያ የተማሪን አካላዊ ወይም የአእምሮ ጤንነት አውቆ ወይም በግድየለሽነት አደጋ ላይ የሚጥል በትምህርት ቤት ውስጥ ወይም በግል ቦታ ላይ የሚከሰት ምግባር ወይም ሁኔታ ማለት ነው። ሁሉም የሁለተኛ ደረጃ ተማሪዎች ከማሳቹሴትስ አንደኛና ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት መምሪያ የሚመጣ የማዋረጃ እንቅስቃሴዎችን በተመለከተ መግለጫ የመፈረም ግዴታ አለባቸው።

የማዋረጃ እንቅስቃሴ ማድረግ የትምህርት ቤት ፖሊሲን መጣስ ነው። የማዋረጃ እንቅስቃሴ ውስጥ የሚሳተፉ ተማሪዎች ለጊዜው ከትምህርት ቤት እንዲወጡ ሊደረጉ ይችላሉ። ወንጀላዊ አቤቱታ ይገባል። ይህን የሚመለከት መረጃ ለተማሪዎች ሁሉ ትምህርት ቤት ሲከፈት ይሰራጫል። *የማሳቹሴትስ አጠቃላይ ሕጎች አንቀጽ 269፥ ክፍል 17*

የማዋረጃ እንቅስቃሴ ወንጀል፥ ፍቺ፥ ቅጣት

በዚህ ውስጥ በተሰጠው ፍቺ ውስጥ የማዋረጃ እንቅስቃሴ ወንጀል ላይ ዋና አዘጋጅ ወይም ተሳታፊ የነ ሰው ከሶስት ሺህ ዶላር የማይበልጥ ቅጣት ወይም ማረሚያ ቤት ውስጥ እስከ አንድ ዓመት ደርስ እሥራት ወይም በሁለቱም መቀጮም እሥራትም ይቀጣል።

የማዋረጃ እንቅስቃሴ ማለት በዚህ ክፍል ውስጥ በምንጠቀመው መሠረትና በክፍሎች አሥራ ስምንትና አሥራ ዘጠኝ ውስጥ በተሰጠው ፍቺ መሠረት ማንኛውም ዓይነት የተማሪ ክፍል ወይም ቡድን ውስጥ መግቢያ የተማሪን አካላዊ ወይም የአእምሮ ጤንነት አውቆ ወይም በግድየለሽነት አደጋ ላይ የሚጥል በትምህርት ቤት ውስጥ ወይም በግል ቦታ ላይ የሚከሰት ምግባር ወይም ሁኔታ ማለት ነው። ይህም ግርፊያን፥ ድብደባን፥ በጋለ ብረት ምልክት ማድረግን፥ በግድ ስፖርት ማሠራትን፥ የተለያየ አየር ሁኔታ ላይ ማስወጣትን፥ ምንም ዓይነት ምግብ፥ መጠጥ፥ ዕጽን በግድ ማስወሰድን ወይም ሌላ ማንኛውንም ዓይነት ጨካኝ አያያዝን ወይም ጤናን ወይም ደህንነትን ሊጎዳ የሚችል የግዳጅ አካላዊ እንቅስቃሴ ወይም ማንኛውንም ተማሪ ወይም ሰው ለከፍተኛ የአእምሮ ጭንቀት የሚዳርግ፥ እንቅልፍ ወይም እረፍት የሚያሳጣ ወይም ለረጅም ጊዜ ለብቻ የሚያስደርግ እንቅስቃሴዎችን ያካትታል።

እዚህ ክፍል ውስጥ ያሉት አቅራቦቶች ተቃራኒው ቢንም በዚህ ድርጊት ላይ ስምምነት ነበር ብሎ መከራከር አይቻልም።

በ St. 1985፥ c. 536 የተጨመረ፥ በ1987, c. 665 የተሻሻለ። ማሳቹሴትስ አጠቃላይ ሕጎች አንቀጽ 269፥ ክፍል 18

የማዋረጃ እንቅስቃሴን የማሳወቅ ግዴታ

ማንኛውም አንድ ሰው በክፍል አሥራ ሰባት ውስጥ ባለው ፍቺ መሠረት የማዋረጃ እንቅስቃሴ ተጠቂ እንደነበረ የሚያቅና ወንጀሉ ሲፈጸም በቦታው የነበረ ሰው፥ እራሱን ወይም ሌሎችን አደጋ ላይ እስካልጣለ ድረስ በተቻለ መጠን በፍጥነት ለተገቢው ሕግ አስከባሪ አካል ማሳወቅ አለበት። እንደዚህ ዓይነት ወንጀል ያላሳወቀ ሰው ከአንድ ሺህ ዶላር ያልበለጠ የገንዘብ መቀጮ ይደርስበታል።

በ St. 1985፥ c. 536 የተጨመረ፥ በ1987, c. 665 የተሻሻለ። ማሳቹሴትስ አጠቃላይ ሕጎች አንቀጽ 269፥ ክፍል 19

ለተማሪ ቡድኖች የሚቀርቡ ደንቦች፥ የማክበሪያ መግለጫና አስፈላጊ የቅጣት ፖሊሲ

እያንዳንዱ የሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ተቋምና ከሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ባሻገር ያለ እያንዳንዱ የመንግሥትና የግል ተቋም ለሁሉም የተማሪ ቡድን፥ የተማሪ Team ወይም የተቋሙ የነ ወይም በተቋሙ እውቅና ያለው ወይም ተቋሙ ስሙን ወይም ቦታውን እንዲጠቀም ፈቃድ የሰጠው ወይም በራሱ የቆመ የተማሪ ቡድን፥ የተማሪ Team ወይም የተማሪ ድርጅት የዚህ ክፍል ቅጂና የክፍሎች አሥራ ሰባትና አሥራ ስምንት ቅጂ ይደርሰዋል፥ ኖም አንድ ተቋም የዚህ ክፍልንና የክፍሎች አሥራ ሰባትና አሥራ ስምንት ቅጂዎችን በራሳቸው ለቆሙ የተማሪ ቡድኖች፥ Teams ወይም ድርጅቶች የመስጠት የዚህ ክፍል መስፈርቶችን አከበረ ማለት ተቋሙ እውቅና ሰጣቸው ማለት አይደለም።

እያንዳንዱ እንደዚህ ዓይነት ቡድን፥ Team ወይም ድርጅት ለእያንዳንዱ አባሉ፥ ቃል ገቢ፥ አዲስ ገቢ ወይም ለአባልነት ማመልከቻ አስገቢ የዚህን ክፍል ቅጂና የክፍሎች አሥራ ሰባትና አሥራ ስምንት ቅጂዎችን ይሰጣል። እያንዳንዱ እንደዚህ ዓይነት ቡድን፥ Team ወይም ድርጅት ለእያንዳንዱ አባሉ፥ ቃል ገቢ፥ አዲስ ገቢ ወይም ለአባልነት ማመልከቻ አስገቢ የዚህን ክፍል ቅጂና የክፍሎች አሥራ ሰባትና አሥራ ስምንት ቅጂዎችን እንደሰጠና እንደዚህ ዓይነት ቡድኑ፥ Team ወይም ድርጅት የዚህ ክልና የክፍሎች አሥራ ሰባትና አሥራ ስምንት አቅራቦቶች እንደሚገባውና እንደሚስማማ በሹሙ በኩል በየዓመቱ ባለ ማረጋገጫ መግለጫ መላክ አለበት።

እያንዳንዱ የሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ተቋምና ከሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ባሻገር ያለ እያንዳንዱ የመንግሥትና የግል ተቋም ቢያንስ በየዓመቱ ምዝገባ ከመጀመሩ በፊት ወይም ምዝገባ በሚጀመርበት ጊዜ በተቋሙ ውስጥ ሙሉ ጊዜ ለሚመዘገብ ተማሪ ሁሉ የዚህን ክፍል ቅጂና የክፍሎች አሥራ ሰባትና አሥራ ስምንት ቅጂዎችን ይሰጣል።

እያንዳንዱ የሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ተቋምና ከሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ባሻገር ያለ እያንዳንዱ የመንግሥትና የግል ተቋም ቢያንስ በየዓመቱ ከፍተኛ ደረጃ ትምህርት ቦርድ ጋር ዘገባ ማስገባት አለበት፥ የሁለተኛ ደረጃ ተቋሞች ደግሞ ተቋሙ የተማሪ ቡድኖችን፥ Teamsን ወይም ድርጅቶችን የማሳወቅ ግዴታውን እንደተወጣ ያረጋገጠው የትምህርት ቦርድ ጋር ማስገባት አለባቸው፥ እንዲሁም እያንዳንዱን ሙሉ ጊዜ የተመዘገበ ተማሪ የዚህን ክፍልና የክፍሎች አሥራ ሰባትና አሥራ ስምንት አቅራቦቶች ማሳወቅና የማዋረጃ እንቅስቃሴ አዘጋጅና ተሳታፊዎች ላይ የቅጣት ፖሊሲ እንዳለው፥ ይህም ፖሊሲ የተማሪዎች መመሪያ ውስጥ እንዳለ ማሳወቅ አለበት። የከፍተኛ ደረጃ ትምህርት ቦርድና ለሁለተኛ ደረጃ ተቋሞች የትምህርት ቦርዱ፥ የነዚህን ዘገባዎች ይዘትና ድግግሞሽ ደንቦች ያውጃል፥ ዘገባውን ሳያደርግ የሚቀርንም ተቋም ለአጠቃላይ ጠበቃ ዘገባ በማድረግ ያሳውቃል።

በ St. 1985፥ c. 536 የተጨመረ፥ በ1987, c. 665፥ St. 1998, c. 161፥ ss. 557፥ 558 የተሻሻለ።

25. አውዳሚነት

የትምህርት ቤት ንብረት ላይ ማንም ሰው መጉዳት፥ ማጥፋት፥ ማበላሸት ወይም መተላለፍ አይችልም። ሁሉም ተማሪዎችና ሠራተኞች የትምህርት ቤት ሕንጻዎችን በጥንቃቄና በአክብሮት እንዲይዙ ይጠየቃሉ። ልጃቸው ሕንጻ ላይ ላደረሰው ጉዳት ወላጆች/አሳዳጊዎች/ተንከባካቢዎች የመክፈል ኃላፊነት ይኖርባቸዋል። የትምህርት ቤት መምሪያው ወላጆች/አሳዳጊዎች/ተንከባካቢዎችን ፍርድ ቤት ይወስዳል። ስለ ሕንጻ ወይም ስለ ይዘቱ ጉዳት ምንም ዓይነት መረጃ ያላቸው ሰዎች ለደህንነትና ጥበቃ ቢሮ ማሳወቅ አለባቸው። ትምህርት ቤት አካባቢ አላግባብ መጻፍ ወይም መርጨት - ግራፊቲ፥ ጠረጴዛ ላይ መቅረጽ፥ መጽሐፍ ማበላሸት፥ መስኮት መስበር፥ መጫሪያ ማበላሸት ወይም ቁሳቁሶች መጉዳት የትምህርት ቤት ማህበረሰብ ንጹህ

አካባቢ እንዳይኖረው መብትን መተላለፍ ነው። ተማሪዎች ሲያወድሙ ወላጆች/አሳዳጊዎች/ተንከባካቢዎች ኃላፊነቱን ይወስዳሉ።

26. መደባደብ/አካላዊ ጥቃት

ድብድብ ውስጥ የሚሳተፉ ወይም ድብድብ የሚያበረታቱ ግለሰቦች ከፍተኛ፥ አስቸኳይ የቅጣት እርምጃ ይወሰድባቸዋል። እንደዚህ ዓይነት የረብሻ ባሕርይ በምንም ዓይነት ተቀባይነት አይኖረውም። የእንደዚህ ዓይነት ባሕርይ ቅጣት እንደ ተሳተፎው ጥልቀት፥ የጥፋት ቁጥሮች እና/ወይም እንደ ክስተቱ ከፍተኛነት ከአንድ ቀን መባረር እስከ አሥር ቀን ሊን ይችላል። ሰው ላይ ድብደባ መፈጸም ወንጀል እንደነና አካላዊ ድብደባዎች ሁሉ ለፖሊስ እንደሚነገሩና ወላጆች/አሳዳጊዎች/ተንከባካቢዎች ወንጀላዊ አቤቱታ ሚድልሴክስ አውራጃ ፍርድ ቤት ጋር ማስገባት እንደሚችሉ ይነገራቸዋል። CPS እንደ ሁኔታው ድብደባን በተመለከተ ወንጀላዊ አቤቱታ ሊያስገባ ይችላል። ተማሪዎች ጥል ላይ ሲኑ ያውቃሉ፥ በሰላም ለመፍታት አስፈላጊ ከነ እርዳታ እንዲጠይቁም ይጠበቅባቸዋል። አንድ ተማሪ ስለ ሁኔታው ማንኛውም የትምህርት ቤት ሹም በማሳወቅ ድብድብ የመከላከል ኃላፊነት አለበት። ጥሎችን ለመፍታት የተማሪ/አስተማሪ ሽማግሌዎች በደህንነትና ጥበቃ ቢሮ በኩል ማግኘት ይችላል።

የሚደባደቡ ወይም አካላዊ ጥቃት የሚያደርሱ ተማሪዎችን ለመቅጣት የሚከተሉትን መመሪያዎች መከተል ያስፈልጋል።

ምድብ 1 – አነሳሽ/አስተዋዋቂ/አነቃቂ:-

ረብሻ የተሞላ አለመግባባት ወይም ድብድብ ካለበት ቦታ አንድ ተማሪ ርቆ እንዲሄድ ተጠይቆ እምቢ ካለ በዚህ ምድብ ውስጥ ይገባል።

> የመጀመሪያ ጥፋት – ከትምህርት ቤት እስከ ሶስት ቀን ድረስ ማስወጣት። ወላጅ/አሳዳጊ/ተንከባካቢ እንዲያውቅ ይደረጋል።
>
> ሁለተኛ ጥፋት – ከሶስት እስከ አምስጥ ቀን ከትምህርት ቤት ማስወጣት። ከወላጅ/አሳዳጊ/ተንከባካቢ ጋር ስብሰባ።
>
> ሶስተኛ ጥፋት– ከአምስት እስከ አሥር ቀን ድረስ ከትምህርት ቤት ማስወጣት። ከወላጅ/አሳዳጊ/ተንከባካቢ ጋር ስብሰባ። ተቆጣጣሪ/የከፍተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ዋና ኃላፊ ቢሮ ውስጥ የማባረር ይግባኝ።

ምድብ 2 – ሰው ላይ ድብደባ መፈጸም:-

አንድ ሰው ላይ ድብደባ መፈጸም ወንጀል ነው። ፖሊስ ይነገረዋል፥ ተጠቂዎችም ወንጀላዊ ክስ የማቅረብ መብት እንዳላቸው ይነገራቸዋል። CPS አጥቂው ላይ ወንጀላዊ ክስ ሊያቀርብ ይችላል።

> የመጀመሪያ ጥፋት - ከሶስት እስከ አምስጥ ቀን ከትምህርት ቤት ማስወጣት። ከወላጅ/አሳዳጊ/ተንከባካቢ ጋር ስብሰባ።
>
> ሁለተኛ ጥፋት - ከአምስት እስከ አሥር ቀን ድረስ ከትምህርት ቤት ማስወጣት። ከወላጅ/አሳዳጊ/ተንከባካቢ ጋር ስብሰባ። ተቆጣጣሪ/የከፍተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ዋና ኃላፊ ቢሮ ውስጥ የማባረር ይግባኝ።

ምድብ 3 – ድብድብ/እርስበርስ ድብደባ:-

> የመጀመሪያ ጥፋት - ከትምህርት ቤት እስከ ሶስት ቀን ድረስ ማስወጣት። ከወላጅ/አሳዳጊ/ተንከባካቢ ጋር ስብሰባይደረጋል። ትምህርት ቤት ሲመለሱ ሽምግልና አለ እንዲካፈሉም ይበረታታል።
>
> ሁለተኛ ጥፋት - ከሶስት እስከ አምስጥ ቀን ከትምህርት ቤት ማስወጣት። ከወላጅ/አሳዳጊ/ተንከባካቢ ጋር ስብሰባ። ትምህርት ቤት ሲመለሱ ሽምግልና አለ እንዲካፈሉም ይበረታታል።
>
> ሶስተኛ ጥፋት – ከአምስት እስከ አሥር ቀን ድረስ ከትምህርት ቤት ማስወጣት። ተቆጣጣሪ/የከፍተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ዋና ኃላፊ ቢሮ ውስጥ የማባረር ይግባኝ።

ምድብ 4 – በክፍሎች፥ ካፌቴሪያ፥ ስብሰባ፥ ኮሪዶር፥ በመተላለፊያ ሰዓት፥ የትምህርት ቤት ዳንስ ላይ ወዘተ ድብድብ/እርስበርስ ድብደባ:- ጥሎች (አካላዊም ነ የቃል) በማንኛውም ጊዜ ሲከሰቱ፥ በተለይም ብዙ ሰው ባለበት ቦታ ላይ ሲከሰቱ በትምህርት ቤታችን ውስጥ ተለዋዋጭ ሁኔታ ይፈጥራሉ። ይህ የረብሻና አስጨናቂ ባሕርይ ጥብቅ የቅጣት እርምጃ ያስከትላል። ለምሳሌ:- በካፌቴሪያ ውስጥ በምሳ ሰዓት፥ ውጪ በመለቀቂያ ሰዓት ወይም ሕንጻ ውስጥ በመግቢያ ሰዓት፥ በዳንሶች ላይ፥ የስፖርት ዝግጅቶች ላይ ወይም ማንኛውም የትምህርት ቤት ስብሰባ ወይም ዝግጅት ላይ።

> የመጀመሪያ ጥፋት - ከትምህርት ቤት እስከ ሶስት ቀን ድረስ ማስወጣት። ከወላጅ/አሳዳጊ/ተንከባካቢ ጋር ስብሰባይደረጋል። ትምህርት ቤት ሲመለሱ ሽምግልና አለ እንዲካፈሉም ይበረታታል።
>
> ሁለተኛ ጥፋት - ከሶስት እስከ አምስጥ ቀን ከትምህርት ቤት ማስወጣት። ከወላጅ/አሳዳጊ/ተንከባካቢ ጋር ስብሰባ። ትምህርት ቤት ሲመለሱ ሽምግልና አለ እንዲካፈሉም ይበረታታል።
>
> ሶስተኛ ጥፋት – ከአምስት እስከ አሥር ቀን ድረስ ከትምህርት ቤት ማስወጣት። ተቆጣጣሪ/የከፍተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ዋና ኃላፊ ቢሮ ውስጥ የማባረር ይግባኝ።

27. ጸረ-አስፈራሪ ተማሪዎች ፖሊሲና የአስፈራሪ ተማሪዎች ማገጃና መፍትሄ ማምጫ ዕቅድ

CPS ለተማሪዎች ሁሉ ደህንነቱ የተጠበቀ፣ እንክብካቤና አክብሮት የተሞላ አካባቢ ለመፍጠር ቃል የገባ ሲን፣ አስፈራሪ ተማሪዎች፣ በኢንተርኔት የሚያስፈራሩትንም ጨምሮ እንዲሁም ስለሚያስፈራሩ ተማሪዎች ጥቆማ የሚያደርጉ፣ አንድ ምርመራ ላይ መረጃ የሚሰጡ፣ ምስክር ነው የሚቀርቡ ወይም ስለ አስፈራሪው ጥሩ መረጃ ይዘው የሚቀርቡ ላይ አጸፋ እርምጃ መውሰድን በጥብቅ የሚከለክል ነው። በትምህርት ቤት አስተዳደርና ሠራተኛ፣ ተማሪዎች፣ ቤተሰቦችና የማህበረሰብ አባሎች ትብብር የጎለበቱ በቦታው ላይ የተመሠረቱ እርምጃዎች የሚከተሉትን ለማድረግ ይጥራሉ:- (1) በሁሉም ዕድሜ ያሉ ተማሪዎችና ሁሉም ዓይነት ብቃት ያላቸው ተማሪዎች ደህንነታቸው የተጠበቀ ኖ በጥሞና እንዲያስቡና በራሳቸው እንዲተማመኑ መርዳት እና (2) ተማሪዎች ለሚዘግቡትና አዋቂዎች እራሳቸው ላስተዋሉት ነገር አዋቂዎች ውጤታማ ምላሽ እንዲሰጡ መርዳት።

ማስፈራራት ማለት አንድ ወይም ብዙ ተማሪ፣ ወይም የትምህርት ቤት ሠራተኛ ማለትም አስተማሪን፣ አስተዳዳሪን፣ የትምህርት ቤት ነርስን፣ የካፌቴሪያ ሠራተኛን፣ ጽዳት ሠራተኛን፣ አውቶቡስ አሽከርካሪን፣ የስፖርት አሰልጣኝን፣ ከትምህርት በተጨማሪ ለሚሰጡ እንቅስቃሴዎች አማካሪን ጨምሮ በተደጋጋሚ በጽሑፍ፣ በቃል ወይም በኤሌክትሮኒክ መንገድ ወይም በአካል ድርጊት ወይም በምልክት ተጠቂው ላይ የሚከተሉትን ሲያስከትሉ ነው:-

(1) ተጠቂው ላይ አካላዊ ወይም ስሜታዊ ጉዳት ወይም ንብረቱ ላይ ጉዳት፣ (2) ተጠቂው ባግባቡ እራሱ ላይ ወይም ንብረቱ ላይ ጉዳት ይደርስብኛል ብሎ ሲፈራ፣ (3) ለተጠቂው በጥላቻ መንፈስ የተሞላ ሁኔታ በትምህርት ቤት ውስጥ ሲፈጥር፣ (4) በትምህርት ቤት ውስጥ የተጠቂው መብቶች ላይ ተጽዕኖ ሲያደርግ፣ ወይም (5) የትምህርት ሂደቱን ወይም የትምህርት ሥርዓቱን በተጨባጭና በከፍተኛ ሁኔታ ሲያጨናግፍ። በዚህ ፖሊሲ ላይ ማስፈራራት ማለት የኢንተርኔት ማስፈራራትንም ይጨምራል።

በስቴቱ ሕግ መሠረት የኬምብሪጅ መንግሥት ትምህርት ቤቶች አንዳንድ ተማሪዎች በሚከተሉት መለያዎች ምክንያት ከሌሎች የበለጠ የማስፈራራት ተጠቂ ሊኑ እንደሚችሉ ያውቃል፦ ማለትም በዘር፣ ቀለም፣ ዜግነት፣ ዘር ማንዘር፣ ኃይማኖት፣ ዕድሜ፣ አካል ብቃት፣ የሥነ ዘር መረጃ፣ ውትድርና ውስጥ በፊት በማገልገል፣ የጋብቻ ሁኔታ፣ ጾታ፣ መታወቂያ ጾታ ወይም ጾታ መግለጫ፣ የጓደኛ ጾታ ምርጫ፣ ነፍሰ ጡርነት፣ ወይም ከነፍሰ ጡርነት ጋር የተያያዘ ሁኔታ፣ የገቢ ደረጃ፣ ቤት አልባነት፣ የትምህርት ነጥብ፣ አካላዊ ገጽታ፣ የወላጅ ሁኔታ ወይም ከእነዚህ ነገሮች ውስጥ አንድ (1) ወይም ከዛ በላይ ካለው ሰው ጋር አብሮ በመን።

<u>በኢንተርኔት ማስፈራራት</u> ማለት በኤሌክትሮኒክ መሳሪያ በኩል ማስፈራራት ሲን፣ ይህም ምልክቶችን፣ ጽሑፎችን፣ ስዕሎችን፣ ድምጾችን፣ መረጃን በሙሉ ወይም በከፊል በድብቅ ማዳመጫ፣ በሬዲዮ፣ በኤሌክትሮማግኔቲክ፣ በኤሌክትሮኒክ ፎቶ ሲስተም፣ በኢሜል፣ በኢንተርኔት መነጋገሪያ መንገዶች፣ በኢንስታንት መልዕክት ወይም በፋክስ ማስተላለፍን ይጨምራል። በኢንተርኔት ማስፈራራት የሚከተሉትንም ይጨምራል፦ (1) ያልኑትን ሰው ነኝ ብሎ ድህረ ገጽ ወይም ብሎግ መክፈት ወይም (2) አውቀው ያልኑትን ሰው ነኝ ብለው በዛ ሰው ስም መልዕክቶችና ጽሑፎች ማቅረብ፣ ሌላውን ሰው ማስመሰሉ ከመስፈርቶች (1) እስከ (5) ያሉትን የማስፈራራት ፍቺ ውጤቶች ካስከተሉ። በኢንተርኔት ማስፈራራት ማለት በተጨማሪም በኤሌክትሮኒክ መንገድ ለብዙ ሰዎች መረጃ ማሰራጨት ወይም ከአንድ ሰው በላይ የሚያየው ቦታ ላይ ይህን መረጃ መለጠፍ፣ መረጃው ከመስፈርቶች (1) እስከ (5) ያሉትን የማስፈራራት ፍቺ ውጤቶች ካስከተሉ።

<u>አጥቂ</u> ወይም ወንጀለኛ_ ማለት በአካልም ነ በኢንተርኔት የሚያስፈራራ ወይም አጸፋ መላሽ ተማሪ ወይም የትምህርት ቤት ሠራተኛ ማለትም አስተማሪን፣ አስተዳዳሪን፣ የትምህርት ቤት ነርስን፣ የካፌቴሪያ ሠራተኛን፣ ጽዳት ሠራተኛን፣ አውቶቡስ አሽከርካሪን፣ የስፖርት አሰልጣኝን፣ ከትምህርት በተጨማሪ ለሚሰጡ እንቅስቃሴዎች አማካሪን፣ የትምህር ቤት በጎ ፈቃደኛ አገልጋይን፣ ሻጭ ወይም በትምህርት ቤት አውራጃው ኮንትራት ሥር የሚሠራ ሰውን ጨምሮ ነው።

<u>በጥላቻ የተሞላ አካባቢ</u> ማለት በ M.G.L. c. 71, § 37O ውስጥ በተሰጠው ፍቺ መሠረት፣ በማስፈራራት ምክንያት የተማሪው ትምህርት ሁኔታ በዛቻ፣ ውርደት ወይም ስድብ የተሞላ ሲን መጠኑ ከፍተኛ ከመኑ የተነሳ የተማሪውን የትምህርት ሁኔታ እስከመቀየር ደርሷል ማለት

<u>በቀል</u> ማለት ማስፈራራትን የሚጠቁም፣ የማስፈራራት ምርመራ ሂደት ላይ መረጃ የሚሰጥ ወይም የማስፈራራት ምስክር ኖ የሚታመን መረጃ ያለው ተማሪ ላይ ዛቻ ማድረግ፣ አጸፋ ምላሽ መስጠት ወይም መጎትጎት ማለት ነው።

<u>ሠራተኛ</u> ማለት አስተማሪዎችን አስተዳዳሪዎችን፣ አማካሪዎችን፣ የትምህርት ቤት ነርሶችን፣ የካፌቴሪያ ሠራተኞችን፣ ጽዳት ሠራተኞችን፣ አውቶቡስ አሽከርካሪዎችን፣ ስፖርት አሰልጣኞችን፣ የትርፍ ሰዓት እንቅስቃሴ አማካሪዎችን፣ የድጋፍ ሠራተኞችንና ሙያተኞችን ይጨምራል።

<u>ዒላማ ወይም ተጠቂ</u> ማለት ማስፈራራት፣ የኢንተርኔት ማስፈራራት ወይም አጸፋ መልስ የደረሰበት ተማሪ ወይም አዋቂ ነው።

ማስፈራራት በብዙ መልክና በማንኛውም ሁኔታ ሊከሰት ይችላል። ማስፈራራት የሚከተሉትን ሊያካትት ይችላል፦ ዛቻን ለምሳሌ መሳደብ፣ ማህበራዊ ማግለል ለምሳሌ ማራቅ ወይም ስም ማጥፋት፣ ወይም አካላዊ ጥቃት ለምሳሌ ተማሪን ወይም የተማሪውን ንብረት ማጥቃት። ማስፈራራት ለሁሉም የትምህርት ቤት ማህበረሰብ የፍርሃት ስሜት ሊፈጥር ይችላል። በተጨማሪም አንድ ተማሪ ትምህርት ቤት መሄዱን፣ ትምህርት ቤት ውስጥ የመማር ችሎታው፣ የትምህርት ቤት ሕንጻ ውስጥ መራመዱን፣ የትምህርት ቤት ካፌቴሪያ ውስጥ መብላት መቻሉን፣ የትምህርት ቤቱ መዝናኛ ቦታዎች ላይ መጫወት መቻሉን፣ ልዩ ፕሮግራሞች ወይም ከትምህርት ውጪ ያሉ ክፍሎች ውስጥ መሳተፍ መቻሉን ወይም ከቤት ወደ ትምህርት ቤት መመላለሱ ላይ ተጽዕኖ ፈጥሮ አላስፈላጊና አላግባብ የነ ጭንቀት ሊፈጥር ይችላል። በይበልጥ ግልጽ ለማድረግ "በጥላቻ የተሞላ አካባቢ" ማለት በማስፈራራት ምክንያት የተማሪው ትምህርት ሁኔታ በዛቻ፣ ውርደት ወይም ስድብ የተሞላ ሲን መጠኑ ከፍተኛ ከመኑ የተነሳ የተማሪውን የትምህርት ሁኔታ እስከመቀየር ደርሷል ማለት ነው። መፍትሄ ያልተገኘላቸው የማስፈራራት ባሕርዮች ወጣቶች ላይ አስከፊ ውጤቶች ሊያስከትሉ ይችላሉ፦ የሥነ ልቦና ውድቀትን፣ ትምህርት ላይ ድክመትና ከትምህርት ቤት መቅረትን ጨምሮ። የማስፈራራት ባሕርዮች ዝም ከተባሉ ሌሎች ተማሪዎች የሚያገኙት መልዕክት አሉታዊ ባሕርይ መያዝ ተቀባይነት እንዳለው ነው።

በትምህርት ቤቱ ውስጥ ማስፈራራት በሕግ የተከለከለ ሲን CPS በጭራሽ የሚቀበለው ነገር አይደለም። በዚህ ፖሊሲ ላይ "ትምህርት ቤት" ሲባል ትምህርት ቤቶችን፣ የትምህርት ቤት ግቢዎችን፣ ወደ ትምህርት ቤት እና/ወይም ትምህርት ቤቱ ድጋፍ ወደሚያደርግባቸው ዝግጅቶች መመላለስን፣ የትምህርት ቤት ግቢ ጎን ያሉ ንብረቶችን፣ በትምህርት ቤት ድጋፍ ወይም ከትምህርት ቤት ጋር የተያያዙ እንቅስቃሴዎችን፣ ድግሶችን፣ በትምህርት ቤት ውስጥም ውጪም ያሉ መርሀ ግብሮችን (ለምሳሌ ማህበራዊ ዝግጅቶች፣ ጉዞዎች፣ የስፖርት ዝግጅቶች ወይም ተመሳሳይ በትምህርት ቤት ድጋፍ የተዘጋጁ ዝግጅቶች)፣ የትምህርት ቤት አውቶቡስ መጠበቂያ ጣቢያን፣ አውቶቡስ ውስጥ ወይም ሌላ የትምህርት ቤት አውራጃው ንብረት የነ ወይም የተከራየው ተሽከርካሪን፣ ከትምህርት ቤት ወይም ወደ ትምህርት ቤት ጉዞ ላይ ወይም የትምህርት ቤት አውራጃው ንብረትነት የነ ወይም የትምህርት ቤት አውራጃው የሚከራየው ወይም የሚጠቀመው ኤሌክትሮኒክ መሳሪያ በመጠቀም፣ እንዲሁም ከትምህርት ቤት ጋር ያልተያያዘ ቦታ፣ እንቅስቃሴ፣ ዝግጅት ወይም መርሃ ግብር ወይም የትምህርት ቤት አውራጃው ንብረትነት ያልነ ወይም የትምህርት ቤት አውራጃው የማይከራየው ወይም የማይጠቀመው ኤሌክትሮኒክ መሳሪያ በመጠቀም የሚደረግ ማስፈራራት ትምህርት

ቤት ውስጥ የጥላቻ ስሜት የሚፈጥር ከነ፣ በትምህርት ቤት ውስጥ የተጠቂውን ወይም የምስክሮችን መብቶች የሚነካ ከነ፣ እንዲሁም የትምህርት አሰጣጡን ወይም የትምህርት ሥርዓቱን የሚረብሽ ከነ ሁሉንም ያጠቃልላል። በስቴቱ ሕግ መሠረት CPS አንዳንድ ተማሪዎች በሚከተሉት መለያዎች ምክንያት ከሌሎች የበለጠ የማስፈራራት ተጠቂ ሊኑ እንደሚችሉ ያውቃል፦ ማለትም በዘር፣ ቀለም፣ ዜግነት፣ ዘር ማንዘር፣ ኃይማኖት፣ ዕድሜ፣ አካል ብቃት፣ የሥነ ዘር መረጃ፣ ውትድርና ውስጥ በፊት በማገልገል፣ የጋብቻ ሁኔታ፣ ጾታ፣ መታወቂያ ጾታ ወይም ጾታ መግለጫ፣ የጓደኛ ጾታ ምርጫ፣ ነፍሰ ጡርነት፣ ወይም ከነፍሰ ጡርነት ጋር የተያያዘ ሁኔታ፣ የገቢ ደረጃ፣ ቤት አልባነት፣ የትምህርት ነጥብ፣ አካላዊ ገጽታ፣ የወላጅ ሁኔታ ወይም ከእነዚህ ነገሮች ውስጥ አንድ (1) ወይም ከዛ በላይ ካለው ሰው ጋር አብሮ በመን።

CPS የማስፈራራት ክሶችን በቁም ነገር የሚወስድ ሲን የማስፈራራት ክሶች ሲቀርቡ በፍጥነት መልስ ይሰጣል። በተጨማሪም ማስፈራራትን የሚጠቁም፣ የማስፈራራት ምርመራ ሂደት ላይ መረጃ የሚሰጥ ወይም የማስፈራራት ምስክር ኖ የሚታመን መረጃ ያለው ሰው ላይ በቀል ማድረግ የተከለከለ ነው።

አንድ ተማሪ ማስፈራራት ደርሶበታል ወይም ማስፈራራትን በመጠቆሙ፣ የማስፈራራት ምርመራ ላይ መረጃ በመስጠቱ ወይም ምስክር ኖ የሚታመን መረጃ ስላለው በቀል ደርሶበታል ብሎ አንድ ተማሪ፣ የአንድ ተማሪ ወላጅ/አሳዳጊ/ተንከባካቢ፣ ሠራተኛ ወይም ሌላ የማህበረሰቡ አባል ካመነ ተማሪው የሚሄድበት ትምህርት ቤት ውስጥ ያለው የከፍተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ዋና ተቆጣጣሪ ጋር ጉዳዩን ማቅረብ አለባቸው። ይህ በቃል ወይም በጽሑፍ ሊደረግ ይችላል። የማስፈራራት ክሶች እና/ወይም ማስፈራራትን በመጠቆሙ፣ የማስፈራራት ምርመራ ላይ መረጃ በመስጠቱ ወይም ምስክር ኖ የሚታመን መረጃ ስላለው የበቀል ክሶች ተማሪው የሚሄድበት ትምህርት ቤት ውስጥ ያለው የከፍተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ዋና ተቆጣጣሪ ጋር ስምን ሳይገልጹ በምስጢር ማቅረብም ይቻላል። ኖም እባክዎን ልብ ይበሉ፦ በምስጢር ክስ ሲደርስ በሱ ላይ ብቻ ተመስርቶ አንድ ተማሪ ላይ የቅጣት እርምጃ አይወሰድም።

ሁሉም የትምህርት ቤት ሠራተኞች (አስተማሪዎችን አስተዳዳሪዎችን፣ አማካሪዎችን፣ የትምህርት ቤት ነርሶችን፣ የካፌቴሪያ ሠራተኞችን፣ ጽዳት ሠራተኞችን፣ አውቶቡስ አሽከርካሪዎችን፣ ስፖርት አሰልጣኞችን፣ የትርፍ ሰዓት እንቅስቃሴ አማካሪዎችን፣ የድጋፍ ሠራተኞችንና ሙያተኞችን ጨምሮ) የ CPS ጸረ-ማስፈራራት ፖሊሲና የማስፈራራት ማስወገጃና ማስተናገጃ ዕቅድን በተመለከተ ዓመታዊ ስልጠና ያገኛሉ። የሠራተኞች ግዴታዎችና ኃላፊነቶች በ CPS ጸረ-ማስፈራራት ፖሊሲና የማስፈራራት ማስወገጃና ማስተናገጃ ዕቅድ ውስጥና *የሠራተኞች ፖሊሲዎች መመሪያ* ውስጥ ይገኛሉ።

ከቤተሰቦች ጋር ትብብር

Welcoming Schools/School Climate Coordinator and Family Liaisons (ተቀባይ የትምህርት ቤቶች/የትምህርት ቤት መንፈስ አስተባባሪና የቤተሰብ አገናኝ) ከማዕከላዊ ቢሮና ተቆጣጣሪዎች/የከፍተኛ ትምህርት ቤቶች ዋና ኃላፊ ጋር በመተባበር ለወላጆች/አሳዳጊዎች/ተንከባካቢዎች አስፈራረነትን እንዴት ለይቶ ማወቅ እንደሚቻልና ተጠቂዎች፥ ተመልካቾና አስፈራሪ ግለሰቦች ላይ ስላለው ተጽዕኖ መማሪያ ዕድሎች ያቀርባሉ። ለወላጆች/አሳዳጊዎች/ተንከባካቢዎች በተጨማሪም በልጃቸው ትምህርት ቤት ውስጥ አስፈራሪዎችን በተመለከተ ስላለው የትምህርት ሥርዓት፥ የማስፈራራት ሁለንተና ባሕርይና ስለ ኢንተርኔት ደህንነትና በኢንተርኔት ማስፈራራትን በተመለከተ፥ ሕጉ ማስፈራራት ላይ ስላለው ተጽዕኖና አንድ ልጅ ወይም ሠራተኛ ማስፈራራት ላይ ቢሳተፉ ሊያመጣ የሚችለው መዘዝ እንዲሁም ማስፈራራትን ለማሳወቅ ያለው ሂደትና የማሳቹሴትስ ተማሪ መዝገብ የምስጢርነት ደንቦች 603 C.M.R. 23.00፥ እና የ Federal Family Educational Rights and Privacy Act (ፌዴራል የቤተሰብ ትምህርታዊ መብቶችና የግለኝነት ሕግ) ደንቦች፥ 34 C.F.R. ክፍል 99፥ 603 C.M.R. 49.07 ውስጥ ባለው መሠረት ተቆጣጣሪ/የከፈተኛ ደረጃ ዋና ኃላፊ ወላጅ/አሳዳጊን/ተንከባካቢን ስለ ማስፈራራት ወይም አጸፋ ስለመመለስ የተደረገ ዘገባን ስለማሳወቅ መረጃ ያገኛሉ።

ጣልቃ ገብነትና የማሳወቅ መስፈርቶች

ኖም ሠራተኞች ሁሉ ያዩትን ወይም የሰሙትን የማስፈራራት ወይም የአጸፋ መልስ ሁኔታ ወዲያውኑ ለትምህርት ቤቱ የከፍተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ዋና ኃላፊ ወይም ተወካዩ የማሳወቅ ድጌታ እንዳለባቸው ማስተዋሉ አስፈላጊ ነው። ለትምህርት ቤቱ የከፍተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ዋና ኃላፊ ወይም ለተወካዩ የማሳወቅ ግዴታ ሠራተኛው በትምህርት ቤት አውራጃው የባሕርይ አስተዳደርና ቅጣት ፖሊሲዎችና ሂደቶች መሠረት የባሕርይ ወይም የሚያስቀጡ ክስተቶች ሲካሄዱ ምላሽ ለመስጠት ያለውን ሥልጣን ይወስነዋል ማለት አይደለም።

ተቆጣጣሪ/የከፍተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ዋና ኃላፊው ክሱ ሲደርሰው ወዲያውኑ የሚከተሉትን ያሳውቃል፦

- የተጠቂ ተብዬው ወላጆች/አሳዳጊዎች/ተንከባካቢዎች
- የአጥቂ ተብዬው ወላጆች/አሳዳጊዎች/ተንከባካቢዎች ወይም አጥቂ ተብዬውን የትምህርት ቤት ሠራተኛ ከነ
- የደህንነትና ጥበቃ ቢሮ

ተቆጣጣሪ/የከፍተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ዋና ኃላፊ ወዲያውኑ የደረሰውን ክስ በተመለከተ ምርመራ ያካሂዳል።

ተቆጣጣሪ/የከፍተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ዋና ኃላፊው የትምህርት ቤት ግልጋሎቶች ሹምን ሊያማክር ይችላል ኖም ስለ ተጠቂ ተብዬው ወይም አጥቂ ተብዬው ምንም ዓይነት መለያ መረጃ አያካፍልም።

የከፍተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ዋና ኃላፊው የተጠቂ ተብዬውና የአጥቂ ተብዬው ወላጆች/አሳዳጊዎች/ተንከባካቢዎችን ሲያሳውቅ በ Massachusetts Student Record (ማሳቹሴትስ የተማሪ መዝገብ) ደንቦች 603 C.M.R. 23.00 እና በ Federal Family Educational Rights and Privacy Act (ፌዴራል የቤተሰብ ትምህርት መብቶችና ምስጢራዊ ሕግ) 34 C.F.R. Part 99 ደንቦች 603 C.M.R. 49.07 ውስጥ በተዘረዘረው መሠረት በምስጢር የመያዝ መስፈርቶችን ተከትሎ መን አለበት። በተለይም የከፍተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ዋና ኃላፊው ለወላጆች/አሳዳጊዎች/ተንከባካቢዎች ከተጠቂ ተብዬው ወይም ከአጥቂ ተብዬው የተማሪ መዝገብ ውስጥ ምንም ዓይነት መረጃ አሳልፎ መስጠት አይችልም፣ መረጃው ስለ

ወላጆች/አሳዳጊዎች/ተንከባካቢዎች ልጅ ካልነ በስተቀር። አንድ የከፍተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ዋና ኃላፊ ማስፈራራት መከሰቱን ወይም የአጸፋ ምላሽ ድርጊት መከሰቱን ለአካባቢው ሕግ አስከባሪ ድርጅት በ603 C.M.R. 49.06 መሠረት የተማሪውን ወይም የለወላጆች/አሳዳጊዎች/ተንከባካቢዎች ፈቃድ ሳይጠይቅ ሊያሳውቅ ይችላል፣ ኖም የከፍተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ዋና ኃላፊው ከሕግ አስከባሪ ባለሥልጣኖች ጋር ሲነጋገር የዒላማዎችን፣ የምስክር ተማሪዎችንና የአጥቂዎችን ማንነት ሁኔታው እስከሚፈቅደው ድረስ ሳያሳውቅ መን አለበት። በተጨማሪ አጥቂው የትምህርት ቤት ሠራተኛ ከነ የከፍተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ዋና ኃላፊው ተገቢውን የቅጣት እርምጃ ሊወስድ ይችላል፣ ማባረርን ጨምሮ። በተጨማሪም የከፍተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ዋና ኃላፊው ተማሪው ወይም ሌሎች ግለሰቦች ለጤናቸው ወይም ለደህንነታቸው አስጊ ሁኔታ አለ ብሎ ካመነ ከሕግ አስከባሪ ድርጅት ሌላ ለሚመለከታቸው ግለሰቦች ስለ ተጠቂው ወይም ስለ አጥቂው ከተማሪ መዝገቡ ውስጥ መረጃ ሊያካፍል ይችላል፣ በ603 C.M.R. 23.07(4)(e) እና 34 C.F.R. 99.13(a)(10) እና 99.36 መሠረት መረጃውን ማወቅ የተማሪውን ወይም የሌሎች ግለሰቦችን ጤንነት ወይም ደህንነት ይጠብቃል ተብሎ ከታመነ። በዚህ በመጨረሻ በተጠቀሰው ዓይነት ሁኔታ ላይ መረጃ የሚተላለፈው ድንገተኛ ሁኔታው በሚካሄድበት የጊዜ ርዝመት ብቻ ሲን የከፍተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ዋና ኃላፊው የተላለፈውን መረጃና ለጤና ወይም ለደህንነት አስጊ ሁኔታ ነው ብሎ የደመደመበትን ምክንያቶች መመዝገብ አለበት።

ተቆጣጣሪው/የከፍተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ዋና ኃላፊ የ CPS ጸረ-አድሎ ፖሊሲና የጾታ ጉትጎታ ክልከላ እና የኬምብሪጅ መንግሥት ትምህርት ቤቶች ጸረ-ማስፈራራት ፖሊሲ ቅጂ ለሚመለከታቸው ሁሉ ክስ አቅራቢውን፣ ተጠቂ ተብዬ ተማሪውን፣ የተጠቂ ተብዬው ተማሪ ወላጆች/አሳዳጊዎች/ተንከባካቢዎችን፣ አጥቂ ተብዬው ተማሪ ከነ አጥቂ ተብዬውንና የአጥቂ ተብዬው ወላጆች/አሳዳጊዎች/ተንከባካቢዎችን ጨምሮ ይሰጣል።

የማስፈራራት ክሶች እና/ወይም ማስፈራራትን በመጠቆሙ የሚመጡ የበቀል ክሶች ተቆጣጣሪ/የከፍተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ዋና ኃላፊ ጋር ስምን ሳይገልጹ በምስጢር ማቅረብም ይቻላል። ኖም እባክዎን ልብ ይበሉ፦ በምስጢር ክስ ሲደርስ በሱ ላይ ብቻ ተመስርቶ አንድ ተማሪ ላይ የቅጣት እርምጃ አይወሰድም።

የክስ ምርምራ

CPS የማስፈራራት ክስ ወይም ማስፈራራትን በመጠቆም የበቀል ክስ፣ የማስፈራራት ምርመራ ሂደት ላይ መረጃ ስለሰጠ የበቀል ክስ ወይም የማስፈራራት ምስክር ኖ የሚታመን መረጃ ያለው ሰው ላይ የበቀል ክስ ሲደርሰው፣ CPS ክሱን ትክክልና ፈጣን በነ መንገድ ይመረምራል። ምርመራው የሚካሄደው ሁኔታዎቹ እስከሚፈቅዱት ድረስ ማንነትን በምስጢር ይዞና ማስፈራራትን የሚጠቁም ሰው፣ የማስፈራራት ምርመራ ሂደት ላይ መረጃ የሰጠ ሰው ወይም የማስፈራራት ምስክር ኖ የሚታመን መረጃ ያለው ሰው ማስፈራራት ወይም በቀል እንዳይደርስበት በመጠበቅ ነው።

ምርመራው ከተማሪው፣ ከወላጅ/አሳዳጊ/ተንከባካቢ፣ ክሱን ካስገባው ሠራተኛ ወይም የማህበረሰብ አባል፣ የማስፈራራት ወይም የበቀል ተጠቂ ተብዬው ተማሪ፣ ማስፈራራቱን ወይም በቀሉን ፈጽሟል ከተባለው ተማሪ/ዎች ወይም ሠራተኛ/ዎች፣ ከክስተቱ ምስክሮች፣ ወይም ሌሎች ሰዎች ጋር እንደ መምሪያው ውሳኔ ቃለ መጠይቅ ሊያካትት ይችላል። ማስፈራራት ወይም አጸፋ መልስ ተከስቷል ብሎ ከወሰነ በኋላ፣ የከፍተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ኃላፊው የተጠቂውንና ወላጆች/አሳዳጊዎች/ተንከባካቢዎችና አጥቂው ተማሪ ከነ የአጥቂውን ወላጆች/አሳዳጊዎች/ተንከባካቢዎች ወዲያውኑ ይህንኑ ውሳኔና ምላሽ መስጫ ሂደቶችን ያሳውቃል። የከፍተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ኃላፊው ምርመራው ከመካሄዱ በፊት ወላጆች/አሳዳጊዎች/ተንከባካቢዎችን አስቀድሞ የሚገናኝበት አንዳንድ ሁኔታ ሊኖር ይችላል። ማስታወቂያው የሚሰጠው 603 C.M.R. 49.00 ላይ ባሉት ስቴት ደንቦች መሠረት ይናል። የከፍተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ኃላፊው የአጥቂውና የተጠቂውን ወላጆች/አሳዳጊዎች/ተንከባካቢዎች በሚያሳውቅበት ጊዜ በ Massachusetts Student Record (የማሳቹሴትስ የተማሪ መዝገብ) ደንቦች የምስጢራዊነት መስፈርቶች 603 C.M.R. 23.00 መሠረትና በ Federal Family Educational Rights and Privacy Act (ፌዴራል የቤተሰብ ትምህርት መብቶችና ምስጢራዊ ሕግ) 34 C.F.R. Part 99 በ 603 C.M.R. 49.07 ውስጥ የተጠቀሰውን ተከትሎ መን አለበት። በተለይም የከፍተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ዋና ኃላፊው ለወላጆች/አሳዳጊዎች/ተንከባካቢዎች ከተጠቂ ተብዬው ወይም ከአጥቂ ተብዬው የተማሪ መዝገብ ውስጥ ምንም ዓይነት መረጃ አሳልፎ መስጠት አይችልም፣ መረጃው ስለ ወላጆች/አሳዳጊዎች/ተንከባካቢዎች ልጅ ካልነ በስተቀር። አንድ የከፍተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ዋና ኃላፊ ማስፈራራት መከሰቱን ወይም የአጸፋ ምላሽ ድርጊት መከሰቱን ለአካባቢው ሕግ አስከባሪ ድርጅት በ603 C.M.R. 49.06 መሠረት የተማሪውን ወይም የለወላጆች/አሳዳጊዎች/ተንከባካቢዎች ፈቃድ ሳይጠይቅ ሊያሳውቅ ይችላል፣ ኖም የከፍተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ዋና ኃላፊው ከሕግ አስከባሪ ባለሥልጣኖች ጋር ሲነጋገር የዒላማዎችን፣ የምስክር ተማሪዎችንና የአጥቂዎችን ማንነት ሁኔታው እስከሚፈቅደው ድረስ ሳያሳውቅ መን አለበት። በተጨማሪም የከፍተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ዋና ኃላፊው ተማሪው ወይም ሌሎች ግለሰቦች ለጤናቸው ወይም ለደህንነታቸው አስጊ ሁኔታ አለ ብሎ ካመነ ከሕግ አስከባሪ ድርጅት ሌላ ለሚመለከታቸው ግለሰቦች ስለ ተጠቂው ወይም ስለ አጥቂው ከተማሪ መዝገቡ ውስጥ መረጃ ሊያካፍል ይችላል፣ በ603 C.M.R. 23.07(4)(e) እና 34 C.F.R. 99.13(a)(10) እና 99.36 መሠረት መረጃውን ማወቅ የተማሪውን ወይም የሌሎች ግለሰቦችን ጤንነት ወይም ደህንነት ይጠብቃል ተብሎ ከታመነ። በዚህ በመጨረሻ በተጠቀሰው ዓይነት ሁኔታ ላይ መረጃ የሚተላለፈው ድንገተኛ ሁኔታው በሚካሄድበት የጊዜ ርዝመት ብቻ ሲን የከፍተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ዋና ኃላፊው የተላለፈውን መረጃና ለጤና ወይም ለደህንነት አስጊ ሁኔታ ነው ብሎ የደመደመበትን ምክንያቶች መመዝገብ አለበት። በተጨማሪም ይህ ተከስቷል ከተባለ በስቴት ሕግ መሠረት የተጠቂው/ዎቹ ወላጆች/አሳዳጊዎች/ተንከባካቢዎች ስለ ምርመራው ውጤትና ሌላ ማስፈራራት ወይም በቀል እንዳይከሰት ስለሚወሰዱ ስለ ማናቸውም እርምጃዎች ማስታወቂያ ይሰጣቸዋል።

በተጨማሪም በስቴት ሕጉና በ CPS እና በኬምፐሪጅ ፖሊስ መምሪያ መካከል ባለው የመግባቢያ ውል መሠረት ማስፈራራት ወይም በቀል ተከስቷል ተብሎ ከተደመደመ የከፍተኛ ደረጃት ትምህርት ቤት ዋና ኃላፊ ከደህንነትና ጥበቃ ዳይሬክተር ጋር አብሮ በመተባበር የሚከተሉትን ያደርጋል፡-

- ከተደመደመ የከፍተኛ ደረጃት ትምህርት ቤት ዋና ኃላፊ አጥቂው ላይ የወንጀል ክስ ይቀርብበታል ብሎ ካሰበ ወይም ለተማሪው ወይም ለሎች ግለሰቦች ጤና ወይም ደህንነት አስጊ ክስተት ሊኖር ይችላል ብሎ ካመነ የትምህርት ቤት ግሊጋሎቶች ሹምን ማሳወቅ
- በ*መብቶችና ኃላፊነቶች መመሪያ* መሠረት ተገቢውን የቅጣት እርምጃ መውሰድ
- አጥቂው/ዎቹ ተማሪ ከነ ወላጆች/አሳዳጊዎች/ተንከባካቢዎችን ማሳወቅ ወይም አጥቂው ሠራተኛ ከነ እራሱን ማሳወቅ
- የተጠቂውን/ዎቹን ወላጆች/አሳዳጊዎች/ተንከባካቢዎችን በስቴትና ፌዴራል ሕግና ደንቦች መሠረት ማሳወቅ፣ ሌላ ማስፈራራትና በቀል እንዳይደርስ የተወሰደውን እርምጃ ማሳወቅ።

በተጨማሪም የማስፈራራት ወይም የበቀል ክስተቱ የሚመለከታቸው ተማሪዎች የተለያየ የትምህርት ቤት አውራጃ፣ ቻርተር ትምህርት ቤት፣ የመንግሥት ያልነ ትምህርት ቤት፣ ፈቃድ ያለው የግል ትምህርት ቤት፣ የመኖሪያ ቤት ውስጥ ትምህርት ቤት ወይም የትብብር ትምህርት ቤት ውስጥ ከነ የሚሄዱት በመጀመሪያ ስለ ማስፈራራቱ ወይም ስለ በቀሉ መረጃ የደረሰው የትምህርት ቤት አውራጃ ወይም ትምህርት ቤት በስቴትና በፌዴራል ሕግ መሠረት የሌላውን ትምህርት ቤት አውራጃ ወይም የሌላውን ትምህርት ቤት አስተዳዳሪ ተገናኝቶ አሳውቆት ሁለቱም ተገቢውን እርምጃ መውሰድ አለባቸው።

የከፍተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ዋና ኃላፊ ወይም ተወካዩ የማስፈራራት ወይም የአጸፋ ምላሽ ማስታወቂያ ከደረሰው ከማንኛውም ጊዜ በኋላ፣ ከምርመራውም በኋላ ቢ ፣ ተጠቂው ላይ ወንጀላዊ ክስ ይመሰረትበታል ብሎ ካመነ የከፍተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ዋና ኃላፊ ከደህንነትና ጥበቃ ዳይሬክተሩ ጋር አብሮ በመን የአካባቢውን ሕግ አስከባሪ ድርጅት ያሳውቃሉ። ማስታወቂያው የሚሰጠው 603 C.M.R. 49.00 ሥር ባሉት መስፈርቶችና በ CPS እና በኬምፐሪጅ ፖሊስ መምሪያ መካከል ባለው የመግባቢያ ውል መሠረት ነው። በተጨማሪም የማስፈራራት ወይም የበቀል ክስተቱ የተካሄደው በትምህርት ቤት ቅጥር ግቢ ውስጥ ከነና አንዱ ተማሪ ዕድሜው ከ21 ዓመት በታች ኖ ድሮ እንጂ አሁን የትምህርት ቤት አውራጃ፣ ቻርተር ትምህርት ቤት፣ የመንግሥት ያልነ ትምህርት ቤት፣ ፈቃድ ያለው የግል ትምህርት ቤት፣ የመኖሪያ ቤት ውስጥ ትምህርት ቤት ወይም የትብብር ትምህርት ቤት ውስጥ ያልተመዘገበ ተማሪ ከነ ስለ ማስፈራራቱ ወይም ስለ በቀሉ የተነገረው የትምህርት ቤት አውራጃ ወይም ትምህርት ቤት በስቴትና በፌዴራል ሕግና ደንቦች መሠረት ሕግ አስከባሪዎችን መገናኘት አለበት። የከፍተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ኃላፊው ይህንን ውሳኔ ሲያደርግ በዋናው ዕቅድ መሠረት፣ በሚመለከታቸው የትምህርት ቤት አውራጃ ፖሊሲዎችና ሂደቶች መሠረት እንዲሁም በ CPS እና በኬምፐሪጅ ፖሊስ መምሪያ መካከል ባለው የመግባቢያ ውል መሠረት ከትምህርት ቤት ግሊጋሎቶች ሹምና ከሌሎች ግለሰቦች ጋር ተማክሮ ነው።

ለማስፈራራት ክስተት የቅጣት እርምጃ/ምላሾች

ቅጣትን በተመለከተ የኬምብሪጅ መንግሥት ትምህርት ቤቶች ያለው ዓላማ የማህበረሰቡ ግለሰቦች እርስ በርስ ሲጎዳዱ መላ ማህበረሰቡ ላይ የደረሰውን ጉዳት ማስተካከል የሚችሉበትን የመማሪያ ገበታ መፍጠር ነው። ማስፈራራት ወይም ሌላ አግባብ የሌለው ባሕርይ ተከስቷል ተብሎ ከተወሰነ CPS ለሁኔታው አግባብ ያለው እርምጃ ይወስዳል። የቅጣት እርምጃው ኃላፊነት መውሰድንና የትምህርት ቤት ማህበረሰቡ ላይ የደረሰውን ጉዳት መጠገንን አስታርቆ ትክክለኛውን ባሕርይ ያስተምራል። እንዳግባብነቱ መልሶ ገንቢ መንፈስ በመጠቀም የከፍተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ኃላፊው ወይም ተወካዩ አንድ ተማሪ ማስፈራራት እንዳይደርስበት፣ ማስፈራራትን ስለጠቆመ በቀል እንዳይደርስበት፣ የማስፈራራት ምርመራ ሂደት ላይ መረጃ ስለሰጠ በቀል እንዳይደርስበት ወይም የማስፈራራት ምስክር ኖ የሚታመን መረጃ ስላለው በቀል እንዳይደርስበት አግባብ ያላቸው የመከላከያ ስልቶች በሥራ ላይ ያውላል።

የከፍተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ኃላፊው ወይም ተወካዩ አንድ የማስፈራራትን ወይም የበቀልን ክስ ሙሉ በሙሉ ከመመርመሩ በፊት፣ አስፈላጊ ከነ የተጠቂ ተብዬው ደህንነት አደጋ ላይ መኑን ገምግሞ ሰላም ማምጣት እና/ወይም ተጠቂ ተብዬው ሌላ ነገር እንዳይደርስበት መከላከል ካለበት እርምጃ ይወስዳል። ደህንነትን ለመጠበቅ ከሚደረጉት ነገሮች ውስጥ የሚከተሉት የተወሰኑት ናቸው፡- የግል ደህንነት ዕቅድ መፍጠር፣ በክፍል ውስጥ፣ ምሳ ሰዓት ላይ ወይም አውቶቡስ ላይ ተጠቂው እና/ወይም አጥቂው የሚቀመጡባቸውን ቦታዎች አስቀድሞ መለየት፣ ተጠቂው ችግር ቢያጋጥመው የሚሄድበት "የደህንነት ሰው" መለየት፣ የአጥቂውን የጊዜ ሰሌዳና ተጠቂውን ማግኘት የሚችልበትን ሁኔታ መቀየር። የከፍተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ኃላፊው ወይም ተወካዩ በምርመራው ወቅትና ከዛም ባሻገር ደህንነትን ለመጠበቅ አስፈላጊ እርምጃዎች ካሉ እነሱን እርምጃዎች ይወስዳል።

አግባብ ያለው ባሕርይን ማስተማሪያ የተለያዩ አማራጮች አሉ፡- የግል ችሎታ ማጎልበቻ ክፍሎች፣ መልሶ አዳሽ አሠራሮችን ማሳየትና መጠቀም፣ ተማሪዎችን በግል ወይም በቡድን ተያያዥ ትምህርታዊ እንቅስቃሴዎች ውስጥ ከአማካሪዎች እና ከሌሎች ከሚመለከታቸው ሠራተኞች ጋር እየተመካከሩ ማሳተፍ፣ ተማሪዎች አዎንታዊ በነ ማህበራዊ መንገድ ግቦቻቸውን እንዴት ሊመቱ እንደሚችሉ መረዳት እንዲችሉ የተለያዩ ትምህርታዊ እና ትምህርታዊ ያልኑ የባሕርይ ዳጋፎች በሥራ ላይ ማዋል፣ ማስፈራራትን ማስወገጃ መንገዶች ለማጠናከርና ማህበራዊ ስልቶችን ማዳበሪያ እንቅስቃሴዎች በቤት ውስጥ የመሥራት ድጋፍ ለማግኘት ከወላጆች/አሳዳጊዎች/ተንከባካቢዎች ጋር መገናኘት፣ የተለዩ ማህበራዊ ችሎታዎች ለማጎልበት የባሕርይ ዕቅዶች መጀመር።

ማስፈራራት ውስጥ ተሳትፈው የተገኙ ተማሪዎች ላይ ከሚወሰዱት እርምጃዎች የሚከተሉትም ሊካተቱ ይችላሉ፡- አጥቂው ባሕርዩን እንዲያሻሽል ከአንድ የትምህርት ቤት ሠራተኛ ጋር አብሮ መሥራት፣ ለተማሪውና ለሚመለከታቸው የቤተሰቡ አባላት የአማካሪ ማየት ትእዛዝ ወይም የድጋፍ አገልግሎቶች ወይም የሕክምና እርዳታ፣ እስከ ፍርድ ቤት ሊያደርስ የሚችል ቅጣት ለተማሪው፣ ወይም በ*መብቶችና ኃላፊነቶች መመሪያ* መሠረት ከትምህርት ቤት ጋር የተያያዘ ቅጣት ማለትም ጊዜያዊ

ማስወጣትን፣ ማባረርን እና/ወይም ፍርድ ቤት መሄድን ጨምሮ። ማስፈራራት ውስጥ ተሳትፈው የተገኙ ሠራተኞች ቅጣት ሊደርስባቸው ይችላል፥ ማባረርን እና/ወይም ፍርድ ቤት መሄድን ጨምሮ።

ማስፈራራት ውስጥ ተሳትፈው የተገኙ ተማሪዎች በሙሉ በቀል የተከለከለ እንደነና የበቀል ድርጊቶች ቅጣት እንደሚያስከትሉ ይነገራቸዋል።

ተገቢ ያልነ ምግባር ተከስቷል ተብሎ ከተገመገመ CPS ምግባሩን ለማስወገድ ወዲያውኑ እርምጃ ይወስድና እንዳስፈላጊነቱ ማረሚያ እንዲደረግ ያደርጋል፣ ይህም ማለት አጥቂው ባሕርዩን እንዲያሻሽል ከአንድ የትምህርት ቤት ሠራተኛ ጋር አብሮ መሥራት፣ ለተማሪውና ለሚመለከታቸው የቤተሰቡ አባላት የአማካሪ ማየት ትእዛዝ ወይም የድጋፍ አገልግሎቶች ወይም የሕክምና እርዳታ እና/ወይም ቅጣት እንዳግባብነቱ ማስወጣትን፣ ማባረርን እና/ወይም ፍርድ ቤት መሄድን ጨምሮ። በተጨማሪም ማስፈራራት ወይም በቀል ተከስቷል ተብሎ ከተደመደመ፣ በስቴቱ ሕግ መሠረት የከፍተኛ ደረጃት ትምህርት ቤት ዋና ኃላፊ ከደህንነትና ጥበቃ ዳይሬክተር ጋር አብሮ በመተባበር የሚከተሉትን ያደርጋል፦ (1) የከፍተኛ ደረጃት ትምህርት ቤት ዋና ኃላፊ አጥቂው ላይ የወንጀል ክስ ይቀርብበታል ብሎ ካሰበ ያካባቢውን ሕግ አስከባሪ ድርጅት ማሳወቅ፣ (2) ተገቢውን የቅጣት እርምጃ መውሰድ፣ (3) የአጥቂውን ወላጆች/አሳዳጊዎች/ተንከባካቢዎች ማሳወቅ፣ እና (4) የተጠቂውን ወላጆች/አሳዳጊዎች/ተንከባካቢዎች ማሳወቅና የስቴቱና የፌዴራል ሕግ እስከሚፈቅደው ድረስ ተጨማሪ ማስፈራራት ወይም በቀል እንዳይከሰት የተወሰደውን እርምጃ ማሳወቅ። ከዚህም በላይ፣ አንድ ተማሪ አውቆ የውሸት የማስፈራራት ክስ ወይም የበቀል ክስ እንዳቀረበ ከታወቀ በ*መብቶችና ኃላፊነቶች መመሪያ* ውስጥ ባሉት አቅራቦቶች መሠረት ቅጣት ይደርስበታል፥ ይህም ተማሪውን ማባረር እና/ወይም ፍርድ ቤት መሂድን ሊያካትት ይችላል።

ለዒላማውና ለሌሎች ደህንነትን ማጠናከር

የማስፈራራት ዒላም ለነው ተማሪ ደህንነትን ዳግም ለማምጣትና ዒላማው ምን ዓይነት የደህንነት ጥበቃ እንደሚያስፈልገው ለመገምገም ከተማሪው፣ የተማሪው ወላጆች/አሳዳጊዎች/ተንከባካቢዎችና ከተገቢዎቹ የትምህርት ቤት ሠራተኞች ጋር (ማለትም ከትምህርት ቤት ተቆጣጣሪ፣ ከከፍተኛ ደረጃ ዋን ኃላፊ፣ ከረዳት ተቆጣጣሪ፣ ከተማሪዎች ጉዳይ ዋና ኃላፊ፣ ከደህንነት ባለሙያ እና/ወይም ከትምህርት ቤት ግልጋሎቶች ሹም ጋር) ስብሰባ ይደረጋል። የዚህ ስብሰባ ዓላማ ለተማሪው የደህንነት ጥበቃ የሚገን ዕቅድ ጉልበታና ሥራ ላይ መዋልንና ምንም ዓይነት ችግሮች ቢመጡ ተማሪው ሊነግረው የሚችለው ሠራተኛ ማን እንደሚገን ለመወያየት ነው። CPS እንዳስፈላጊነቱ አማካሪ ማየትን፣ የድጋፍ አገልግሎቶችን ወይም ሌሎች የሕክምና እርዳታዎችን ተማሪው እና የሚመለከታቸው የቤተሰብ አባላት እንዲያገኙ ሐሳብ ሊሰጥ ይችላል።

ማረሚያው እና/ወይም የቅጣት እርምጃው በተወሰነ አግባብ ባለው ጊዜ ውስጥ የከፍተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ኃላፊው ወይም ተወካዩ ዒላማውን ይገናኝና የተከለከለው ምግባር ዳግም መከሰቱንና ተጨማሪ የድጋፍ እርምጃዎች ያስፈልጉ እንደነ ይጠይቃል። የሚያስፈልግ ከነ የከፍተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ኃላፊው ወይም ተወካዩ ከተገቢው የትምህርት ቤት ሠራተኛ ጋር አብሮ ኖ ወዲያውኑ ሥራ ላይ

ማገጃ የፍርድ ቤት ትእዛዝ ካለ፣ የስብሰባው አንዱ ዓላማ የማገጃ ትእዛዙን ለመቃኘትና የማገቻ ትእዛዝ ጥሰት ቢከሰት የማሳወቂያ ሂደቶቹን ለማወቅ ነው። የማገጃ ትእዛዙ አንድ ተማሪ ወይም ሠራተኛ ላይ ከነ፣ ከዛ ግለሰብ ጋር ሌላ ስብሰባ ለብቻው ተደርጎ የማገጃ ትእዛዙን አብሮ ይቃኙና፣ ትእዛዙ ቢጣስ የሚከተሉት ውጤቶች ምን እንደኑ ውይይት ይደረጋል።

የውሸት ክስ/በቀል

አንድ ተማሪ አውቆ የውሸት ማስፈራራት ወይም የውሸት በቀል ክስ እንዳደረገ ከተደመደመ በ*መብቶችና ኃላፊነቶች መመሪያ* ውስጥ ባሉት አቅራቦቶች መሠረት ቅጣት ይደርስበታል።

ተማሪዎች ሁሉ በሕግ ሥር ያለው ሁኔታቸው ምንም ዓይነት ቢን አንድ ዓይነት ጥበቃ

በትምህርት ቤት ላይ የተመሠረቱ እርምጃዎች ክለሳ

የማስፈራራት ክሱን ያቀረበው ሰው፣ የማስፈራራት ተጠቂ ተብዬው እና/ወይም የማስፈራራት ተጠቂ ተብዬው ወላጆች/አሳዳጊዎች/ተንከባካቢዎች ከከፍተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ዋና ኃላፊ ጋር ተባብረው ከዚህ በላይ የተገለጹትን ኦፊሲዬላዊ ያልኑ መንገዶችን በቅንነት ተጠቅመው ለችግራቸው መፍትሄ ማግኘት ካልቻሉ በጽሑፍ የቀረበ አቤቱታ ለዋና ተቆጣጣሪው ወይም ለዋና ሥራ አስኪያጁ ሊላክ ይችላል። በጽሑፍ የሚቀርበው አቤቱታ ተጨባጭ ጉዳዮቹን ባጭሩ መግለጽና የሚፈለገው መፍትሄ ምን እንደነ መያዝ አለበት።

ዋና ተቆጣጣሪው ወይም ተወካዩ በጽሑፍ የቀረበው አቤቱታ በደረሰው በሰባት (7) ቀን ውስጥ ስለ ጉዳዩ ለመወያየት ቀንና ሰዓት ወስኖ ማስታወቂያ በፖስታ መላክ አለበት። ከስብሰባው በኋላ ዋና ተቆጣጣሪው ማስፈራራት ወይም ሌላ አግባብ የሌለው ምግባር ተከስቶ እንደነ፣ ማስፈራራቱ ወይም ሌላው አግባብ የሌለው ምግባር ዳግም እንዳይከሰት እስካሁን የተወሰደው እርምጃ ምን እንደነና ተጨማሪ የድጋፍ እርምጃዎች ያስፈልጉ እንደነ ይገመግማል። ስብሰባው በተካሄደ በአምስት (5) ቀን ውስጥ እነዚህን ጉዳዮችና ሌሎች ማናቸውም የትምህርት ቤት አውራጃው የሚወስዳቸው እርምጃዎች ካሉ እነሱን የያዘ ደብዳቤ ይላካል።

የማስፈራራት ክስ ያቀረበው ሰው፣ ዒላማ ተብዬው እና/ወይም የዒላማ ተብዬው ወላጆች/አሳዳጊዎች/ተንከባካቢዎች ከዋና ተቆጣጣሪው ወይም ከተወካዩ ጋር ከተሰበሰቡ በኋላ ለጉዳዩ መፍትሄ ማግኘት ካልቻሉ የግምገማ ጥያቄ የትምህርት ቤት ኮሚቴው ጋር መላክ ይቻላል። የትምህርት ቤት ኮሚቴው በራሱ ፈቃድ ምስክሮች የሚሉትን ማዳመጥ፣ ተጨማሪ ማስረጃ መቀበል እና የትምህርት ቤቱን ግኝቶችና ሐሳቦች መቃኘት እንዲሁም የዋና ተቆጣጣሪውን ወይም የተወካዩን ግኝቶችና ሐሳቦች መገምገም ይችላል። የትምህርት ቤት ኮሚቴው ግምገማውን ባደረገ በአምስት (5) ቀን ውስጥ የጽሑፍ ውሳኔ ያስተላልፋል፣ ይህም የዋና ተቆጣጣሪውን ግኝቶችና ሐሳቦች የሚደግፍ፣ የሚለውጥ ወይም የሚያሻሽልና ለተጠቀሱት ጉዳዮች መፍትሄ የሚኑ እርምጃዎች የትምህርት ቤት አውራጃው የሚወስድ ከነ እነሱንም ያካትታል።

ሌሎች የአቤቱታ ማቅረቢያ ሂደቶች

በዚህ ክፍል ውስጥ ከላይና በጸረ-አስፈራሪ ተማሪዎች ፖሊሲና የአስፈራሪ ተማሪዎች ማገጃና መፍትሄ ማምጫ ዕቅድ ውስጥ የተዘረዘሩት የሂደቶች አቅራቦቶች አንድ ተማሪን ማንኛውም ዓይነት የአድሎ ወይም በሕግ በተጠበቀት ልዩ ምልክቶች ማለትም በዘር፣ ቀለም፣ ዜግነት፣ ዘር ማንዘር፣ ኃይማኖት፣ ዕድሜ፣ አካል ብቃት፣ የሥነ ዘር መረጃ፣ ውትድርና ውስጥ በፊት በማገልገል፣ የጋብቻ ሁኔታ፣ ጾታ፣ መታወቂያ ጾታ፣ የጓደኛ ጾታ ምርጫ፣ ነፍሰ ጡርነት፣ ወይም ከነፍሰ ጡርነት ጋር የተያያዘ ሁኔታ ላይ የተመሠረተ አቤቱታ ካለው የኬምብሪጅ መንግሥት ትምህርት ቤቶችን "ጸረ-አድሎ ፖሊሲና ጾታዊ ጉትጎታ ክልከላ ፖሊሲ" ውስጥ ያለውን የአቤቱታ ሂደት ከመጠቀም አያግዱትም።

በተጨማሪም በ*መብቶችና ኃላፊነቶች መመሪያ* መሠረት የመብት መንፈግን በተመለከተ ያለ አቤቱታን ለመፍታት እዚህ ክፍል ላይ ያሉት አቅራቦቶች *የመብቶችና ኃላፊነቶች መመሪያ* ክፍል 23.0 ላይ ያለውን የአቤቱታ ሂደት ከመከተል አያግዱትም።

ከሌሎች ሕጎች ጋር ያለው ግንኙነት

በፌዴራልና በስቴት ሕጎችና ደንቦች መሠረት እንዲሁም በትምህርት ቤት አውራጃው ፖሊሲዎች መሠረት ማንም ሰው በዘር፣ ቀለም፣ ዜግነት፣ ዘር ማንዘር፣ ኃይማኖት፣ ዕድሜ፣ አካል ብቃት፣ የሥነ ዘር መረጃ፣ ውትድርና ውስጥ በፊት በማገልገል፣ የጋብቻ ሁኔታ፣ ጾታ፣ መታወቂያ ጾታ፣ የጓደኛ ጾታ ምርጫ፣ ነፍሰ ጡርነት፣ ወይም ከነፍሰ ጡርነት ጋር የተያያዘ ሁኔታ ምክንያት ማንኛውም ከተማ ውስጥ ያለ የመንግሥት ትምህርት ቤት ውስጥ ከመግባት ወይም ትምህርት ቤቱ ውስጥ ያሉትን መብቶች፣ ጥቅሞችና ትምህርቶች ከማግኘት አድሎ ሊደርስበት አይችልም።

አንድ ሰው በአካባቢው፣ በስቴት ወይም በፌዴራል ሕግ ከተጠበቁት ዘርፎች ውስጥ የአንዱ አባል ስለነ አድሎ ወይም ጉትጎታ ቢደርስበት አንድ ትምህርት ቤትን ወይም አንድ የትምህርት ቤት አውራጃን አድሎውን ለማስተካከል እርምጃ ከመውሰድ በዚህ ክፍል ውስጥም ነ በ*መብቶችና ኃላፊነቶች መመሪያ* ነ በጸረ-አስፈራሪ ተማሪዎች ፖሊሲና የአስፈራሪ ተማሪዎች ማገጃና መፍትሄ ማምጫ ዕቅድ ውስጥ የሚያግዱት ነገር የለም። በተጨማሪም በዚህ ክፍል ውስጥም ነ በ*መብቶችና ኃላፊነቶች መመሪያ* ውስጥም ነ በጸረ-አስፈራሪ ተማሪዎች ፖሊሲና የአስፈራሪ ተማሪዎች ማገጃና መፍትሄ ማምጫ ዕቅድ ውስጥ የአንድ ትምህርት ቤትን ወይም የትምህርት ቤት አውራጃን በ

M.G.L.c. 71፣ ክፍሎች 37H እና 37H ½ እና 37H ¾ እንዲሁም ሌሎች የሚመለከታቸው ሕጎች ወይም የአካባቢው ትምህርት ቤት ወይም የትምህርት ቤት አውራጃ ፖሊሲዎች መሠረት አሰቃቂ፣ ጎጂ ወይም ረብሻ የተሞላ ባሕርይ ቢኖር፣ ባሕርዩ በ*መብቶችና ኃላፊነቶች መመሪያ* ውስጥ፥ በጸረ-አስፈራሪ ተማሪዎች ፖሊሲና የአስፈራሪ ተማሪዎች ማገጃና መፍትሄ ማምጫ ዕቅድ ውስጥ ተጠቅሶ ቢንም ባይንም፣ የቅጣት እርምጃ መውሰጃ ሥልጣናቸውን የሚወስን ነገር የለም።

28. የጎረምሶች የፍቅር ጓደኝነት ጥቃት ፖሊሲ

CPS የፍቅር ጓደኝነት ጥቃትን በጭራሽ የሚቀበለው ነገር አይደለም። በዚህ አስተሳሰብ መሠረት፣ CPS ከፍቅር ጓደኝነት ጥቃት ነጻ የነ አካባቢ ለማጎልበት ቃል ገብቷል። ስለዚህም የኬምብሪጅ መንግሥት ትምህርት ቤቶች የጎረምሶች ፍቅር ጓኝነት ጥቃት ግንዛቤን ከፍ ለማድረግ ይጥራል፣ ለተጠቂዎችም ነ ለእንደዚህ ዓይነት ጥቃት ምስክር ለኑ ልጆችም የሚሰጠውን እርዳታ ከፍ ማድረግ ይሻል።

በማንኛውም ቦታ የሚከሰት የጎረምሶች ፍቅር ጓደኝነት ጥቃት ሕገወጥ ሲን በትምህርት ቤት ውስጥ ለሚከሰት የፍቅር ጓደኝነት ጥቃት ምንም ዓይነት ትእግስት አይኖርም። በተጨማሪም የጎረምሶች ፍቅር ጓደኝነት ጥቃት አቤቱታ ያቀረበ ግለሰብ ላይ ወይም የጎረምሶች ፍቅር ጓደኝነት ጥቃት ምርመራ ላይ የተባበረ ግለሰብ ላይ የሚደረግ አጸፋ ምላሽ በትዕግስት የምናሳልፈው አይንም። CPS የጎረምሶች ፍቅር ጓደኝነት ጥቃትና የበቀል አቤቱታና ማስታወቂያ ሲደርሰው ወዲያውኑ መልስ ይሰጥና አስፈላጊውን የቅጣት እርምጃ ይወስዳል።

በዚህ ፖሊሲ ውስጥ የተጠቀሟቸው ፍቺዎች እንደሚከተለው ናቸው:-

<u>የቤት ውስጥ ጥቃት/የርስ በርስ ጥቃት:-</u> የቤት ውስጥ ጥቃት ማለት በሁለት አብረው በሚኖሩ ሰዎች መካከል አንዱ ሌላውን የማስገደድ ባሕርይ በተደጋጋሚ ሲከሰት ነው፣ ማለትም አንዱ ሌላውን በማስፈራራት ወይም ከሚከተሉት መንገዶች አንዱን ተጠቅሞ ለመቆጣጠር ሲሞክር ነው:- በአካል፣ በግብረ ሥጋ ግንኙነት፣ በቃል፣ በገንዘብ፣ በስነ ልቦና ጥቃት እና/ወይም በቴክኖሎጂ (ማለትም የኢንተርኔት ማስፈራራት)።

የቤት ውስጥ ጥቃት በአገር ውስጥ ሁሉንም ማህበረሰብ፣ ዘር፣ ባህል ወይም ልምድ ሳይል ሁሉንም የሚመለከት ጉዳይ ነው። በማንኛውም ዕድሜ፣ ገቢ፣ ኃይማኖት፣ የጓደኛ ጾታ ምርጫ፣ ጾታ እና የትምህርት ደረጃ ያሉ ሰዎች የቤት ውስጥ ጥቃት፡ሊደርስባቸው ይችላል።

<u>የጎረምሶች የፍቅር ጓደኝንት ጥቃት:-</u> የፍቅር ጓደኝነት ጥቃት (ወይም የግንኙነት ጭቆና) ማለት ከልክ ባለፈ መንገድ የፍቅር ጓደኛን የመቆጣጠር ባሕርይ ነው። የፍቅር ጓደኝነት ጥቃት በብዙ መልክ ሊገለጽ ይችላል:- የአእምሮ/የስሜት ጭቆና፣ የአካል ጭቆናና የግብረ ሥጋ ግንኙነት ጭቆና እና/ወይም ቴክኖሎጂ መጠቀምን (ማለትም በኢንተርኔት ማስፍራራት) ያካትታል። አንድ ሰው የአካል ጭቆና ሳይደርስበት የፍቅር ጓደኝነት ጥቃት ሊደርስበት ይችላል። መደበኛ የፍቅር ጓደኝነት ውስጥም ዘለቄታዊ ግንኙነት ውስጥም ሊከሰት ይችላል።

<u>የልጅ ምስክር/ለቤት ውስጥ ጥቃት መጋለጥ:-</u> ጥቃትን ማየት የአንድ ልጅን ሕይወት ገጽታዎች በሙሉ፣ እድገትና መጎልበት ላይ ተጽዕኖ ሊያመጣ ይችላል። መጋለጥ ማለት ጥቃቱን ማየት ወይም መስማት፣የጥቃቱን ውጤቶች ማየት (የወላጆች/አሳዳጊዎች/ተንከባካቢዎች ቁስል ወይም የተሰበረ የቤት ዕቃ ወዘተ.) እና/ወይም ወላጆች/አሳዳጊዎች/ተንከባካቢዎችን ከጥቃት እከላከላለሁ ሲል መጎዳትን ሊያካትት ይችላል።

<u>የቤተሰብ ጥቃት:-</u> የቤተሰብ ጥቃት ማለት ሰፋ ያለ ትርጉም ሲኖረው የልጅ ጭቆናን፣ የአዛውንት ጭቆናን እና ሌሎች በቤተሰቦች መካከል የሚከሰቱ አስከፊ ድርጊቶችን ያካትታል።

<u>ተጠቂ/ተራፊ/ተደብዳቢ:-</u> የተጎዳውን፣ የተጨቆነውን ወይም የጥቃት ዛቻ የደረሰበትን ሰው፣ አካላዊ ጉዳት ቢኖርም ባይኖርም፣ ለመግለጽ የሚጠቅሙ ተለዋዋጭ ቃሎች።

ጨቋኝ/አጥቂ/ደብዳቢ:- ጭቆናውንና ጉዳት ያደረሰውን ሰው፣ አካላዊ ጉዳት ቢያስከትልም ባያስከትልም፣ ለመግለጽ የሚጠቅሙ ተለዋዋጭ ቃሎች።

በተጨማሪ እንደዚህ ዓይነቱ ምግባር እንደ ጉትጎታ ይቆጠራል፣ ይህም ከአድሎ ስለሚመደብ በፌዴራልና በስቴት ሕግ የተከለከለ ነው፣ እና/ወይም እንደዚህ ዓይነቱ ምግባር እንደ ማስፈራራት ተቆጥሮ ከኢንተርኔት ማስፈራራት ከተመደበ በስቴት ሕግ የተከለከለ ነው። የኬምብሪጅ መንግሥት ትምህርት ቤቶች ጸረ-አድሎ ፖሊሲና የጾታ ጉትጎታ፣ የኬምብሪጅ መንግሥት ትምህርት ቤቶች ጸረ-ጥቃት ፖሊሲና የኬምብሪጅ መንግሥት ትምህርት ቤቶች ጸረ-ማስፈራራት ፖሊሲ።

አሳሳቢ ምልክቶችን አስቀድሞ ማወቅ

የጨቋኝ ባሕርይ ምልክቶች የሚከተሉትን ይይዛሉ:- የተማሪው የፍቅር ጓደኛ ከሌሎች ጋር ለምን አወራ/አወራች ብሎ በጣም መቅናት፣ ሌላው ማድረግ ያለበትን ለመምራት መሞከር፣ አለመስማማት ሲኖር ከልክ በላይ ማጋነን፣ ሁልጊዜ የፍቅር ጓደኝነትን ለማቋረጥ ማስፈራራት፣ በአንደበት እራስን መቆጣጠር መሳን፣ የራስን ችግር ሌሎች ላይ ማላከክ፣ የፍቅር ጓደኛን በአካልም ነ   በስሜት መጉዳት ወይም የኢንተርኔት ማስፈራራት ድርጊቶች።

የተጠቂ ምልክቶች የሚከተሉትን ይይዛሉ:- በማይመስሉ ምክንያቶች ቀጠሮን ሁልጊዜ መሰረዝ፣ ሁልጊዜ የፍቅር ጓደኛን እንዳላስቆጣ ብሎ መጨነቅ፣ ለራስ አስፈላጊ የኑ   ነገሮችን መተው፣ የአካል ጉዳት ምልክቶች ማሳየት:- ለምሳሌ ጠባሳዎች ወይም ቁስሎች፣ የግብረ ሥጋ ግንኙነት ለማድረግ ተጽዕኖ ላይ መወደቅ ወይም ለግብረ ሥጋ ዓላማ ብቻ ለመጠቀም የመፈለግ ስሜት፣ በፈለገው/በፈለገችው ጊዜ ሁሉ እንዲገኝ/እንድትገኝ የሚፈልግ የፍቅር ጓደኛ እና ከቤተሰብና ከጓደኞች መገለል ወይም በኢንተርኔት ማስፈራራት እራስ ላይ ሲደርስ።

የፍቅር ጓደኝነት ጥቃትን ማሳወቂያ ሂደት

የፍቅር ጓደኝነት ጥቃት ተጠቂ ነኝ፣ የፍቅር ጓደኝነት ጥቃት ሊደርስብኝ ነው ብሎ የሚያምን ተማሪ ወይም የፍርድ ቤት ማገጃ ትእዛዝ ያለው ግለሰብ ጉዳዩን ከሚከተሉት ግለሰቦች ለአንዱ ማሳወቅ ይችላል:- (1) የከፍተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ዋና ኃላፊ፣ (2) ረዳት ተቆጣጣሪ፣ (3) የተማሪ ጉዳዮች ኃላፊ፣ (4) አስተማሪ ወይም (5) የትምህርት ቤት ነርስ።

ማሳወቂያ የደረሰው ግለሰብ ወዲያውኑ የከፍተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ዋና ኃላፊውን ማሳወቅ አለበት።

በተጨማሪም በትምህርት ቤት ቅጥር ግቢ ውስጥ ወይም ከትምህርት ቤት ጋር የተያያዘ ዝግጅት ላይ የጎረምሶች ፍቅር ጓደኝነት ጥቃት ያስተዋለ ማንኛውም ሠራተኛ ወዲያውኑ የከፍተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ዋና ኃላፊውን ማሳወቅ አለበት።

የከፍተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ዋና ኃላፊው ወዲያውኑ የሚከተለውን ማድረግ አለበት:- (1) የተጠቂውን ወላጆች/አሳዳጊዎች/ተንከባካቢዎች ማሳወቅ፣ እና (2) የደህንነትና ጥበቃ ቢሮን ማሳወቅ።

የከፍተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ዋና ኃላፊው ለተማሪው እና/ወይም ለተማሪው ወላጆች/አሳዳጊዎች/ተንከባካቢዎች ኦፊሲዬላዊ ባልነ መንገድ መፍትሄ ማግኛ ሂደቶችንና ኦፊሲዬላዊ አቤቱታዎችን ማስገቢያ ሂደቶች የያዘውን የ CPS ጸረ-አድሎ ፖሊሲና የጾታ ጉትጎታ ክልከላን እና የ CPS ጸረ-ማስፈራራት ፖሊሲ ያሳያል፣ የቅጂ ጥያቄ በቀረበለትም ጊዜ ቅጂ ይሰጣል።

የጎረምሶች የፍቅር ጓደኝነት ጥቃት ክስ በሚደርስ ጊዜ፣ ሁኔታው የተከሰተው በትምህርት ቤት ውስጥም ነ   ከትምህርት ቤት ውጪ፣ ከትምህርት ቤት ሲሄዱም ነ   ወደ ትምህርት ቤት ሲመጡ ወይም የትምህርት ቤት ዝግጅት ቦታ ላይ፣ ወይም በትምህርት ቤት ውስጥ በፍርድ ቤት የታዘዘ ማገጃ ከተጣሰ CPS ወዲያውኑ ለሚመለከታቸው ባለሥልጣኖችን ተከሰተ ስለተባለው ጉዳይ ያሳውቃል። እንደዚህ ዓይነት ክስተትን ሲያሳውቁ *ሁኔታው በሚፈቅደው መጠን ሁሉ* ምስጢራዊነቱ በተጠበቀ ሁኔታ ይናል።

የጎረምሶች የፍቅር ጓደኝነት ጥቃትን በተመለከተ የሶስተኛ አካል መረጃን በጥሞና መቀበል አስፈላጊ ነው። ባግባቡ ሥልጠና ያገኘ ሠራተኛ ስለተሰማው ጉዳይና ሊኖሩ ስለሚችሉ ችግሮች ለመወያየት ተማሪውን ቢያነጋግረው ይመረጣል። ጭቆና አለ ብሎ ተማሪው ካመነ አማካሪ የማየት፣ የድጋፍ ቡድኖችና የፖሊስ/የፍርድ ቤት እርዳታ የሚገኙበትን መንገድ ከማካፈል በተጨማሪ "የደህንነት ዕቅድ" ማጎልበት ይስፈልጋል።

በተጨማሪም ተከስቷል ተብሎ የሚጠረጠር ጭቆናና ከፍተኛ ቸልተኝነት ካለ የትምህርት ቤት ሠራተኞች በሕግና ደንቦች መሠረት ማሳወቅ እናደለባቸው ማስታወስ አለባቸው (ማሳወቂያ 51A)። 51A አቤቱታዎችን ሲያስገቡ የ CPS የልጅ ጭቆናና ከፍተኛ ቸልተኝነት ማሳወቂያ መመሪያዎችን ውስጥ ባለው መስፈርት መሠረት መን   አለበት፣ እንዲሁም የከፍተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ዋና ኃላፊን ስለ ጭቆናውና ስለ ከፍተኛ ቸልተኝነቱ ማሳወቅ ያስፈልጋል። በተጨማሪም የትምህርት ቤት ሠራተኞች ለፖሊስ ማሳወቅ ማስታወስ አለባቸው። ሠራተኞች የከፍተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ዋና ኃላፊን ያሳውቃሉ፣ እሱ የደህንነትና ጥበቃ ሹሙን ያሳውቃል፣ እሱ ደግሞ ለፖሊስ የማሳወቅ ሂደቱን ያቀነባብራል። እንደዚህ ዓይነት ሁኔታ ሲያሳውቁ *ሁኔታው እስከሚፈቅደው ድረስ* የመረጃውን ምስጢራዊነት በጠበቀ መንገድ መን   አለበት።

የፍርድ ቤት ማገጃ ትእዛዝ ሲሰጠው ትምህርት ቤቱ የሚከተላቸው ሂደቶች

አንድ ተማሪ ሌላ ግለሰብ ላይ የፍርድ ቤት ማገጃ ትእዛዝ ሲኖረውና የትእዛዙን ቅጂ ለትምህርት ቤቱ ሲሰጥ፣ የከፍተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ዋና ኃላፊ ከሠራተኛው ወይም ከተማሪውና ከተማሪው ወላጆች/አስዳጊዎች/ተንከባካቢዎች ጋር ስብሰባ አድርጎ የፍርድ ቤት ማገጃ ትእዛዙንና በውስጥ ያሉትን ዝርዝሮች መቃኘት አለበት። ተጠቂው የሚያስፈልጉትንና የሚያሳስቡትን ነገሮች የሚያመቻች "የደህንነት ዕቅድ" መጎልበት አለበት፣ ይህም ተማሪው ወይም ሠራተኛው በትምህርት ቤት ወይም በትምህርት ቤት ዝግጅት ላይ ሳለ ችግር ቢፈጠር ወይም የፍርድ ቤት ማገጃ ትእዛዙ ቢጣስ ተማሪው ሊያሳውቀው የሚገባው ሠራተኛን መለየትን ማካተት አለበት። የፍርድ ቤት ማገጃ ትእዛዙ ሌላ የትምህርት ቤት

ማህበረሰብ አባል ላይ ከነ፣ የፍርድ ቤት ማገጃውን ትእዛዝ ዝርዝሮችን፣ ከግለሰቡ የሚጠበቁ ነገሮችንና ትእዛዙ ቢጣስ ምን እንደሚደርስ ለመቃኘት ከዛ ግለሰብ ጋር ሌላ ስብሰባ ይደረጋል። "የደህንነት ዕቅዱ" ሥራ ላይ የሚውለው ሁኔታዎች በፈቀዱ መጠን የጉዳዩን ምስጢራዊነት በጠበቀ መንገድ ይናል።

የቅጣት እርምጃ

አግባብ የሌለው ምግባር ተከስቷል ተብሎ ከተገመገመ CPS እንድሁኔታው ይህን እርምጃ ይወስዳል። እርምጃው ከአማካሪ ማየት እና/ወይም ቅጣት እስከ ሌጊዜው ከትምህርት ቤት ማስወጣት ወይም ማባረር ሊን ይችላል።

ሌሎች መፍትሄዎች

ትምህርት ቤት ውስጥ፣ ከትምህርት ቤት ወይም ወደ ትምህርት ቤት ሲሄዱ ወይም የትምህርት ቤት ዝግጅት ላይ የሚከሰትን የጎረምሶች የፍቅር ጓደኝነት ጥቃት ከማሳወቅ በተጨማሪ ከላይ በተጠቀሱት ሂደቶች መሠረት የጎረምሶች የፍቅር ጓደኝነት ጥቃት ደርሶብኛል ብለው የሚያምኑ ተማሪዎች የጉትጎታ እና/ወይም የማስፈራራት ክስ በ CPS ጸረ-አድሎ ፖሊሲና የጾታ ጉትጎታ ክልከላ ሂደት መሠረት እና/ወይም በኬምብሪጅ ትምህርት ቤቶች ጸረ-ማስፈራራት ፖሊሲ መሠረት ማስገባት ይችላሉ። በተጨማሪም ከትምህርት ቤት ውጪ እና/ወይም ከትምህርት ሰዓት ውጪ የጎረምሶች የፍቅር ጓደኝነት ጥቃት ተጠቂ ነኝ ብለው የሚያምኑ ተማሪዎች ክሱን ለፖሊስ ማሳወቅ ይችላሉ።

አደጋ ላይ ነኝ ብለው የሚያምኑ ተማሪዎች እራሳቸውን ከጉዳት ወይም ከዛቻ ለመከላከል ባካባቢው በሚገኘው ፍርድ ቤት ውስጥ ማመልከቻ አስገብተው የማገጃ ትእዛዝ መጠየቅ ይችላሉ።

የቅጣት ሂደቶች (የሕግ ሂደት)

የቅጣት ሂደቶች በ*መብቶችና ኃላፊነቶች መመሪያ* ውስጥ ይገኛሉ። እነዚህ ሂደቶች ባጭሩ እንደሚከተለው ናቸው:-

29. ጊዜያዊ ማባረር

በ CPS መምሪያ መሠረት ተማሪዎች የምግባር ችግር ሲያጋጥማቸው ከፍተኛ የቅጣት እርምጃ ከመወሰዱ በፊት ችግሩን በሌላ መንገድ ለመፍታት መሞከር አለበት። ከትምህርት ቤት ለጊዜው ማስወጣት የሚታየው እንደ መጨረሻ አማራጭ ነው። ስለዚህ አንድ ተማሪ ትምህርትና ጥሩ ምግባር እንዲኖረው ለማበረታታት የትምህርት ቤት ተቆጣጣሪዎች/የከፍተኛ ትምህርት ቤቶች ዋና ኃላፊዎች ወይም ተወካዮች የጊዜያዊ ማስወጣት እርምጃ ከመውሰዳቸው በፊት ሌሎች አግባብ ያላቸውን የቅጣት እርምጃዎች ሁሉ መጀመሪያ መሞከር አለባቸው። ኖም የተማሪው ባሕርይ ትምህርት ቤቱ የሚረብሽ ከነ፣ ለራሱ ወይም ለሌሎች ጎጂ ከነ ወይም የCommonwealth of Massachusettsን (የማሳቹሴትስ መንግሥት) ሕጎች የሚጥስ የተከለከለ እንቅስቃሴ ከፈጸመ ጊዜያዊ ማባረር ሊያስፈልግ ይችላል።

የተማሪው ጊዜያዊ መባረር የሚካሄደው በተቆጣጣሪው/የከፍተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ዋና ኃላፊው ነው። የጊዜያዊ ማባረር ውሳኔ ከመወሰኑ በፊት ከተለመደው ውጪ የነ ልዩ ሁኔታ ካለ ከግምት ይገባል።በይበልጥ መረጃ ለማግኘት *የመብቶችና ኃላፊነቶች መመሪያውን* ይመልከቱ።

በትምህርት ቤት ሕንጻ ውስጥ፥ በትምህርት ቤት ቅጥር ግቢ ውስጥ ወይም ከቤት ወደ ትምህርት ቤት በሚጓጓዝበት ጊዜ ወይም በተፈቀደ የትምህርት ቤት ዝግጅት ላይ በትምህርት ቤት ውስጥም ነ ውጪ አንድ ተማሪ የትምህርት ቤት ደንብ ከተላለፈ ተቆጣጣሪው/የከፍተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ዋና ኃላፊው ከአንድ እስከ አሥር ቀን ድረስ ከትምህርት ቤት ሊያስወጣው ይችላል። *የመብቶችና ኃላፊነቶች መመሪያ* ውስጥ ያሉትን የምግባር ደንቦች ወይም የትምህርት ቤት ደንብ የጣሰ ተማሪ እንደ ከስተቱ ክብደት ከአንድ እስከ አሥር ቀን ድረስ ከትምህርት ቤት እንዲወጣ ሊደረግ ይችላል። ማስወጣት ሊያስከትሉ የሚችሉ ምግባሮች:-

- ጥቃትን፣ ኃይልን፣ ማስገደድን፣ ዛቻን፣ ማስፈራራትን ወይም ሌላ ተመሳሳይ ምግባር መጠቀም፥
- ማንኛውንም የትምህርት ቤት ሕንጻ ወይም ንብረት ላይ እሳት መለኮስ ወይም ንብረት ማጥፋት፥
- የእሳት ወይም የፖሊስ ድንገተኛ መውጫ በር እንደሌለ እያወቁ የትምህርት ቤት የሚመስል ደወል መደወል፥
- ከዚህ በፊት መሣሪያ ይዞ ከነበረ ወይም ይዞ ከተገኘ፥
- በቁጥጥር ሥር ያለ ዕጽ ወይም አልኮል መጠጥ ይዞ ወይም ተጠቅሞ ቢገኝ፥
- በከፍተኛ ወንጀል ተከሶ ተፈርዶበት ትምህርት ቤት መቆየቱ ለትምህርት ቤቱ አጠቃላይ ደህንነት አስጊ ነው ብሎ ከተደመደመ፥
- ማንኛውንም የትምህርት ቤት ወይም ትምህርታዊ ዝግጅትን ወይም ማንኛውንም ትምህርት ቤት ውስጥ የሚደረግ ሕጋዊ ስብሰባን በአካል ማከላከል ወይ በአካል ለማከላከል መሞከር።
- ትምህርት ቤት ውስጥ ኖ የሌላ ሰውን ንብረት ማጥፋት ወይም መስረቅ ወይም የተሰረቀ የግል ንብረት ይዞ መገኘት፥
- የትምህርት ቤት ንብረት ላይ ጉዳት ማድረስ ወይም ጉዳት ለማድረስ መሞከር፥ ወይም የትምህርት ቤት ንብረት መስረቅ ወይም ለመስረቅ ሙከራ ማድረግ፥
- ማንኛውም ተማሪ ላይ አውቆ አካላዊ ጉዳት ማድረስ ወይም አካላዊ ጉዳት ለማድረስ ሙከራ ማድረግ፥
- ማንኛውንም በሥልጣኑ የሚንቀሳቀስ የትምህርት ቤት ሠራተኛ የሚሰጠውን መመሪያ ባለመከተል የሌሎች ትምህርት ሂደት ላይ ረብሻ መፍጠር፥
- ዛቻ፣ ጉትጎታ ወይም ማስገደድን ተጠቅሞ የትምህርት ቤት ሠራተኛን ካስቸገረ ወይም ከሞከረ ወይም ማንኛውንም የትምህርት ቤት እንቅስቃሴ ኃይልን ወይም ጥቃትን ተጠቅሞም ሳይጠቀምም መረበሽ፥
- የማሳቹሴትስ መንግሥት ሕግ የትምህርት ቤት እንቅስቃሴ የሚረብሽ ድርጊት ነው ብሎ በሚከለክለው ድርጊት ላይ ተካፋይ መን ፥
- *የመብቶችና ኃላፊነቶች መመሪያ* ውስጥ ያሉትን ደንቦችና ኃላፊነቶች በተደጋጋሚ አውቆ የሚተላለፍ ድርጊት ማስደረግ ወይም ማድረግ፥
- የማዋረጃ እንቅስቃሴዎችን የሚከለክለውን የማሳቹሴትስ ሕግን የሚጥስ እንቅስቃሴ ተካፋይ ኖ መገኘት (G.L. c. 269, §§17-19)፥

- በትምህርት ቤት ውስጥ ወይም በትምህርት ቤት እንቅስቃሴ ላይ ወይም ከትምህርት ቤት ቅጥር ግቢ ውጪ ኖ ማንም ሰው ላይ መዛት፣ መጎትጎት ወይም ማስፈራራት፥
- M.G.L.c. 71, ክፍል37H እና/ወይም 37H½ን የሚጥስ ምግባር ተካፋይ መን ፥ እና/ወይም
- የትምህርት ቤት ደንቦችን ወይም *የመብቶና ኃላፊነቶች መመሪያን* የሚጥስ ሌላ ማንኛውም ምግባር ማካሄድ።

አንድ ተማሪ ለጊዜ እንዲወጣ በተደረገ ጊዜ በትምህት ቤት አካባቢ መገኘት አይችልም፥ እንዲሁም ማንኛውም የትምህርት ቤት እንቅስቃሴ ወይም ዝግጅት ላይ መሳተፍ አይችልም። እነዚህን መስፈርቶች አለማክበር ተቆጣጣሪው/የከፍተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ዋና ኃላፊው የመባረሩን ጊዜ እንዲያራዝመው ሊያስደርግ ይችላል።

30. ማባረር

የCPS ፖሊሲ ተማሪዎች ሁሉ ደህንነቱ በተጠበቀ አካባቢ ውስጥ እንዲማሩና መርሃ ግብሮች ውስጥ መሳተፍ እንዲችሉ ማድረግ ነው።

ኖም የአንድ ተማሪ ባሕርይ ለሌሎች ተማሪዎች ወይም ለትምህርት ቤት ሠራተኞች አስጊ ሊንበት የሚችልበት ሁኔታ ሊፈጠር ስለሚችል ተማሪውን ማባረር አስፈላጊ ኖ ሊገኝ ይችላል።

በማሳቹሴትስ አጠቃላይ ሕጎች አንቀጽ 71፥ ክፍል 37H መሠረት ተቆጣጣሪ/የከፍተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ዋና ኃላፊ አንድ ተማሪ አደገኛ መሣሪያ፥ በቁጥጥር ሥር ያለ ዕጽ ይዞ ስለተገኘ ወይም የትምህርት ቤት ሠራተኛ ላይ ድብደባ ስለፈጸመ ማባረር ወይም ለጊዜው ማስወጣት ይችላል።

በማሳቹሴትስ አጠቃላይ ሕጎች አንቀጽ 71፥ ክፍል 37H ½ መሠረት ተቆጣጣሪው/የከፍተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ዋና ኃላፊው በከፍተኛ ወንጀል የተከሰሰ ተማሪን ጊዜው ላልተወሰነ ጊዜ ሊያስወጣና ትምህርት ቤት መቆየቱ ለትምህርት ቤቱ አጠቃላይ ደህንነት አስጊ የነን በከፍተኛ ወንጀል የተከሰሰ ተማሪን ሊያባርር ይችላል።

የማባረር ይግባኝ ሂደት፡- ከይግባኙ በኋላ ተቆጣጣሪው/የከፍተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ዋና ኃላፊው ተማሪውን በ M.G.L. c. 37H ሥር ጥሰት ስላለው ለማባረር ከወሰነ፥ ይግባኙ ከተደረገበት ቀን ጀምሮ እስከ አሥር ቀን ውስጥ ዋና ተቆጣጣሪውን ስለ ይግባኙ ማሳወቅ ይችላል። የይግባኙ ርእስ ተማሪው በዚህ ክፍል ውስጥ ጥሰቶች እንዳሉት በተጨባጭ ለመገምገም ብቻ አይንም። ከይግባኙ በኋላ ተቆጣጣሪው/የከፍተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ዋና ኃላፊው ተማሪውን በ M.G.L. c. 71፥ ክፍል 37H ½፥ ሥር ጥሰት ስላለው ለማባረር ወይም ላልተወሰነ ጊዜ ለማስወጣት ከወሰነ፥ ይግባኙ ከተደረገበት ቀን ጀምሮ እስከ አምስት ቀን ውስጥ ዋና ተቆጣጣሪውን ስለ ይግባኙ ማሳወቅ ይችላል። ይግባኙ ላይ ውሳኔ እስከሚተላለፍ ድረስ ተማሪው ከትምህርት ቤት ውጪ መቆየት አለበት። ዋና ተቆጣጣሪው ወይም ተወካዩ ፊት ተማሪው ጠበቃ የመያዝ መብት አለው። ዋና ተቆጣጣሪው ወይም ተወካዩ ይግባኙ ላይ የተወሰደውን ውሳኔ ለወላጅ/አሳዳጊ/ተቆጣጣሪ በጽሑፍ ያሳውቃል። በይበልጥ መረጃ ለማግኘት *የመብቶችና ኃላፊነቶች መመሪያን* ይመልከቱ።

31. የተማሪ ፍተሻዎችና ምርመራ

የትምህርት ቤት ደህንነት ጥበቃ ተማሪን መፈተሽና መመርመር በተመለከተ የኬምብሪጅ ትምህርት ቤት ኮሚቴ ያለው ፖሊሲ እንደሚመለከተው ነው፡-

ከአጸደ ሕጻናት እስከ 8ኛ ክፍል፡- የተማሪ ፍተሻ ከመደረጉ በፊትና የትምህርት ቤት ደህንነት ጥበቃ ወይም ከትምህርት ቤት ውጪ የነ ሠራተኛ ጥያቄያዊ ምርመራ ለተማሪው ከማቅረቡ በፊት የከፍተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ዋና ኃላፊ፣ ረዳት ተቆጣጣሪ ወይም የከፍተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ዋና ኃላፊ ተወካይ ፈቃድ መስጠት አለበት።

ከ9ኛ እስከ 12ኛ ክፍል፡- ዋና ተቆጣጣሪው፣ ረዳት ተቆጣጣሪው፣ የተማሪዎች ኃላፊ ወይም የዋና ተቆጣጣሪው ተወካይ የትምህርት ቤት ደህንነት ጥበቃ ለሚያደርጋቸው ፍተሻዎች አስቀድሞ ፈቃድ መስጠት አለበት።

ሁሉም ክፍሎች (ከአጸደ ሕጻናት እስከ 12ኛ ክፍል)፡- ሁኔታው የሚፈቅድ ከነ የከፍተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ዋና ኃላፊ፣ ረዳት ተቆጣጣሪ፣ የተማሪዎች ጉዳይ ኃላፊ ወይም የከፍተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ዋና ኃላፊ ተወካይ ወደ ትምህርት ቤቱ እና/ወይም ወደ አነስተኛ መማሪያ ማህበረሰብ ጋር የሚላከው የደህንነት ጥበቃ የትኛው እንደነ ጥያቄ ማቅረብ ይችላል።

ከአጸደ ሕጻናት እስከ 8ኛ ክፍል፡- ተማሪዎች ፍተሻ በሚደረግባቸው ወቅት ወይም የትምህርት ቤት ደህንነት ጥበቃ ወይም ከትምህርት ቤት ውጪ የነ ሠራተኛ ጥያቄያዊ ምርመራ ለተማሪዎች በሚያደርግበት ወቅት የከፍተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ዋና ኃላፊ፣ ረዳት ተቆጣጣሪ ወይም የከፍተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ዋና ኃላፊ ተወካይ መገኘት አለበት።

ከ9ኛ እስከ 12ኛ ክፍል፡- ተማሪዎች ፍተሻ በሚደረግባቸው ወቅት ወይም የትምህርት ቤት ደህንነት ጥበቃ ወይም ከትምህርት ቤት ውጪ የነ ሠራተኛ ጥያቄያዊ ምርመራ ለተማሪዎች በሚያደርግበት ወቅት የከፍተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ዋና ኃላፊ፣ ረዳት ተቆጣጣሪ፣ የተማሪዎች ጉዳይ ኃላፊ ወይም የከፍተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ዋና ኃላፊ ተወካይ መገኘት አለበት።

ከአጸደ ሕጻናት እስከ 8ኛ ክፍል፡- ተማሪዎች በትምህርት ቤት ደህንነት ጥበቃ ጥያቄያዊ ምርመራ በሚደረግላቸው ወቅት በተቻለ መጠን ጾታው ከተማሪው ጋር አንድ ዓይነት የነ ግለሰብ አብሮ መገኘት አለበት። የትምህርት ቤት ደህንነት ጥበቃ ተማሪዎች ላይ የሚያደርጋቸው ፍተሻዎች ሁሉ የሚመሩት ከተማሪው ጋር አንድ ዓይነት ጾታ ያለው ግለሰብ መን አለበት።

ከ9ኛ እስከ 12ኛ ክፍል፡- የትምህርት ቤት ደህንነት ጥበቃ ተማሪዎች ላይ የሚያደርጋቸው ፍተሻዎች ሁሉ የሚመሩት ከተማሪው ጋር አንድ ዓይነት ጾታ ያለው ግለሰብ መን አለበት።

ከአጸደ ሕጻናት እስከ 8ኛ ክፍል፡- የትምህርት ቤት ደህንነት ጥበቃ ፍተሻ ከማድረጉ በፊት የከፍተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ዋና ኃላፊ፣ ረዳት ተቆጣጣሪ ወይም የከፍተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ዋና ኃላፊ ተወካይ ወላጆች/አሳዳጊዎች/ተንከባካቢዎችን አስቀድሞ ማሳወቅ አለበት። አስቀድሞ ማሳወቅ ካልተቻለ ወላጆች/አሳዳጊዎች/ተንከባካቢዎች ከፍተሻው በኋላ በተቻለ መጠን በፍጥነት እንዲያውቁ ይደረጋል፣ የዛንኑ ቀን ደብዳቤም ይላክላቸዋል።

ከ9ኛ እስከ 12ኛ ክፍል፡- የትምህርት ቤት ደህንነት ጥበቃ ፍተሻ እንዳደረገ የከፍተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ዋና ኃላፊ፣ ረዳት ተቆጣጣሪ ወይም የከፍተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ዋና ኃላፊ ተወካይ ወላጆች/አሳዳጊዎች/ተንከባካቢዎችን ወዲያው ማሳወቅ አለበት። በተጨማሪ፣ የዛንኑ ቀን ደብዳቤ ይላክላቸዋል።

ከአጸደ ሕጻናት እስከ 8ኛ ክፍል፦ የትምህርት ቤት ደህንነት ጥበቃ ለተማሪው ጥያቄያዊ ምርመራ ከማድረጉ በፊት የከፍተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ዋና ኃላፊ፣ ረዳት ተቆጣጣሪ ወይም የከፍተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ዋና ኃላፊ ተወካይ ወላጆች/አሳዳጊዎች/ተንከባካቢዎችን ወይም የድንገተኛ ተጠሪውን አስቀድሞ ማሳወቅ አለበት። አስቀድሞ ማሳወቅ ካልተቻለ ወላጆች/አሳዳጊዎች/ተንከባካቢዎች ከምርመራው በኋላ በተቻለ መጠን በፍጥነት እንዲያውቁ ይደረጋል፣ የዛንኑ ቀንም ደብዳቤም ይላክላቸዋል።

ልብ ይበሉ፦ የድንገተኛ ተጠሪ ማለት ቅጣት ነክ ጉዳይ ሲያጋጥም፣ ጥያቄያዊ ምርመራን ወይም ፍተሻዎችን ጨምሮ ኃላፊነት ወስዶ ምላሽ እንዲሰጥ ወላጅ/አሳዳጊ/ተንከባካቢ የሰየመው ግለሰብ ነው። በየትምህርት ዓመቱ ወላጅ/አሳዳጊ/ተንከባካቢ ቅጣት ነክ ጉዳይ ሲያጋጥም፣ ጥያቄያዊ ምርመራን ወይም ፍተሻዎችን ጨምሮ በድንገተኛ ጊዜ ተጠሪ የሚን ግለሰብ እንዲሰይሙ ይጠየቃሉ፣ ይህም ግለሰብ ቅጣት ነክ ጉዳይ፣ ጥያቄያዊ ምርመራ ወይም ፍተሻዎችን በተመለከተ በወላፍ/አሳዳጊ/ተንከባካቢ ምትክ እሱ እስከፈቀደው መጠን ድረስ እርምጃ ይወስዳል።

ሁሉም ክፍሎች (ከአጸደ ሕጻናት እስከ 12ኛ ክፍል)፦ ሁኔታው የሚፈቅድ ከነ ተቆጣጣሪው/የከፍተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ዋና ኃላፊ፣ ረዳት ተቆጣጣሪ፣ የቤት አስተዳዳሪ ወይም ተወካዩ ተማሪዎች በትምህርት ቤት ደህንነት ጠባቂ ከመፈተሻቸው ወይም ቃለ ምልልስ ከማድረጋቸው በፊት ስላላቸው መብቶች ማሳወቅ አለበት።

ከ9ኛ እስከ 12ኛ ክፍል፦ የትምህርት ቤት ደህንነት ጥበቃ ለአንድ ተማሪ ጥያቄያዊ ምርመራ ሲያደርግ ወላጅ/አሳዳጊ/ተንከባካቢን የማሳወቅ ግዴታ የለበትም።

የትምህርት ቤት ደህንነት ጥበቃ አስቀድሞ ከዋና ተቆጣጣሪው ፈቃድ ሳያገኝ በራሱ ምርመራ አይጀምርም።

ልብ ይበሉ፦ የግል ምርመራ ማለት የተማሪዎችን እና/ወይም የሠራተኞችን ደህንነት የሚመለከት በአንድ ክስተት ብቻ ያልተወሰነ ቀጣይነት ያለው የአስጊ ዛቻ ምርመራ ነው። ምርመራው የሚመለከተው አንድ ወይም ከዛ በላይ የኑ ትምህርት ቤቶችን ወይም በአውራጃው ውስጥ ያሉ የCRLS ትምህርት ቤቶችን መን አለበት።

32. የተማሪ ቅሬታ ሂደት

ተማሪው ወይም ወላጅ/አሳዳጊ/ተንከባካቢ በ*መብቶችና ኃላፊነቶች መመሪያ* ውስጥ ያሉ የተማሪ መብቶች በአንድ የትምህርት ቤት መምሪያ ሠራተኛ ተጥሰዋል ብለው ካመኑና ሁሉም በቀና ልብ የተሞከሩ መፍትሄዎች ካልተሳኩ፥ ተማሪው ወይም ወላጅ/አሳዳጊ/ተንከባካቢ ዋና ተቆጣጣሪው ጋር በጽሑፍ አቤቱታ ማቅረብ ይችላሉ። በጽሑፍ የቀረበው አቤቱታ ቅሬታውን፥ የተከለከለውን መብት በግልጽ፥ የጭብጥ ነጥቦች መግለጫና የተፈለገውን መፍትሄ መግለጽ አለበት። ዋና ተቆጣጣሪው ቅሬታውን ለከሳሽ አጥጋቢ በነ ሁኔታ ቅሬታው በደረሰው በሰባት የትምህርት ቀን ውስጥ መፍታት ካልቻለ፥ ለሁለቱም ወገኖች ማስታወቂያ ይልካል።

ማስታወቂያው የሚከተሉትን የያዘ ይናል፦

- አቤቱታው ከደረሰ በኋላ በአሥር ቀን ውስጥ ስብሰባ የሚደረግበትን ሰዓትና ቦታ፥ ኖም ሁለቱም ወገኖች ለይግባኙ ለመዘጋጀት ተጨማር አምስት የትምህርት ቀኖች ይኖሯቸዋል፥ ቅሬታው በጽሑፍ የቀረበው አቤቱታ ውስጥ መደበኛ በነ ሁኔታ ተገልጾ፥
- የጭብጥ ጉዳዮችን ሙሉ መግለጫ፥ ስሞችና ምስክሮችን ጨምሮ፥
- የተፈለገው መፍትሄ መግለጫ እና፥
- የሁሉም ወገኖች መብቶች መግለጫ፥ ወገኖች ሁሉ ስብሰባው ላይ ጠበቃ ወይም ሌላ ሰው እንዲወክላቸው መብት እንዳላቸው እንዲሁም ምስክሮችና ማስረጃ የማምጣትና ተቃራኒ ምስክሮችን የመመርመር መብት እንዳላቸው የሚገልጽ መግለጫ።

ስብሰባው የሚከተሉትን መመሪያዎች መከተል አለበት፦

- በዋና ተቆጣጣሪው ወይም በተወካዩ ፊት መካሄድ አለበት፥
- በዝግ ሁኔታና መደበኛ ባልነ ሁኔታ የሚመራ፥
- ሁሉም ወገኖች በጠበቃ ወይም በሌላ በመረጡት ሰው የመወከል መብት አላቸው፥
- ሁሉም ወገኖች የትምህርት ቤት መዝገቦችንና ከአቤቱታው ጋር የተያያዙ ሰነዶችን የመመርመር መብት አላቸው፥ እና
- ሁሉም ወገኖች ምስክሮችን ጥያቄ የመጠየቅና ምስክሮችና ማስረጃ የማቅረብ መብት አላቸው።

ዋና ተቆጣጣሪው ወይም ተወካዩ የተማሪው መብቶች ተጥሰዋል ብሎ ከገመገመ ተገቢውን መፍትሄ መወሰን ይችላል።

33. የትርፍ ሰዓት እንቅስቃሴዎች ውስጥ ተሳትፎ

የCPS አስተዳደርና የደህንነትና ጥበቃ መምሪያ የተመልካቾችንና ተሳታፊዎችን ደህንነት ስጋት ላይ የሚጥል ሰው የትርፍ ሰዓት እንቅስቃሴዎች ውስጥ እንዳይሳተፍ የመከልከል መብት አላቸው።

ከሚከተሉት ምድቦች ውስጥ የሚገቡ ተማሪዎች ከስፖርት፥ ድራማ፥ ሙዚቃ፥ ዳንስ፥ የመጨረሻ ዳንስ፥ ትምህርታዊ ጉዞና ሌሎች ተመልካች ካላቸው ዝግጅቶች ይታገዳሉ፦

- ከትምህርት ቤት ለጊዜው እንዲወጡ የተደረጉ ተማሪዎች፥
- የተባረሩ የቀድሞ ተማሪዎች፥ እና/ወይም
- በቅጣት ምክንያት አማራጭ መርሃ ግብር ውስጥ የተመዘገቡ ተማሪዎች።

ማንኛውም ከላይ የተጠቀሱት ምድቦች ውስጥ ያለ ባሕርዩ ለመግባት ድጋሚ እንዲታይለት የሚፈልግ ተማሪ ለተቆጣጣሪው/የከፍተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ዋና ኃላፊ፥ ረዳት ተቆጣጣሪ ወይም የተማሪ ጉዳዮች ኃላፊ ጥያቄ ማቅረብ አለበት። ተማሪው የትርፍ ሰዓት እንቅስቃሴ ውስጥ እንዲገባ ፈቃድ ለማግኘት በደህንነት ዳይሬክተርና በተቆጣጣሪው/የከፍተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ዋና ኃላፊው ወይም ረዳት ተቆጣጣሪው ወይም የተማሪ ጉዳዮች ኃላፊ መሃል ስምምነት መኖር አለበት።

በተጨማሪም CPS የሚከተሉትን የማህበረሰብ አባላት ከስፖርት፥ ድራማ፥ ሙዚቃ፥ ዳንስ፥ የመጨረሻ ዳንስ፥ ትምህርታዊ ጉዞና ሌሎች ተመልካች ካላቸው ዝግጅቶች የማገድ መብት አለው፦

- ከማህበረሰቡ ጋር ከፍተኛ ክስተት ላይ የተሳተፉ፥
- የአመጽ ታሪክ ያላቸው፥ እና/ወይም

• ሠራተኞችን የረበሸ ወይም ለሠራተኞች አክብሮት የሌለው።

መብቶችና ልዩ ጥቅሞች

34. ተማሪዎች ላይ ጸረ-አድሎ

የማሳቹሴትስ አጠቃላይ ሕጎች አንቀጽ 76፥ ክፍል 5 የሚከተለውን አቅራቦት ይዟል፡- “[ማንንም] ሰው በማንኛውም ከተማ ውስጥ የመንግሥት ትምህርት ቤት ውስጥ ከመግባት ወይም የመንግሥት ትምህርት ቤት ውስጥ ከመማር የሚመጡትን ልዩ ጥቅሞች ከመጠቀም በዘር፥ ቀለም፥ ጾታ፥ ኃይማኖት፥ ብሔር፥ መታወቂያ ጾታ፣ የጓደኛ ጾታ ምርጫ ላይ ተመሥርቶ መከልከል አይቻልም።”

CPS ተማሪዎች ሁሉ ሊማሩበትና ከትምህርት ቤት ጋር የተያያዙ እንቅስቃሴዎች ውስጥ መሳተፍ የሚችሉበት ሁኔታ ለማቅረብ ተግቶ ይሠራል። አካላዊ ቅጣት በማንኛውም መልኩ የተከለከለ ነው። በተጨማሪም ምንም ዓይነት የሌሎችን ክብር የሚሳደብ፥ የሌሎች የመማር ነጻነት ላይ ጣልቃ የሚገባ ወይም የጥላቻ የትምህርት አካባቢ የሚፈጥር ባሕርይ ተቀባይነት የለውም፥ የቅጣት እርምጃም ያስከትላል። እንዲሁም ምንም ዓይነት የተማሪዎች ማስፈራራት፥ ማዋረድ፥ ማንቋሸሽ ወይም ሌላ የበቀል ምግባር ተቀባይነት የለውም፥ የቅጣት እርምጃም ያስከትላል። የትምህርት ቤት ሠራተኞች እንደዚህ ዓይነት ምግባርን ለባለሥልጣኖች ተማሪዎች ወይም ወላጆች/አሳዳጊዎች/ተንከባካቢዎች ከማሳወቅ እንቅፋት አይኑባቸውም። እንደዚህ ዓይነት እንቅፋትነት ወዲያውኑ ለዋና ተቆጣጣሪ መዘገብ አለበት።

ከዚህ በታች የ CPSን የተለያዩ ጸረ-አድሎ ፖሊሲዎች አጭር መግለጫ ያገኛሉ።

35. አግባብ ያለው ማመቻቸት ፖሊሲና ሂደት

CPS ትምህርት ቤት መቀበል ላይ፥ መስተንግዶ ላይ ወይም ለመርሃ ግብሮቹ ወይም እንቅስቃሴዎቹ መግቢያ እና/ወይም ቅጥር ላይ አድሎ አያደርግም። የታወቀ የአካል ወይም የአእምሮ ጉዳት ላላቸው ተማሪዎች CPS አግባብ ያለው ማመቻቸት የማድረግ ፖሊሲ አለው። ለክፍል 504 የተማሪ አቅራቦቶች የተማሪው ትምህርት ቤት ውስጥ የሚገኘው የ504 አስተባባሪ ጋር በቀጥታ ጥያቄ ማቅረብ ይቻላል። የትምህርት ቤት አውራጃው የ504 አስተባባሪ የተማሪ አገልግሎቶች ረዳት ተቆጣጣሪ ነው፡- Cambridge Public Schools, 159 Thorndike Street, Cambridge, MA 02141፥ 617-349-6500።

36. በ1973 ዓ.ም. የተሃድሶ ሕግ ክፍል 504 ሥር ያለ የመብቶች ማስታወቂያ

እነዚህ መብቶች የሚመለከቱት ወላጆች/አሳዳጊዎች/ተንከባካቢዎችና ዕድሜያቸው ለአቅመ አዳም/ሔዋን የደረሱ ማለትም በማሳቹሴትስ ሕግ መሠረት 18 (አሥራ ስምንት) ዓመት የናቸውን ሲን እንደሚከተለው ናቸው፡-

1. የትምህርት ቤት አውራጃው ሲለይ፥ ሲገመግም፥ አልገመግምም ሲል፥ አዲስ ትምህርታዊ ምደባ ሲያደርግ፥ አዲስ ትምህርታዊ ምደባ አላደርግም ሲል ወይም የተማሪው ምደባ ላይ በተማሪው አካል/አእምሮ ጉዳት ምክንያት ወይም የአካል/አእምሮ ጉዳት አለው ተብሎ ስለሚጠረጠር ከፍተኛ የምደባ ለውጥ ሲደረግ ወላጅ/አሳዳጊ/ተንከባካቢ ወይም ዕድሜው ለአቅመ አዳም/ሔዋን የደረሰ ተማሪ የሥርዓታዊ መብቶች ማስታወቂያ ቅጂ የማግኘት መብት አላቸው።
2. ወላጅ/አሳዳጊ/ተንከባካቢ ወይም ዕድሜው ለአቅመ አዳም/ሔዋን የደረሰ ተማሪ፥ የትምህርት ቤት አውራጃው የተማሪውን የመማር ችሎታ ወይም የሌላ የሕይወት እንቅስቃሴ በከፍተኛ ሁኔታ የሚገድብ የአእምሮ ወይም የአካል ጉዳት አለው ብሎ ካመነ ለተማሪው ግምገማ የማስደረግ መብት አለው። ወላጅ/አሳዳጊ/ተንከባካቢ ወይም ዕድሜው ለአቅመ አዳም/ሔዋን የደረሰ ተማሪ ይህን ግምገማ የማስደረግ መብት ያለው ምንም ዓይነት የማመቻቸት ዕቅድ ከመውጣቱ በፊትና የልጁ ትምህርታዊ ምደባ ላይ ምንም ዓይነት ለውጥ ከመደረጉ በፊት ነው። የትምህርታዊ ምደባ ላይ ከፍተኛ ለውጥ አንድ ምሳሌ ለማባረር መጠቀም ነው።
3. ተማሪው በነጻ አግባብ ያለው የመንግሥት ትምህርት የማግኘት መብት አለው። ወላጅ/አሳዳጊ/ተንከባካቢ የአካል/የአእምሮ ጉዳት የሌለባቸው ልጆች ወላጆች/ተንከባካቢዎች/አሳዳጊዎች ያለባቸውን ዓይነት አንድ ዓይነት ወጪ ያክል ኃላፊነት አለበት።
4. እስከ ጫፍ ድረስ ተማሪው የአካል/የአእምሮ ጉዳት ከሌለባቸው ልጆች ጋር አብሮ የመማር መብት አለው።
5. ወላጅ/አሳዳጊ/ተንከባካቢ ወይም ዕድሜው ቢያንስ አሥራ አራት ዓመት የነው ወይም ዘጠነኛ ክፍል የገባ ተማሪ ትምህርት ቤቱ ተማሪውን በተመለከተ የሚይዘውን አግባብ ያለው መዝገብ ሁሉ የመመርመር መብት አለው።
6. በተሃድሶ ሕግ ክፍል 504 መሠረት የተማሪውን መታወቂያ፥ ግምገማ ወይም ምደባ በተመለከተ የኬምብሪጅ መንግሥት ትምህርት ቤቶች የወሰደውን እርምጃ መቃወም ቢፈልጉ ወላጅ/አሳዳጊ/ተንከባካቢ ወይም ዕድሜው ለአቅመ አዳም/ሔዋን የደረሰ ተማሪ ትክክለኛ ይግባኝ የማግኘት መብት አላቸው።
7. የክፍል 504 Team የወሰደውን እርምጃ በተመለከተ ወላጅ/አሳዳጊ/ተንከባካቢ ወይም ዕድሜው ለአቅመ አዳም/ሔዋን የደረሰ ተማሪ የይግባኝ ሂደት ተጠቅሞ መቃወም ቢፈልግ የይግባኝ ጥያቄ ለ Bureau of Special Education Appeals (BSEA), One Congress Street, 11th Floor, Boston, MA 02114 ማስገባት ወይም በፋክስ በቁጥር 617-626-7270 ለBSEA አለበት። ይህ በጽሑፍ የሚገባ ጥያቄ ለትምህርት ቤቶች ዋና ተቆጣጣሪም በሚከተለው አድራሻ Superintendent of Schools, Cambridge Public Schools, 159 Thorndike Street, Cambridge, MA 02141 መግባት አለበት። ወላጅ/አሳዳጊ/ተንከባካቢ ወይም ዕድሜው ለአቅመ አዳም/ሔዋን የደረሰ ተማሪ በመጨረሻ የይግባኙ ሹሙ በሰጠው ውሳኔ ካልተስማሙ የፌዴራል አውራጃ ፍርድ ቤቱ ጋር አቤቱታ በማስገባት ጉዳዩ በድጋሚ እንዲታይላቸው መጠየቅ ይችላሉ።

8. ወላጅ/አሳዳጊ/ተንከባካቢ ወይም ዕድሜው ለአቅመ አዳም/ሔዋን የደረሰ ተማሪ ከመታወቂያ፥ ግምገማ ወይም ከምደባ ጋር ያልተያያዙ ሌሎች ችግሮች ካሏቸው፥ የተማሪ አገልግሎቶች ረዳት ዋና ተቆጣጣሪ ለነው ለትምህርት ቤት አውራጃው ክፍል 504 አስተባባሪ ክስ ወይም አቤቱታ ማቅረብ ይችላሉ። ቢሮው የሚገኘው አንደኛ ፎቅ ላይ በ 159 Thorndike Street, Cambridge, Massachusetts አድራሻ ነው። የተማሪ አገልግሎቶች ቢሮ ስልክ 617-349-6500 ነው።

9. ወላጅ/አሳዳጊ/ተንከባካቢ ወይም ዕድሜው ለአቅመ አዳም/ሔዋን የደረሰ ተማሪ የአሜሪካ ሕዝብ መብቶች ትምህርት መምሪያ ጋር በሚከተለው አድራሻ አቤቱታ የማስገባት መብትም አላቸው Office of Civil Rights of the United States Department of Education, 5 Post Office Square, 8th Floor, Boston, MA 02109-3921 ስልክ፡- 617-289-0111፥ ፋክስ፡- 617-289-0150; መስማት ለሚሳናቸው፡- 1-800-877-8339፥ ኢሜል፡- OCR.Boston@ed.gov.

37. ልዩ ትምህርት

በፌዴራልና በስቴት ሕግ መሠረት ተማሪዎች ሁሉ ምንም ዓይነት የአካል ወይም የአእምሮ ጉዳት ቢኖርባቸው፥ የነጻና አግባብ ያለው የመንግሥት ትምህርት የማግኘት መብት አላቸው። ልጅዎ ልዩ ትምህርት ያስፈልገዋል ብለው የሚያምኑ ከነ ልጅዎ ተገቢዎቹን አገልግሎቶች ለማግኘት መስፈርቶች ያሟላ እንደነ ለማየት ለልጅዎ ግምገማ እንዲደረግ የመጠየቅ መብት አልዎት። አንድ ሠራተኛ የአንድ ተማሪ ትምህርታዊ እና/ወይም ማህበራዊ ባሕርይ ካሳሰበው፥ ያሳሰቡትን ጉዳዮች ለተቆጣጣሪው/ለከፍተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ዋና ኃላፊ ማቅረብ አለበት፥ እሱም በተራው የአስቀድሞ ደራሽ እና/ወይም የትምህርታዊ ድጋፍ ቡድን ሂደት ማስጀመር ይችላል።

38. IEP እና 504 ዕቅዶች ያሏቸው ተማሪዎች

ልዩ ትምህርት የሚያገኙ ወይም 504 ዕቅዶች ያሏቸው ተማሪዎች *የመብቶችና ኃላፊነቶች መመሪያ* አቅራቦቶች ይመለከቷቸዋል። በፌዴራልና በስቴት ሕጎች ፍቺ መሠረት 504 ዕቅዶች ያሏቸው የአካል ወይም የአእምሮ ጉዳት ያላቸው ተማሪዎች በክፍል 18 ውስጥ በተጠቀሱት ሁኔታዎች ካልነ በስተቀር የዚህ *የመብቶችና ኃላፊነቶች መመሪያ* አቅራቦቶች ይመለከታቸዋል። በፌዴራልና ስቴት ሕጎችና ደንቦች ፍቺ መሠረት የአካል/የአእምሮ ጉዳት ያላቸውና የ 504 ዕቅድ ያላቸው ተማሪዎች በ*መብቶችና ኃላፊነቶች መመሪያ* ክፍል 18 ውስጥ ካሉት አቅራቦቶች በስተቀር በ*መብቶችና ኃላፊነቶች መመሪያ* አቅራቦቶች ሥር ይተዳደራሉ። IEPዎችና 504 ዕቅዶች ተማሪው በ*መብቶችና ኃላፊነቶች መመሪያ* ውስጥ ያሉትን መደበኛ የሥርዓት ምግባሮች መከተል ይችል እንደነ ወይም የተማሪው ሁኔታ ልዩ የሥርዓት ደንቦች ያስፈልጉት እንደነ ይገልጻሉ። የተማሪው የአካል/የአእምሮ ጉዳት ባሕርዩ ላይ ተጽዕኖ ካለው በ IEPው እና/ወይም በ504 Team ሂደት የሚስተናገድ ይናል። በ*መብቶችና ኃላፊነቶች መመሪያ* መሠረት አስተዳደራዊ ውሳኔ ከማድረግ በተጨማሪ፣ የከፍተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ዋና ኃላፊው (ወይም ተወካዩ) የተማሪ አገልግሎቶች ቢሮን (ወይም ተወካዩን) የአካል ወይም የአእምሮ ጉዳት ያለውና የተማሪው IEP እና/ወይም 504 ዕቅድ መመሪያው ውስጥ ያሉት የቅጣት ደንቦች ወይም የትምህርት ቤቱ ደንቦች ማሻሻያ እንደሚያስፈልጋቸው የሚያሳይ ከነ የተማሪውን ጥፋት ያሳውቃል፣ እንዲሁም የማስወጣት ማስታወቂያ ግልባጭ ለተማሪ አገልግሎቶች ቢሮ ይላካል። የተማሪ አገልግሎቶች ቢሮ ሠራተኞች የአካል ወይም የአእምሮ ጉዳት ያላቸውን ተማሪዎች በተመለከተ በ*መብቶችና ኃላፊነቶች መመሪያ ሥር* ባሉ በሁሉም አስተዳደራዊ ውሳኔዎች ውስጥ ተሳታፊ ይናሉ። በ*መብቶችና ኃላፊነቶች መመሪያ ሥር* ያለ አስተዳደራዊ ውሳኔ የተማሪ ምደባ ላይ ተጽዕኖ ከሌለው እና/ወይም በአንድ ትምህርት ዓመት ውስጥ ተማሪው በአጠቃላይ ከአሥር (10) ቀን በላይ እንዲወጣ ካልተደረገ የ TEAM ስብሰባ አስፈላጊ አይደለም። በ*መብቶችና ኃላፊነቶች መመሪያ ሥር* ያለ አስተዳደራዊ ውሳኔ የተማሪ ምደባ ላይ ተጽዕኖ ካለው እና/ወይም በአንድ ትምህርት ዓመት ውስጥ ተማሪው በአጠቃላይ ከአሥር (10) ቀን በላይ እንዲወጣ ከተደረገ፣ ቅጣትን በተመለከተ ምንም ዓይነት አስተዳደራዊ ውሳኔ ከመደረጉ በፊት የTEAM ስብሰባ መደረግ አለበት። በ*መብቶችና ኃላፊነቶች መመሪያ ሥር* አስተዳደራዊ ውሳኔ ከመደረጉ በፊት ተማሪው የአካል ወይም የአእምሮ ጉዳት አለበት ተብሎ መሰየሙን ወይም ልዩ ትምህርት ያስፈልገው እንደነ ለመገምገም ተልኮ ግን ገና ብቃት እንዳለው አለመወሰኑን የከፍተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ዋና ኃላፊ መገምገም አለበት። አንድ ልዩ ትምህርትና ተያያዥ አገልግሎቶች ለማግኘት ብቃት እንዳለው ገና ግምገማ ያልተደረገለት የምግባር ወይም ሌላ ድንብ የጣሰ ተማሪ፣ የቅጣት እርምጃ ያስከተለውን ጥፋት ከማጥፋቱ በፊት ትምህርት ቤቱ የአካል ወይም የአእምሮ ጉዳት ያለበት ተማሪ መኑን የማያውቅ ከነበረ በስቴቱና በፌዴራል የልዩ ትምህርት ሕጎች የቀረቡ ጥበቃዎችን መጠቀም ይችላል።

የቅጣት እርምጃውን ያስከተለው ጥፋት ከመከሰቱ በፊት የሚከተለው ከተከሰተ የትምህርት ቤት መምሪያው ተማሪው የአካል ወይም የአእምሮ ጉዳት እንዳለው ዕውቀት ነበረው ተብሎ ይታሰባል፡-

- ወላጅ/አሳዳጊ/ተንከባካቢ ለተቆጣጣሪዎች ወይም ለአስተዳደር ሥራተኞች ወይም ለልጁ አስተማሪ ልጁ ልዩ ትምህርትና ተያያዥ አገልግሎቶች እንደሚያስፈልጉት በጽሑፍ ሐሳባቸውን አካፍለው ነበር፣ ወይም
- ወላጅ/አሳዳጊ/ተንከባካቢ ተማሪው ግምገማ እንዲደረግለት ጥያቄ አቅረበው ነበር፣ ወይም
- ተማሪው ስላሳየው ባሕርይ ሐሳብ ይዟቸው የተማሪው አስተማሪ ወይም ሌላ የትምህርት ቤት ሠራተኛ በቀጥታ ለተማሪ አገልግሎቶች ቢሮ ወይም የተማሪ አገልግሎቶች ቢሮ ውስጥ ላለ ተቆጣጣሪ ሠራተኛ አሳውቀው ነበር።

የትምህርት ቤት መምሪያው ተማሪው የአካል ወይም የአእምሮ ጉዳት እንዳለው ዕውቀት አልነበረውም ተብሎ የሚታሰበው የሚከተለው ከተከሰተ ነው፡-

- ወላጅ/አሳዳጊ/ተንከባካቢ ተማሪው ግምገማ እንዲደረግለት አልፈቀደም፣ ወይም
- ወላጅ/አሳዳጊ/ተንከባካቢ ለተማሪው አገልግሎቶች አልቀበልም ብሎ እምቢ ብሏል፣ ወይም
- ተማሪው ግምገማ ተደርጎለት ልዩ ትምህርትና ተያያዥ አገልግሎቶች ለማግኘት ብቃት የለውም ተብሎ ተወስኗል።

የትምህርት ቤት መምሪያው ተማሪው የአካል ወይም የአእምሮ ጉዳተኛ እንደነ ዕውቀት አልነበረውም ተብሎ ከተገመተ፣ ከሚከተሉት ገደቦች በስተቀር ተማሪው ላይ *በመብቶችና ኃላፊነቶች መመሪያ* ውስጥ ባለው የቅጣት ድንብ መሠረት የቅጣት እርምጃ ሊወሰድበት ይችላል፡-

- ተማሪው ቅጣት ላይ ባለ ጊዜ የተማሪው ወላጆች/አሳዳጊዎች/ተንከባካቢዎች ግምገማ እንዲደረግለት ከጠየቁ ግምገማው በተፋጠነ መልኩ መካሄድ አለበት፣ እና

- ግምገማው እስከሚገባደድ ድረስ ተማሪው የትምህርት ቤት ሥልጣናት በመደቡለት የትምህርት ምደባ ውስጥ ይቆያል።

በመብቶችና ኃላፊነቶች መመሪያ ሥር አንድ አስተዳደራዊ ውሳኔ የተማሪው ምደባ ላይ ተጽዕኖ ካመጣ እና/ወይም በአንድ የትምህርት ዓመት ውስጥ ባጠቃላይ ከአሥር(10) ቀን በላይ የሚያስወጣው ከነ እና/ወይም ውጤቱ እስከመጨረሻው መባረር ከነ የሚቀጥሉት አቅራቦቶች ሥራ ላይ ይውላሉ:-

የተማሪው ጥፋት የአካል ወይም የአእምሮ ጉዳቱ መገለጫው መኑን ለመገምገም ትምህርት ቤቱ፣ የተማሪው ወላጆች/አሳዳጊዎች/ተንከባካቢዎችና ሌሎች የሚመለከታቸው የተማሪው Team የመገለጫ ግምገማ ያደርጋሉ። Team ይህንን ግምገማ ሲያደርግ የሚከተሉትን ከግምት አስገብቶ ነው:- (ሀ) ምግባሩ የተከሰተው በቀጥታ በልጁ የአካል ወይም የአእምሮ ጉዳት ምክንያት ወይም ከልዩ የአካል ወይም የአእምሮ ጉዳት ጋር በተያያዘ መኑን፣ ወይም (ለ) ምግባሩ የተከሰተው የተማሪው IEP እና/ወይም 504 ዕቅድ በሥራ ላይ ያለመዋሉ ቀጥተኛ ውጤት መኑን። እንደ መገለጫው ግምገማ ውጤት ታይቶ፣ የቀረበው ይቅጣት እርምጃ ሥራ ላይ ሊውልም ላይውልም ይችላል። የተማሪው ምግባር የአካል ወይም የአእምሮ ጉዳቱ መገለጫው ነው ብሎ Team ከገመገመ፣ የተማሪው ባሕርይ ነክ የመፍትሄ ዕቅድ ምደባውን መለወጥ ኖ ወላጆች/አሳዳጊዎች/ተንከባካቢዎችና የትምህርት ቤት አውራጃው ምደባውን ለመቀየር ካልተስማሙ በስተቀር ተማሪው ከወጣበት ምድብ ይመለሳል። በተጨማሪም IEP እና/ወይም 504 ዕቅድ ውስጥ፣ ምደባ ላይ ወይም ሥራ ማዋል ላይ የተገኙ ጉድለቶችን ለማረም Team በስቴትና ፌዴራል ሕጎች መሠረት ፈጣን እርምጃ ይወስዳል፣ የመገለጫ ግምገማ ቡድን ስብሰባ እንዲደረግ መንስኤ የነው ምግባር ከመከሰቱ በፊት ለተማሪው ተግባራዊ የባሕርይ ግምገማ ያልተደረገ ከነ ይህ እርምጃ ተግባራዊ የባሕርይ ግምገማን ያካትታል፣ እንዲሁም የባሕርይ መፍትሄ ዕቅድ በሥራ ላይ ማዋል ወይም ተማሪው ነባር የባህርይ መፍትሄ ዕቅድ ካለው እሱን ቃኝቶ ማሻሻል ያስፈልጋል።

የተማሪው ምግባር የአካል ወይም የአእምሮ ጉዳቱ መገለጫው አይደለም ብሎ Team ከገመገመ:-

- ተማሪው ወጥቶ እንዳለ አግባብ ያለው የመንግሥት ትምህርት በነጻ የሚያገኝበትን ዕቅድ Team ያጎለብታል፣

- አማራጭ ዕቅዱንና በስቴትና በፌዴራል ደንቦችና ሕጎች መሠረት የሚያስፈልገውን የጽሑፍ ማስታወቂያ Team ለወላጆች/አሳዳጊዎች/ተንከባካቢዎች ያቀርባል። ወላጆች/አሳዳጊዎች/ተንከባካቢዎች በአማራጭ ዕቅድ ሥር የቀረቡትን አገልግሎቶች ለመቀበል አንስማማም ቢሉ ማስወጣቱን ሥራ ላይ ከማዋል አያግድም።

የተማሪው ወላጆች/አሳዳጊዎች/ተንከባካቢዎች በ Massachusetts Department of Education Bureau of Special Education Appeals (የማሳቹሴትስ ትምህርት መምሪያ የልዩ ትምህርት ይግባኝ ቢሮ) ፊት ቀርበው ይግባኝ እንዲካሄድላቸው አቤቱታ ካስገቡ፣ ትምህርት ቤቱ *በመብቶችና ኃላፊነቶች መመሪያ* መሠረት ባደረገው አስተዳደራዊ ውሳኔ መሠረት፣ ቅጣቱ እስከሚያበቃ ድረስ ወይም የይግባኝ ሹም የተማሪውን ምደባ እስከሚቀይረው ድረስ ተማሪው ጊዜያዊ አማራጭ የትምህርት ምደባ ውስጥ ይቀጥላል።

የምደባ ለውጥ በሚደረግበት ጊዜ ወይም ከትምህርት ቤት ለአሥር (10) ቀን ወይም ከዛ በላይ ተማሪው በሚወጣበት ጊዜ ሁሉ ተማሪው አግባብ ያለው ነጻ የመንግሥት ትምህርት እንዲቀርብለት ይደረጋል። የምግባር ደንብ የጣሰ ተማሪን ምደባ ለመቀየር በሚወስኑበት ጊዜ የትምህርት ቤት ሠራተኞች ማናቸውንም ልዩ ሁኔታዎች በግል ይቃኛሉ።

የቅጣት እርምጃውን ሥራ ላይ ለማዋል አስተዳደራዊ ውሳኔ በተደረገ በአሥር (10) ቀን ውስጥ የሚከተለው መከሰት አለበት:-

- Team ተሰብስቦ ለተማሪው ተግባራዊ የባሕርይ ግምገማ ማድረግ አለበት፣ ይህ የሚነው አስቀድሞ የተደረገ ግምገማ ከሌለ ነው፣

- Team የተማሪውን የባሕርይ መፍትሄ ዕቅድ ሥራ ላይ ማዋል አለበት፣ ቅጣት ያስከተለው ባሕርይ ከመከሰቱ በፊት እንደዚህ ዓይነት ዕቅድ ሥራ ላይ ውሎ ካልነበረ፣ ወይም

- ቅጣት ያስከተለው ባሕርይ ከመከሰቱ በፊት ተማሪው የባሕርይ መፍትሄ ዕቅድ ከነበረው Team ዕቅዱን ዳግም ቃኝቶ ማሻሻል አለበት።

- ወላጅ/አሳዳጊ/ተንከባካቢ ፈቃድ ቢሰጥም ባይሰጥም፣ ከአርባ አምስት (45) የትምህርት ቀን ላልበለጠ ጊዜና አግባብ ያለው የነጻ መንግሥት ትምህርት ከሚከተሉት ሁኔታዎች ውስጥ ባንዱ ወይም በብዙው ላይ እስከቀረበ ድረስ Team ምደባውን ወደ ጊዜያዊ አማራጭ የትምህርት ሁኔታ መቀየር አለበት ብሎ ሊገመግም ይችላል:-

- ተማሪው ትምህርት ቤት ወይም ትምህርት ቤቱ ያዘጋጀው ዝግጅት ላይ መሳሪያ ይዞ ከሄደ፣

- አንድ ተማሪ በትምህርት ቤት ውስጥ ወይም ትምህርት ቤት ባዘጋጀው ዝግጅት ላይ አውቆ ሕገወጥ ዕጽ እና/ወይም በቁጥጥር ሥር ያሉ ዕጾች ይዞ ቢመጣ፣ ቢጠቀም፣ ቢሸጥ ወይም ቢጠይቅ፣

- አንድ ተማሪ በትምህርት ቤት ውስጥ፣ በትምህርት ቤት ቅጥር ግቢ ውስጥ:ወይም የትምህርት ቤት ዝግጅት ላይ ሌላ ሰው ላይ ከፍተኛ የሰውነት ጉዳት ቢያስከትል። "ከፍተኛ የሰውነት ጉዳት" ማለት ለሞት የሚዳርግ፣ ከፍተኛ ሕመም የሚያስከትል፣ ግልጽ የነ የሰውነት ክፍል ላይ ወይም አእምሮ ላይ ከባድ ጉዳት የሚያደርስ በሚል ልዩ ፍቺ ይሰጠዋል።

ተማሪው በወቅቱ ያለበት ምደባ ተማሪውን ወይም ሌሎችን ጉዳት ላይ የመጣል ዕድሉ ከፍተኛ ነው ብሎ ትምህርት ቤቱ ከገመገመ፣ ተማሪው እስከ አርባ አምስት (45) ቀን ድረስ ከትምህርት ቤት ወጥቶ ወደ ጊዜያዊ አማራጭ የትምህርት ሁኔታ እንዲሸጋገር የሚያደርግ ትእዛዝ ከ Massachusetts Department of Education Bureau of Special Education Appeals (የማሳቹሴትስ ትምህርት መምሪያ የልዩ ትምህርት ይግባኝ ቢሮ) ሊጠይቅ ይችላል።

39. Affirmative Action (አድሎ ማስወገጃ ሕግ)/ጸረ-አድሎ ማስታወቂያ

CPS በአሠራሮቹ በሙሉ፥ በትምህርቱም በቅጥሩም ዕድሎች አኳያ እኩል ዕድል ለመስጠት ተግቶ ይሠራል። መርሃ ግብሮቹና እንቅስቃሴዎቹ ውስጥ ወይም በመቀበል ላይ ወይም ቅጥር ላይ በዘር፣ ቀለም፣ ዜግነት፣ ዘር ማንዘር፣ ኃይማኖት፣ ዕድሜ፣ አካል ብቃት፣ የሥነ ዘር መረጃ፣ ውትድርና ውስጥ በፊት በማገልገል፣ የጋብቻ ሁኔታ፣ ጾታ፣ መታወቂያ ጾታ፣ የጓደኛ ጾታ ምርጫ፣ ነፍሰ

ጡርነት፣ ወይም ከነፍሰ ጡርነት ጋር የተያያዘ ሁኔታ ላይ የተመሠረተ አድሎ ይከለክላል እርሱም አያደርግም። CPS Boy Scouts (የወንዶች ቡድን) ውስጥና ሌሎች የተመደቡ የወጣት ቡድኖች ውስጥ ለመሳተፍ ፌዴራል ሕግ በሚያስገድደው መሠረት እኩል ዕድል ይሰጣል። ጸረ አድሎ ፖሊሲዎችን በተመለከተ ጥያቄ ካለ የሚከተለው የተመደበን ሰው ይገናኙ፡- Director of Diversity Development (የሕብራዊነት ጉልበታ ዳይሬክተር), 159 Thorndike Street, Cambridge, MA 02141፥ 617-349-6457።

ጸረ-አድሎን በተመለከተ ተጨማሪ መረጃ ለማግኘት Office of Civil Rights of the United States Department of Education (የአሜሪካ ትምህርት መምሪያ ማህበራዊ መብት ቢሮ ይገናኙ)፡- 5 Post Office Square, 8th Floor, Boston, MA 02109 ስልክ፡- 617-289-0111፥ ፋክስ፡- 617-289-0150።

40. የቤት አልባ ትምህርት አገናኝ

CPS ቤት አልባ ልጆችና ሸኚ የሌላቸው ወጣቶች እንደ ሌሎች የኬምብሪጅ ልጆች እኩል የመንግሥት ትምህርት እንዲያገኙ ተግቶ ይሠራል። ቤት አልባ ልጆችና ሸኚ የሌላቸው ወጣቶች ጋር የተያያዙ ችግሮችን በተመለከተ እርዳታ ለማግኘት Homeless Education Liaison for the Cambridge Public Schools (ለኬምብሪጅ መንግሥት ትምህርት ቤቶች የቤት አልባ ትምህርት አገናኝ) ን ይገናኙ። የቤት አልባ ትምህርት አገናኝ በ Title I ቢሮ ውስጥ በሚከተለው አድራሻ ይገኛል፡- 159 Thorndike Street, Cambridge, MA 02141። ስልክ ቁጥሩ 617-349-6487 ነው።

41. የመሰብሰብ ነጻነት

ተማሪዎች በትምህርት ቤት ቅጥር ግቢ ውስጥ በነጻነትና ሰላማዊ በነ   መንገድ የመሰብሰብ ነጻነት አለቸው፥ ሐሳባቸውንና አመለካከታቸውን መግለጽም ይችላሉ። ተማሪዎች የስብሰባ ዕቅድ ሲኖራቸው አስቀድመው ከተቆጣጣሪ/ከፍተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ዋና ኃላፊ ወይም ከረዳት ተቆጣጣሪ ፈቃድ ማግኘት አለባቸው። ተማሪዎች ከውጪ ተናጋሪዎችን መጋበዝና በትምህርት ቤት ውስጥ ማዳመጥ ይችላሉ። የትምህርት ቤት ባለሥልጣናት አግባብ ባለው መንገድ የንግግሮችን ሰዓትና ቦታ ሊቆጣጠሩ ይችላሉ፣ እንዲሁም የጊዜ ግጭቶችን ለማስወገድና ለትምህርት ቤት ማህበረሰቡ ተገቢውን ጥበቃ ለማሰናዳት አስቀድሞ እንዲያሳውቋቸው ሊጠይቁ ይችላሉ። አስቀድሞ ፈቃድ ለማግኘት ተማሪዎች ከውጪ የምሚመጡ ተናጋሪዎችን ስም ለከፍተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ዋና ኃላፊ ወይም ለረዳት ተቆጣጣሪ የመስጠት ግዴታ አለባቸው። የተናጋሪው መምጣት የትምህርት ቤት እንቅስቃሴዎች ላይ ረብሻ ይፈጥራል ተብሎ ከፍተኛ ተጨባጭ ምክንያት ከሌለ በስተቀር የከፍተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ዋና ኃላፊ ወይም ረዳት ተቆጣጣሪው ፈቃዱን ይሰጣል። የተማሪ አስተዳደር ስብሰባዎችና የትምህርት ቤት ማህበረሰብ ስብሰባዎች እንደነዚህ ዓይነት ዝግጅቶችን ለማድረግ አግባብ ያላቸው ቦታዎች ናቸው።

42. ሐሳብን የመግለጽ ነጻነት

ፍርድ ቤቶች አንዳንድ በሕገ መንግሥት ውስጥ የተጠቀሱ መብቶችን ለትምህርት ቤቶች እንዴት   አድርገው ፍቺ በሰጧቸው መሠረት ተማሪዎች የነዚህ መብቶች ተካፋይ ናቸው። ተማሪዎች በቃል፣ በጽሑፍ፣ አንዳንድ እንደ ቁልፍ፣ አርማ፣ የክንድ ማሰሪያ በማድረግ ወይም በሌላ መንገድ ሐሳባቸውን የመግለጽ መብት አላቸው። የከፍተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ዋና ኃላፊው ወይም ተወካዩ የተወሰነ ዓይነት ሐሳብ ገለጻ በትምህርት ቤት እንቅስቃሴዎች ላይ ድንገተኛና ከፍተኛ ረብሻ ያመጣል ብሎ ተጨባጭ ምክንያት ካለው ሐሳብ መግለጽ ላይ ቁጥጥር ሊያደርግ ይችላል። ረብሻ ማለት ዘረኝነትን የሚደግፍ፣ ዘማዊ፥ ጸያፍ፣ ስም የሚያጠፋ፥ ወይም ሌሎች የትምህርት ቤት ደንቦችን እንዲጥሱ የሚቀሰቅስ ድርጊት ሊ   ይችላል።

43. የግለሰብ ነጻነት

ተማሪዎች በትምህርት ቤት ሕንጻዎች ውስጥ፣ የትምህርት ቤት ግቢ ውስጥ እንዲሁም ከቤት ወደ ትምህርት ቤት በሚመላለሱበት ጊዜና በማንኛውም ትምህርት ቤቱ በፈቀደው ዝግጅት ላይ ሲገኙ የግለሰብ ደህንነታቸው መጠበቅ መብት አላቸው። ማንኛውም ተማሪ፣ አስተማሪ ወይም የትምህርት ቤት ሹም አውቆ የአካል ጉልበት ተጠቅሞ ሌላ ተማሪ፣ አስተማሪ ወይም የትምህርት ቤት ሹም ላይ ጉዳት ማስከተል አይችልም። አንድ አስተማሪ ወይም የትምህርት ቤት ሹም አስፈላጊና አግባብ ካለው የአካል ጉልበት ሊጠቀም ይችላል። ይህ የሚፈቀድበት ሶስት ሁኔታዎች የሚከተሉት ናቸው:-

- መሳሪያ ወይም ሌላ አደገኛ ዕቃ ለመንጠቅ፣
- እራስን ከአደጋ ለመከላከል፣ እና
- ሌላን ሰው ወይም ንብረት ከአደጋ ለመከለከል።

ኃይል መጠቀም ሲያስፈልግ በአስተዋይነትና ልምድ ላይ ተመሥርቶ መን   አለበት። ተማሪን ሥርዓት ለማስያዝ ወይም ለምቅጣት ተብሎ ጉልበት መጠቀም ክልክል ነው።

44. ጸረ-አድሎ ፖሊሲና የጾታ ጉትጎታ ክልከላ

CPS ከማንኛውም በዘር፣ ቀለም፣ ዜግነት፣ ዘር ማንዘር፣ ኃይማኖት፣ ዕድሜ፣ አካል ብቃት፣ የሥነ ዘር መረጃ፣ ውትድርና ውስጥ በፊት በማገልገል፣ የጋብቻ ሁኔታ፣ ጾታ፣ መታወቂያ ጾታ፣ የጓደኛ ጾታ ምርጫ፣ ነፍሰ ጡርነት፣ ወይም ከነፍሰ ጡርነት ጋር የተያያዘ ሁኔታ ላይ የተመሠረተ አድሎ ነጻ የነ   የትምህርትና የሥራ ሁኔታ ለመጠበቅና ማንኛውም ዓይነት የሌሎችን ክብር የሚነካ ማስፈራራት፥ ዛቻ፥ በኃይል ማስገደድ እና/ወይም ማስጨነቅ ወይም ከመማርና ከመሥራት ነጻነት የሚያግድ ተግባርን አይቀበልም።

CPS ማንኛውም ተማሪዎቹ ወይም ሠራተኞቹ ላይ በማንም ቢን፥   ማለትም በሌላ ተማሪ፥ አስተማሪ፥ ተቆጣጣሪ፥ የሥራ ባልደረባ፥ ሻጭ ወይም ሌላ ሶስተኛ ወገን የሚደረግ ጉትጎታና አድሎን፥ ጾታዊም ነ   ሌላ፥ ከተልእኮው ጋር የሚጻረር በመኑና የትምህርትና የሥራ እኩል ዕድል ለመስጠት ተግቶ በመሥራቱ በጥብቅ ይከለክላል።

ማግለል እና ጥቃት ማለት በዘር፣ ቀለም፣ ዜግነት፣ ዘር ማንዘር፣ ኃይማኖት፣ ዕድሜ፣ አካል ብቃት፣ የሥነ ዘር መረጃ፣ ውትድርና ውስጥ በፊት በማገልገል፣ የጋብቻ ሁኔታ፣ ጾታ፣ መታወቂያ ጾታ፣ የጓደኛ ጾታ ምርጫ፣ ነፍሰ ጡርነት፣ ወይም ከነፍሰ ጡርነት ጋር የተያያዘ ሁኔታ ላይ የተመሠረቱ ተቀባይነት የሌላቸው የቃልም ነ የአካል ምግባሮች ናቸው። "የጾታ ጉትጎታ" ማለት ሳይፈልጉት የሚመጣ ግብረስጋዊ ነክ ምግባር ነው። በሚከተሉት ሁኔታዎች ላይ ግብረስጋዊ ግብዣን፣ ግብረስጋዊ ጥቅም መጠየቅን እንዲሁም

ግብረስጋዊ ተፈጥሮ ያለው አንደበታዊ ወይም አካላዊ ምግባርን ያካትታል፡-

- እንደነዚህ ዓይነት ግብዣዎችን መቀበል ወይም አለመቀበል ሥራ ከማግኘት፣ ከትምህርት ነጥብ፣ ከትምህርት ጋር የተያያዙ ዕድሎች ወይም ከቅጥር ውሳኔዎች ጋር የተያያዙ መስፈርቶች ነው   ሲቀርቡ።
- እንደነዚህ ዓይነት ግብዥዎች፣ ጥያቄዎች ወይም ምግባር ያላቸው ዓላማ ወይም የሚያስከትሉት ውጤት የአንድ ግለሰብ የትምህርት ወይም የሥራ አፈጻጸም ላይ አስፈሪ፣ አስጊ፣ አዋራጅ ወይም አስቀያሚ የሥራ ሁኔታ የሚፈጥር አግባብ የሌለው ተጽዕኖ ሲያመጡ።

የጾታ ጉትጎታ፣ ግብረስጋዊ ጥቃትን ወይም ማንኛውም ዓይነት በአልኮል መጠጥም ነ   በአደንዛዥ ዕጽ መጠቀም ምክንያት ሙሉ በሙሉ አንድ ሰው ፈቃድ መስጠት በማይችልበት ሁኔታ ላይ ኖ፣ ወይም የአእምሮ ወይም የአካል ጉዳት ያለበትን ሰው አስገድዶ ግብረስጋዊ ድርጊት የተፈጸመበትንም ሁኔታ ይጨምራል። የተለያዩ ድርጊቶች ማለትም አስገድዶ መድፈር፣ ግብረስጋዊ ዛቻ፣ ግብረስጋዊ ማስፈራራት ከግብረስጋዊ ጥቃት ይመደባሉ። እንደነዚህ ዓይነት ግብረስጋዊ ጥቃቶች በሙሉ በ Title IX ሥር የተሸፈኑ የጾታ ጉትጎታ ዓይነቶች ናቸው።

CPS የቅጥር ወይም የትምህርት ሁኔታ ላይ ተጽዕኖ የሚፈጥር፥ የግለሰብ ትምህርትን ወይም ሥራ የሚያስተጓጉል ወይም የሚያስፈራ ወይም የስድብ ስሜት የሚፈጥር የጉትጎታ ወይም የአድሎ ባሕርይን አይቀበልም። በትምህርት ቤቶች ወይም በሥራ ላይ ሠራተኞች ላይ ወይም ተማሪዎች ላይ አድሎ እና/ወይም ጉትጎታ በሕግ የተከለከለ ነው፥ CPSም በታጋሽነት የሚያየው አይደለም። ይህን ፖሊሲ በተመለከተ “መሥሪያ ቤት” ወይም “ትምህርት ቤት” ማለት በትምህርት ቤት ድጋፍ የተዘጋጁ ማህበራዊ ዝግጅቶችን፣ ጉዞዎችን፣ የስፖርት ዝግጅቶችን፣ ከሥራ ጋር የተያያዙ ጉዞዎችን ወይም ተመሳሳይ ከትምህርት ቤት ወይም ከሥራ ጋር የተያያዙ ሌሎች ዝግጅቶችን፣ ከትምህርት በተጨማሪ የሚሰጡ እንቅስቃሴዎችን፣ የስፖርት ፕሮግራሞችን፣ ትምህርት ቤቱ ወዳዘጋጀው ዝግጅት መጓዝን ጨምሮ ያጠቃልላል። በተጨማሪም ስለ አድሎ፥ ጉትጎታ ወይም ስለ አጸፋ ምላሽ አቤቱታ ያቀረበ ግለሰብ ላይ አጸፋ ምላሽ ማድረግ ወይም በተመሳሳይ የአድሎ፥ የጉትጎታ ወይም የአጸፋ ምላሽ ምርመራ ላይ የተባበረ ግለሰብ ላይ የሚደረግ አጸፋ ምላሽ ሕገወጥ ነው እንዲሁም በትእግሥት የሚታለፍ አይደለም።

CPS የአድሎና የጉትጎታ ክሶችን በቁም ነገር የሚወስድ ሲን ለክሶች በፍጥነት ምላሽ ይሰጣል። አላግባብ የነ   ምግባር ተከስቷል ተብሎ ከተወሰነ፥ ምግባሩን ለማስወገድ CPS ፈጣን እርምጃ ይወስድና እርማት ወዲያውኑ በሥራ ላይ ያውላል፥ አስፈላጊ ከነም   ቅጣትና ከሥራ ማባረ ወይም ከትምህርት ቤት ጋር የተያያዘ ቅጣት ይሰጣል።

አንድ ተማሪ መደበኛ ባልነ   ሁኔታ የአድሎ ክስ ለአስተማሪው፥ ለተቆጣጣሪው/የከፍተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ዋና ኃላፊው ወይም የተማሪዎች ጉዳይ ኃላፊ፥ የሕብራዊነት ልማት ዳይሬክተር ወይም ለማስተማርና መማር ምክትል ዋና ተቆጣጣሪ ማቅረብ ይችላል። አንድ ሠራተኛ ለተቆጣጣሪው፥ ለሕብራዊነት ልማት ዳይሬክተር ወይም ለሰው ኃይል አስተዳደር ሥራ አስኪያጅ አቤቱታ ማቅረብ ይችላል። የሕብራዊነት ልማት ዳይሬክተር፥ የሰው ኃይል አስተዳደርና የማስተማርና መማር ምክትል ዋና ተቆጣጣሪ ቢሮዎች በ 159 Thorndike Street, Cambridge, Massachusetts ይገኛሉ። የሕብራዊነት ልማት ዳይሬክተር ስልክ ቁጥር 617-349-6457 ነው፥ የሰው ኃይል አስተዳደር ስልክ ቁጥር 617-349-6438 ሲን   የማስተማርና መማር ምክትል ዋና ተቆጣጣሪ ስልክ ቁጥር 617-349-6418 ነው። የሕብራዊነት ልማት ዳይሬክተር መደበኛ የአድሎ አሠራሮች ክሶችንም ይቀበላል።

አልፎ አልፎ ክስ የቀረበበት ምግባር በ Title IX ሥር ከጾታዊ ጉትጎታ ሊመደብና እንደ ወንጀላዊ ድርጊት ሊቆጠር ይችላል። ምግባሩ ከወንጀልም ይመደባል ብለው የሚያምኑ ከነ በማንኛውም ጊዜ፥ ትምህርት ቤቱ ምርመራውን በሚያካሂድበት ጊዜም ነ   በኋላ ወንጀላዊ ክስ አብረው ማካተት ይችላሉ።

የትምህርት ቤት አውራጃው ጸረ-አድሎ ፖሊሲና ጸረ ጾታዊ ጉትጎታ ከልከላ በትምህርት ቤት አውራጃው ድህረ ገጽ ላይ ማግኘት ይችላሉ ወይም ከትምህርት ቤት ተቆጣጣሪው/የከፍተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ዋና ኃላፊው ቅጂ መጠየቅ ይችላሉ።

45. የተማሪ ጋብቻ፥ እርግዝናና ወላጅነት

እርጉዝ የኑ፣   ወላጅ የኑ   ወይም ትዳር የያዙ ተማሪዎች ትምህርት ቤት ውስጥ ትምህርት እንዲቀጥሉ እናበረታታለን። እነዚህ ተማሪዎች መደበኛ የትምህርት ክፍላቸው ውስጥ መቆየትና ከትምህርት ውጪ ያሉ እንቅስቃሴዎች ውስጥ ከሌሎች ተማሪዎች ጋር መሳተፍ ይፈቀድላቸዋል። በተጨማሪም ነፍሰ ጡር ተማሪዎች ከወለዱ በኋላ ወደ ትምህርት ቤት ተመልሰው መደበኛ የትምህርት ክፍላቸው ውስጥ መልሰው እንዲቀላቀሉና ከትምህርት ውጪ ያሉ እንቅስቃሴዎች ውስጥ ከሌሎች ተማሪዎች ጋር ከመውለዳቸው በፊት እንደነበረው መሳተፍ ይፈቀድላቸዋል። ማንኛውም ነፍሰ ጡር ተማሪ፣ ወላጅ ወይም ባለትዳር ተማሪ ባለ ትዳር ስለነ፣ ነፍሰ ጡር ስለነች   ወይም ወላጅ ስለነ   ክፍል ውስጥ ትምህርት መነፈግ ወይም ከትምህርት ውጪ ያሉ ክፍሎችን መነፈግ፣ ለጊዜው መባረር፣ እስከመጨረሻው መባረር፣ መቀጣት አይችልም።

46. የTitle IX አስተባባሪ

CPS በሚያካሂዳቸው ትምህርታዊ መርሃ ግብሮች ወይም እንቅስቃሴዎች ላይ የጾታ አድሎ አያደርግም፥ በትምህርታዊ መርሃ ግብሮቹ ወይም እንቅስቃሴዎቹ መግባት ላይ ወይም ቅጥር ላይ በጾታ የተመሠረተ አድሎ አያደርግም። የTitle IX ማመልከቻን በተመለከተ ማንኛውም ጥያቄ መቅረብ ያለበት ለትምህርት ቤት አውራጃው Title IX አስተባባሪ ነው፡- Director of Diversity Development, Cambridge Public Schools, 159 Thorndike Street, Cambridge, MA 02141, 617-349-6457 ወይም ለ United States Department of Education, Office of Civil Rights, 5 Post Office Square, 8th Floor, Boston, MA 02109 ስልክ፡- 617-289-0111፥ ፋክስ፡- 617-289-0150.

47. የኃይማኖት ነጻነት

የማሳቹሴትስ አጠቃላይ ሕጎች አንቀጽ 151C፥ ክፍል 2B የሚከተለውን አቅራቦት ይዟል፡-

> ማንኛውም ከኃይማኖታዊ ትምህርት ቤት ወይም የሙያ ሥልጠና ትምህርት ቤት ውጪ የነ   ትምህርት ቤት ወይም የሙያ ሥልጠና ትምህርት ቤት ውስጥ ያለ ተማሪ በኃይማኖቱ ምክንያት የተወሰነ ቀን ላይ ክፍል መሄድ፥ ፈተና

አለመውሰድ፥ ማጥናት ወይም መሥራት ካልቻለ ይቅርታ ተደርጎለት በሌላ ቀን ፈተናውን፥ ጥናቱን ወይም ሥራውን የማካካስ ዕድል ሊሰጠው ይገባል፥ ይህ የሚሆነው ግን ትምህርት ቤቱ ላይ አላግባብ የነ ጫና የማይፈጥር ከነ ነው። ይህን ዕድል በመስጠቱ ተቋሙ ምንም ዓይነት ክፍያ አያስከፍልም። በዚህ ክፍል መሠረት ያካካሰ ተማሪ ላይ ምንም ዓይነት መጥፎ ወይም ጭፍን ጥላቻ አይደርስበትም።

በኃይማኖት በዓል ምክንያት ከትምህርት ቤት የሚቀሩ ተማሪዎች ይቅርታ የተደረገለት መቅረት ነው ተብሎ ይመዘገብላቸዋል። ሁለተኛ፥ ተማሪዎች አስፈላጊ ፈተናዎች፥ ማጠናቀቂያ እንቅስቃሴዎች፥ ወሳኝ የቤት ሥራዎችና ሪፖርቶች በነዚህ ቀኖች ላይ ቀጠሮ እንዳያደርጉ ይጠየቃሉ። በመጨረሻም ተማሪዎች ወደ ክፍል ሲመለሱ በነዚህ ቀኖች የተሰጠውን የቤት ሥራ ለማካካስ አስተማሪዎች ለተማሪዎች በቂ ጊዜ መስጠት አለባቸው።

48. በሰንደቅ ዓላማ ፊት ቃለ መሃላ መመሪያዎች

የማሳቹሴትስ አጠቃላይ ሕጎች አንቀጽ 71፥ ክፍል 69 የሚከተለውን አቅራቦት ይዟል:-

> እያንዳንዱ አስተማሪ ሁሉም የመንግሥት ትምህርት ቤቶች ክፍሎች የቀኑ የመጀመሪያ ክፍል ሲጀመር "የሰንደቅ ዓላማ ቃላ መሃላ" ንባብ ይመራሉ።

ተማሪዎች ሰንደቅ ዓላማ ፊት ቃለ መሃላ ላይ የመሳተፍ ግዴታ የለባቸውም። ማንኛውም መሳተፍ የማይፈልግ ተማሪ ሌሎች መሳተፍ የሚፈልጉ የተማሪዎችን መብት ያለ ረብሻና ያለማቋረጥ እንዲያከብር ይጠበቅበታል።

አጠቃላይ ፖሊሲዎች

49. ለኮምፒዩተር ኔትወርክ ተቀባይነት ያለው አጠቃቀም ፖሊሲ (AUP)

ለኤሌክትሮኒክ ግንኙነት የሚጠቀሙት ቴክኖሎጂ በሙሉ፥ የ CPS ኔትወርክ ውስጥ መግባትና ኢንተርኔት ውስጥ መግባትን ጨምሮ፥ እንዲሁም CPS ለሠራተኞች እና/ወይም ለተማሪዎች የሰጣቸውን ኤሌክትሮኒክ መሣሪያዎች (ለምሳሌ ኮምፒዩተሮች፥ ስልኮች፥ ወዘተ.) ጨምሮ ሲጠቀሙ ኃላፊነት ወስደው በሕጋዊና ግብረ ገባዊ መንገድ መን እንዳለበት የ CPS ፖሊሲ ይገልጻል።

የCPS ኮምፒዩተር ኔትወርክና የኤሌክትሮኒክ መሣሪያዎች የተዘረጉት ለውስን ትምህርታዊ ዓላማ ሲን እንደ ሕዝብ መጠቀሚያ አገልግሎት ወይም የሕዝብ ፎረም ነው አልተዘረጉም። CPS የኮምፒዩተር ሲስተምና ሁሉም የሚሰጣቸው ኤሌክትሮኒክ መሣሪያዎች ላይ ዕቀባ የማድረግ መብት አለው፥ ተጠቃሚዎች በሙሉ የሲስተሙን ደንቦችና የትምህርት ቤት ኮሚቴ ፖሊሲዎችን፥ የጸረ-አድሎ ፖሊሲና የጾታዊ ጉትጎታና ጸረ-ማስፈራራት ፖሊሲን ጨምሮ እንዲያከብሩ እንዲሁም የተማሪ መዝገብ መረጃና የሠራተኛ መዝገብ መረጃ ምስጢራዊነትን እንዲጠብቁ ማስገደድ።

ኢንተርኔት ላይ ብዙ ጠቃሚ ግልጋሎቶች ቢኖሩም ብዙ ለተማሪዎች አግባብነት የሌላቸውና ምንም ትምህርታዊ ዋጋ የሌላቸው ድህረ ገጾች አሉ። ሁሉም ኢንተርኔት የሚጠቀሙ ግለሰቦች የኮምፒዩተር ኔትወርኩን ለትምህርታዊ ጠቀሜታ ብቻና ከ CPS የትምህርት እንቅስቃሴዎች ጋር ወጥ በነና ኃላፊነት በተሞላ መልኩ መጠቀም አለባቸው፥ በ CPS ቁጥጥር ሥርም ይናሉ ። የCPSን የኔትወርክ መረጃ ግልጋሎቶች ተማሪዎችና አዋቂ ተጠቃሚዎች ሲጠቀሙ ይህንን ፖሊሲ ለመከተል ተስማምተዋል ማለት ነው። የCPSን የኔትወርክ መረጃ ግልጋሎቶች ለሕገወጥ ወይም ለንግድ እንቅስቃሴዎች መጠቀም ክልክል ነው።

CPS ለትምህርት የማይሉ ድህረ ገጾችና አጸያፊና የፖርኖግራፊ ድህረ ገጾች ወይም ለልጆች ጎጂ የሚሉ ድህረ ገጾች ውስጥ መግባት የሚከለከል የማጣሪያ ዘዴ ይጠቀማል። ኖም ፍጹም የነ መፍትሄ እንደሌለና ተማሪዎች ተገቢ ያልነ ድህረ ገጽ ውስጥ አለመግባታቸውን CPS ሊያረጋግጥ እንደማይችል መረዳቱ አስፈላጊ ነው። አግባብ የሌለው ድህረ ገጽ ተማሪ ካየ ለአስተማሪ አሳውቆ ወደተመደበለት ትምህርታዊ ርእስ የመመለስ ኃላፊነት አለበት።

ለማስተማር ኢንተርኔት የሚጠቀሙ አስተማሪዎች፥ አስተዳዳሪዎችና ሌሎች የትምህርት ቤት ሠራተኞች የ CPS Information, Communication and Technology Systems (ICTS) (መረጃ፥ መገናኛና የቴክኖሎጂ ሲስተሞች) ጋር ደውለው የተወሰነ ድህረ ገጽ እንዲታገድ ወይም እንዳይታገድ መጠየቅ ይችላሉ። እንደነዚህ ዓይነት ውሳኔዎች የሚደረጉት የ CPSን ማጣሪያ ሲስተም የሚቆጣጠሩት ከተገቢው የትምህርት ቤት ሠራተኞች ጋር በመተባበር ነው።

የ CPSን ከምፒዩተሮች፥ የኮምፒዩተር ኔትወርክ፥ ኢንተርኔት ውስጥ መግባትን ጨምሮና ኢሜል እንዲሁም ሌሎች የኤሌክትሮኒክ መሣሪያዎች (እንደ ሞባይል ስልኮች እና/ወይም የእጅ ኮምፒዩተሮች) መጠቀም ልዩ ጥቅም እንጂ መብት አይደለም። *የAcknowledgement of Receipt of the Acceptable Use Policyን (አግባብ ያለው የአጠቃቀም ፖሊሲ መድረሱን እውቅና) አልፈርምም ማለት እና/ወይም ማንኛውም የCambridge Public Schools Acceptable Use Policy (የኬምብሪጅ መንግሥት ትምህርት ቤቶች አግባብ ያለው አጠቃቀም ፖሊሲ) ጥሰት የኮምፒዩተር፥ የኮምፒዩተር ኔትወርክ፥ ኢንተርኔት ውስጥ መግባትን ጨምሮና ኢሜል እንዲሁም ሌሎች የኤሌክትሮኒክ መሣሪያዎችን ማጣት ሊያስከትል እና/ወይም ቅጣት እና/ወይም በስቴትና በፌዴራል ሕግ መሠረት ክስ ሊያስከትል እንደሚችል ሁሉም የ CPS ሠራተኞች፥ ተማሪዎች እና የተማሪዎች ወላጆች/አሳዳጊዎች መረዳታቸው አስፈላጊ ነው።*

CPS ለሚያቀርባቸው አገልግሎቶች በግልጽም ነ በእጅ አዙር ምንም ዓይነት ዋስትና አይሰጥም። በማንኛውም ምክንያት ሊያጋጥሟችሁ ለሚችሉ ምንም ዓይነት ጉዳቶች ለምሳሌ መረጃ ቢጠፋ፥ አገልግሎት ቢቋረጥ፥ መዘግየት፥ አለመድረስ ወይም በስህተት መድረስ ቢከሰት CPS ምንም ዓይነት ኃላፊነት አይወስድም። በኔትወርክ በኩል ለመጣ ወይም ኔትወርክ ላይ ተቀመጠ ለተገኘ መረጃ ትክክለኛነት ወይም ጥራት CPS ምንም ዓይነት ኃላፊነት አይኖረውም፥ ይህን ዓይነት መረጃም የምትጠቀሙት በራሳችሁ ኃላፊነት ነው። ኔትወርኩን ከመጠቀም ጋር ለተያያዙ የገንዘብ ግዴታዎች CPS ኃላፊነት አይኖረውም።

በኬምብሪጅ ትምህርት ቤት ኮሚቴና በ CPS ፖሊሲ መሠረት ሁሉም በኤሌክትሮኒክ ሁኔታ የሚተላለፍ መረጃና ተቀማጭ መረጃ በዚህ በ Acceptable Use Policyን (አግባብ ያለው የአጠቃቀም ፖሊሲ) ሥር የሚተዳደር ነው። ሁሉም በኤሌክትሮኒክ ሁኔታ የሚተላለፍ፥ የሚደርስ ወይም የሚቀመጥ መረጃ እንደ CPS እና/ወይም የኬምብሪጅ ትምህርት ቤት ኮሚቴ ንብረት የሚታይ

ሲን በዘፈቀደ፥ ሳይታወቅ ክትትል ሊደረግበት፥ መዝገብ ውስጥ ሊከተት ወይም ሊወጣ ይችላል። የ CPSን ኮምፕዩተር ኔትወርክ፥ ኢንተርኔት ውስጥ መግባትንና ኢሜልን ጨምሮ ሲጠቀሙ ምንም ዓይነት ግለኝነት አለ ብሎ መጠበቅ እንደሌለባቸው፥ የትኛውንም የመገናኛ መሣሪያ በ CPS ኮምፕዩተር ኔትወርክ ተጠቅመው የሚላኩ ሁሉም ግለኝነት እንደሌላቸው የ CPS ሠራተኞች፥ ተማሪዎችና የተማሪዎች ወላጆች/አሳዳጊዎች መረዳታቸው አስፈላጊ ነው። CPSና የኬምብሪጅ ትምህርት ቤት ኮሚቴ የኢሜል ፋይሎች፥ የኮምፕዩተሮች፥ የኮምፕዩተር ሃርድ ድራየቮችና ሌሎች የኤሌክትሮኒክ መገናኛ ፋይሎች፥ ሲስተሞች፥ መሣሪያዎችና ፕላትፎርሞች ትምህርት ቤት ውስጥ ነው የገቡባቸውም ነ ከትምህርት ቤት ውጪ፥ ከሥራም ነ ከቤት ነው በርቀት ሲሠሩ፥ ከትምህርት ቤት አውራጃው ሰርቨር ጋር በቀጥታ የተገናኘ ከኑ፥ አጠቃቀማቸውን የመከታተል ችሎታ አለውም ያደርገዋልም።

ኃላፊነት የተሞሉ የኔትወርክ ተጠቃሚዎች የ CPSን ኮምፕዩተር ኔትወርክ፥ ኢንተርኔትና ኢሜል ለሚከተሉት አያውሉም፡-

(ሀ) ለማናቸውም ዓይነት የንግድ ዓላማ

(ለ) ለፖለቲካ ተጽእኖ፥ ኖም ተጠቃሚዎች ሲስተሙን ከፖለቲካ ተወካዮች ጋር ለመገናኘትና የፖለቲካ ጉዳዮችን በተመለከተ ሐሳባቸውን ለመግለጽ መጠቀም ይችላሉ

(ሐ) ለሕገወጥ እንቅስቃሴዎች

(መ) የራሳቸውን ወይም የሌሎችን የግል መገናኛ መረጃ ለምሳሌ ስም፥ አድራሻ፥ ስልክ ቁጥር፥ የትምህርት ቤት ወይም የሥራ አድራሻ አስቀድመው ከግለሰቡ በጽሑፍ ፈቃድ ሳያገኙ መለጠፍ

(ሠ) አስቀድመው ከትምህርት ቤት አስተዳዳሪ ፈቃድ ሳያገኙና ከተማሪው ወላጅ/አሳዳጊ/ተንከባካቢ የጽሑፍ መረጃ ሳያገኙ የተማሪ መረጃን መለጠፍ፥ ማሳወቅ ወይም ማሰራጨት፥ ይህ ዓይነቱ ማሳወቅ ወይም ማሰራጨት የማሳቹሴትስ የተማሪ መዝገብ ደንቦች የሚፈቅደው ካልነ በስተቀር

(ረ) በግል የተላከላቸውን መልዕክት ከላኪው ፈቃድ ሳያገኙ መለጠፍ ወይም ማሰራጨት። ኖም ይህ አግባብ የሌለውና ደህንነታቸውን ስጋት ላይ የሚጥል መልዕክት አንድ ሰው ቢደርሰው ለአስተማሪ ወይም ለትምህርት ቤት አስተዳዳሪ ከማሳወቅ አይከለክልም።

(ሰ) ለዛቻ፥ ለማዋረድ፥ ለማስፈራራት፥ ለጉትጎታ ወይም አጸቃፊ መረጃ ለሌላ ሰው ወይም ስለ ሌላ ሰው ለመላክ

(ሸ) የኮምፕዩተር ኔትወርክ ተጠቅሞ ሰንሰለት ደብዳቤዎች መለጠፍ፥ ስፓም ማድርግ ወይም ማንኛውም ሌላ አግባብ የሌለው የግንኙንት መልክ መጠቀም

(ቀ) የሠራተኞች መዝገብ መረጃ ከትምህርት ቤት አስተዳዳሪ አስቀድሞ ፈቃድ ሳያገኙ መለጠፍ፥ ማሳወቅ ወይም ማሰራጨት፥ ይህ ዓይነት ማሳወቅ ወይም ማሰራጨት በፌዴራል ወይም በስቴት ሕግ የሚፈቀድ ካልነ በስተቀር

(በ) ወሲባዊ ፎቶዎች፥ ቴክስቶች፥ ኢሜሎች ወይም ሌላ ዓይነት ቁሳቁሶች በማንኛውም ኮምፕዩተር፥ ሞባይል ስልክ ወይም ሌላ ኤሌክትሮኒክ መሣሪያ ማየት፥ መለጠፍ፥ መላክ፥ ማካፈል ወይም ማሰራጨት፥ የፌዴራል ወይም የስቴት የልጆች ፖርኖግራፊ ሕግ ቢጣስም ባይጣስም

(ተ) የትምህርት አካባቢውን ለሚረብሹ እንቅስቃሴዎች

(ቸ) ሥነ ምግባር ለጎደላቸው እንቅስቃሴዎች፥ ለምሳሌ ፕሮጀክቶች ወይም ፈተና ላይ ማታለል

(ኀ) የሌሎችን ግለኝነት የሚነኩ እንቅስቃሴዎች

(ነ) ለግል ጥቅም፥ ማለትም የኬምብሪጅ መንግሥት ትምህርት ቤቶች ኔትወርክና ኤሌክትሮኒክ መሣሪያዎች መዋል ያለባቸው ለሥራ እና/ወይም ለትምህርት ቤት ጉዳዮች ብቻ ነው

(ኘ) ማንኛውንም የኬምብሪጅ መንግሥት ትምህርት ቤቶች ፖሊሲ እና/ወይም የኬምብሪጅ መንግሥት ትምህርት ቤቶች ሙብቶችና ኃላፊነቶች መመሪያ ወይም የትምህርት ቤት ደንቦችን የሚጥስ ወይም የሚተላለፍ ማንኛውም ሥነ ምግባር

(አ) የግል መረጃን ወይም የተማሪን ማንነት የሚያሳውቅ መረጃን (ለምሳሌ ስም፥ አድራሻ፥ ስልክ ቁጥር፥ የኢሜል አድራሻ፥ ወዘተ) ማስገባት የሚጠይቁ ድህረ ገጾችን ተማሪዎች እንዲጠቀሙ አለመፍቀድ፥ ይህን ዓይነት ድህረገጽ መጠቀምን ICTS ካልፈቀደ በስተቀር

(ከ) የM.G.L.c. 71, §37O አቅራቦቶች መጣስ፥ የማስፈራራት፥ የኢንተርኔት ማስፈራራትና የአጸፋ መልስ አቅራቦቶቹን ጨምሮ።

ኃላፊነት የተሞሉ የኔትወርክ ተጠቃሚዎች የሚከተሉትን ያደርጓሉ፡-

(ሀ) ሙቼም ቢን በግልጽ ፈቃድ ካላገኙ በስተቀር የማንንም የግል መረጃ አያሳውቁም፥ ለምሳሌ እንደ አድራሻ፥ ስልክ ቁጥር፥ የክሬዲት ካርድ ቁጥር፥ ሶሻል ሴክዩሪቲ ቁጥር፥ በተጨማሪም ተማሪ ተጠቃሚዎች ማንንም ከወላጅ/አሳዳጊ/ተንከባካቢ ፈቃድ ካላገኙ በስተቀር በኢተርኔት ላይ የሚተዋወቁትን ሰው ሙቼም ቢን በአካል አያገኙም

(ለ) የኮምፕዩተር ኔትወርክ ላይ የሚያገኟቸውን የደህንነት ችግሮች ለሲስተም አስተዳዳሪው ማሳወቅ

(ሐ) ኤሌክትሮኒች መሣሪያዎቻቸውን ኃላፊነት በተመላ መንገድ መጠቀምና የማንኛውም መሣሪያ ፓስወርዳቸውን ወይም አካውንታቸውን ለማንም አሳልፎ አለመስጠት

(መ) የኢሜል፥ የመረጃ ወይም ማንኛውም ኤሌክትሮኒክ መሣሪያ ላይ ያሉ የግል ፋይሎች ይዘት ምንም ዓይነት የግለኝነት ሙብት እንደሌለውና ሁሉም ኤሌክትሮኒክ መሣሪያዎችና ሲስተሙ መዝገብ ውስጥ እንደሚገባ፥ በየጊዜው ጥገና እንደሚደረግ፥ መልዕክቶችና እንደሚታዩና ክትትል እንደሚደረግባቸው እንዲሁም አስፈላጊ ሲን ማግኘት እንደሚቻል መገንዘብ

(ሠ) ማንኛውንም የሚያገኙትን አግባብ የሌለው ወይም ቢሄዱበት ጥበቃ ያላቸው መስሎ የማይሰማቸውን ድህረ ገጽ ወዲያውኑ ለአስተማሪ ወይም ለትምህርት ቤት አስተዳዳሪ ማሳወቅ

(ረ) የCPS ኮምፕዩተር ኔትወርክ ውስጥ ፈቃድ ባልተሰጠበት ሁኔታ ለመግባት አለመሞከር ወይም ተጠቃሚ ከተሰጠው ፈቃድ በላይ ለመሄድ አለመሞከር፥ የኮምፕዩተር ኔትወርኩን ለማበላሸት አለመሞከር ወይም የኮምፕዩተር ቫይረስ በመልቀቅ ወይም በሌላ መንገድ መረጃ ለማጥፋት አለመሞከር፥ ወይም በሌላ መንገድ የኮምፕዩተር ኔትወርኩን፥ ፕሮግራሞችን፥ መረጃን ወይም ኤሌክትሮኒክ መረጃን ወይም መሣሪያዎችን ለማበላሸት፥ ለማጥፋት ወይም ለመስበር አለመሞከር

(ሰ) የሶፍትዌር አምራቾችንና የኔትወርክ አቅራቢዎችን ሕጋዊ መብቶች፣ የኮፒራይትና ፈቃድ ስምምነቶችን ማክበር

(ሸ) አጸያፊና ነውረኛ ነገር (ለምሳሌ ፖርኖግራፊ)፣ ሕገወጥ ድርጊቶች የሚደግፍ፣ ጥቃት ወይም ሌሎች ሰዎች ላይ አድሎ የሚያበረታታ (ለምሳሌ የጥላቻ ጽሑፍ) ወይም ሕገወጥ ነገር (ለምሳሌ ቁማር) ለማየት ሲስተሙን አለመጠቀም

(ቀ) የኬምብሪጅ ትምህርት ቤት ኮሚቴና የCPS ፖሊሲዎችን ማክበር፣ የኮምፕዩተር ኔትወርክ፣ የኮምፕዩተር ሲስተምና ኢሜል ከመጠቀም ጋር በተያያዘ የጸረ አድሎ ፖሊሲና የጾታ ጉትጎታ ክልከላን፣ የጥላቻ ወንጀሎች ተቀባይነት አለመኖር ፖሊሲና ጸረ ማስፈራራት ፖሊሲ ማክበር

(በ) የኮምፕዩተር ኔትወርክ፣ የኮምፕዩተር ሲስተምና ኢሜል ሲጠቀሙ ለሌሎች የትምህርት ቤቱ መገናኛ ጽሑፎች፣ የትምህርት ቤት ማህተም ያለበት ደዳቤ ላይ የሚጠቀሙትን ዓይነት ተመሳሳይ ጥንቃቄ፣ የራስን መላምት እና ሙያነት መጠቀም

(ተ) በ CPS ጸረ አድሎ ፖሊሲና ጸረ ጾታዊ ጉትጎታ ክልከላና ጸረ ማስፈራራት ፖሊሲ መሠረት የዛቻ፣ የማዋረድ፣ የማስፈራራት፣ የኢንተርኔት ማስፈራራት፣ የአጸፋ መልስ፣ የጉትጎታ ወይም ተሳዳቢ መልዕክቶች ሲደርሱ ወይም ሲከሰስቱ ማሳወቅ (በኢሜልም ነ፣ በቴክስት፣ በማህበራዊ ድህረ ገጽ ወይም በሌላ መንገድ)

(ቸ) የርቀት ትምህርት ላይ የሚጠቀሙት ኅትመት ትምህርቱ ውስጥ ለተመዘገቡ ለሚመለከታቸው ተማሪዎች ብቻ መቅረቡን ያረጋግጡ፣ የሚቀርበው ለርቀት ትምህርትም ነ በአካል ለሚገኙበት ክፍል ተጨማሪ ኅትመትም ቢን፣ ሥራዎች ከክፍሉ ርዝመት በላይ አለመቆየታቸውንና ያለፈቃድ አለመሰራጨታቸውን ለማረጋገጥ ተገቢውን ጥንቃቄ መውሰድ (ለምሳሌ ፓስወርድ መጠቀም፣ በኢንተርኔት ፕሮቶኮል አማካኝነት ተጠቃሚና ቦታን ማረጋገጫ መጠቀም፣ ይዘትን ለተወሰነ ጊዜ ብቻ መጠቀም፣ ወረቀት ላይ ማተምና ኮፒ አርጎ መለጠፊያውን እንዳይጠቀሙ እንዳይሠራ ማድረግ)፣ ሥራው በኮፒራይት የተጠበቀ መኑንና፣ በሕጋዊ መንገድ የተገኘ ይዘት ብቻ እንደነ የሚለጠፈው፣ ይዘቱ በአስተማሪው ቁጥጥር ሥር ኖ ብዛቱ በአካል እንደሚገኙበት ክፍል ብዛት ያለው እንደሚን ለተማሪዎች ግልጽ ማድረግ።

(ኃ) አግባብ ስላለው የኢንተርኔት ምግባር፣ በማህበራዊ ድህረገጾች፣ ቻትሩሞችና የኢንተርኔት ማስፈራራትና ምላሽ ግንዛቤን ጨምሮ ተማሪዎች ትምህርት ማግኘታቸውን ማረጋገጥ።

ሥርዓት

የዚህ ፖሊሲ ማንኛውም ጥሰት ኔትወርክ መጠቀም የመቻልን ልዩ ጥቅም ሊያስዘርዝ እና/ወይም በ CPS ደንቦች መሠረት ተገቢውን የቅጣት እርምጃ ወይም አግባብ ካለው ሕጋዊ እርምጃ ሊያስከትል ይችላል።

ማንኛውም ደህንነትን ስጋት ላይ ይጥላል ተብሎ የተለየ ተጠቃሚ ወይም ከሌሎች የኮምፕዩተር ሲስተሞች ጋር ችግር የመኖር ታሪክ ያለው ተጠቃሚ በትምህርት ቤት መምሪያው ውሳኔ መሠረት ኔትወርክ ውስጥ ከመግባት ሊከለከል ይችላል።

በማንኛውም በኔትወርኩ አማካኝነት የተካሄዱ ሕገወጥ እንቅስቃሴዎችን የተመለከተ ምርመራ ላይ የትምህርት ቤት መምሪያው ሙሉ በሙሉ ከአካባቢው የስቴት ወይም የፌዴራል ሹሞች ጋር ይተባበራል።

50. የሶፍትዌር ግብረገብ መመሪያ

በኮፒራይት የተጠበቀ የኮምፕዩተር ሶፍትዌርን ያለፈቃድ ግልባጭ ማድረግ ሕግን መጣስና የ CPS ምግባር ደንቦችን የሚጻረር ነው። CPS ይህን ዓይነት ግልባጭ አይደግፍም፣ ይህን ዓይነት ክስተት እንዳይፈጠርም የሚከተሉትን መመሪያዎች ይከተላል፡-

- CPS በማንኛውም ሁኔታ ፈቃድ ያልተሰጠበትን የሶፍትዌር መገልበጥ ውስጥ አይሳተፍም፣ አይደግፍምም።
- CPS በሕጋዊ መንገድ የተገኘ ሶፍትዌርን ለሕጋዊ ጥቅም እንዲውል ጊዜውን በጠበቀ መንገድና በበቂ መጠን ሶፍትዌሩ ለሚያስፈልጋቸው ኮምፕዩተሮቻችን ሁሉ ያቀርባል።
- CPS ለሚገዛቸው ወይም ለሚጠቀማቸው ሶፍትዌሮች ሁሉ የሚመሯቸውን የፈቃድ ወይም የግዢ ስምምነቶቻቸውን ሁሉ ያከብራል።
- ፈቃድ የሌለው የሶፍትዌር ግልባጭ እንዳይሠራ ወይም ጥቅም ላይ እንዳይውል CPS ውስጣዊ ቁጥጥሮቹን ያጠብቃል፣ ከመስፈርቶቹ ጋር መጣጣሙን ማረጋገጫ መንገዶች መጠቀምና መስፈርቶቹ ከተጣሱ አስፈላጊውን ቅጣት መውሰድን ጨምሮ።

51. ትምህርት ቤት ጎብኚዎች

የትምህርት ቤት ደህንነትን ለመጠበቅ ጎብኚዎች ሁሉ የትምህርት ቤቱ ሕንጻ ውስጥ የትም ሌላ ቦታ ከመሄዳቸው በፊት መጀመሪያ ዋና ቢሮው ጋር መሄድ አለባቸው። አንድ ጎብኚ አግባብ በሌለው ምግባር ምክንያት ወይም አግባብ በሌለው ሰዓት ልጎብኝ ብሎ የተማሪዎችን፣ የአስተማሪዎችን ወይም የሌሎች ሠራተኞችን ሥራ ካስተጓጎለ ተቆጣጣሪው/የከፍተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ዋና ኃላፊው የግለሰቡ መጎብኛ ዕድል ላይ ገደብ ሊያደርግበት፣ ከመምጣቱ በፊት ቀጠሮ እንዲይዝ ሊያስደርገው፣ ትምህርት ቤቱ ውስጥ በሚጎበኝበት ጊዜ በትምህርት ቤት ሠራተኛ እንዲታጀብ ወይም የትምህርት ቤት ሕንጻ ውስጥ እንዳይገባ እንዲከለከል ሊያስደርግ ይችላል። ትምህርት ቤቱ ጎብኚዎችን በተመለከተ ስላለው ፖሊሲ በይበልጥ ለማወቅ እባክዎን ተቆጣጣሪውን/የከፍተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ዋና ኃላፊውን ይገናኙ።

52. የመኪና ሞተር እንደበራ መቆም አይቻልም

የማሳቹሴትስ አጠቃላይ ሕግ አንቀጽ 71፣ ክፍል 37H የትምህርት ቤት አውቶቡስ አሽከርካሪዎችና የግል መኪና አሽከርካሪዎች ሞተራቸው እንደበራ በትምህርት ቤት ቅጥር ግቢ ውስጥ ወይም ከትምህርት ቤት በመቶ (100) ጫማ ርቀት ውስጥ ማቆም ክልክል ነው።

53. የተማሪ ዕቃ ማስቀመጫ ሳጥኖች

ብዙ CPS ትምህርት ቤቶች፣ በተለይ አዲሶቹ፣ ለተማሪዎች የዕቃ ማስቀመጫ ሳጥኖች አሏቸው። የዕቃ ማስቀመጫ ሳጥኖች ልዩ ጥቅሞች ናቸው። የዕቃ ማስቀመጫ ሳጥን የተመደበላቸው ተማሪዎች የሚከተሉትን ሁኔታዎች ማክበር አለባቸው፡-

የሳጥኖቹን ደህንነትና የይዘቱን ግለኝነት ለመጠበቅ የተቻለው ጥረት ሁሉ መደረግ አለበት።

ኃላፊው ካልፈቀደ በስተቀር ተማሪዎች አንድ ሳጥን ለሁለት መጠቀም አይችሉም።

ሳጥኖች ላይ መቸክቸክ ወይም በጽዳትና በደንብ አለመያዝ ተቀባይነት አይኖረውም።

የዕቃ ማስቀመጫ ሳጥኖች ለተማሪዎች ልብስና የትምህርት ዕቃ ለምሳሌ መጽሐፍ፣ ማስታወሻ፣ ፕሮጀክቶች፣ ቁሳቁሶች፣ ምሳ፣ ወዘተ ማስቀመጫ ናቸው።

ተማሪዎች የትምህርት ቤታቸውን የዕቃ ማስቀመጫ ደንቦች፣ በተወሰነ ጊዜ መክፈትን ጨምሮ ወዘተ፣ ማክበር አለባቸው።

የትምህርት ቀን ማብቂያ ላይ ተማሪዎች የሚያስፈልጋቸውን ነገር ከዕቃ ማስቀመጫቸው አውጥተው መውሰድ አለባቸው። ከትምህርት ሰዓት ውጪ አስፈላጊ ነገር ከሳጥኑ ማውጣት ቢፈልጉ የአስተዳደር ፈቃድ ያስፈልጋል።

ዕቃ ማስቀመጫ ሳጥኖች የትምህርት ቤቱ ንብረት እንደመናቸው መጠን፣ የአንድ ተማሪ ዕቃ ማስቀመጫ ሳጥን ሐገወጥ ዕቃ፣ መሣሪያ ወይም ከትምህርት ቤት ሕግ ወይም ደንብ ጥሰት ጋር የተያያዘ ማስረጃ አለው ተብሎ ወይም ወዲያውኑ የትምህርት ቤቱን ሕንጻ ወይም ውስጡ ያሉትን ሰዎች አደጋ ላይ የሚጥል ነገር አለው ተብሎ ከተጠረጠረ፣ የትምህርት ቤቱ መምሪያ ሳጥኖችን የመፈተሽ መብት አለው። ትምህርት ቤቶች አስቀድሞ ተናግረው ወይም አስቀድሞ ሳይናገሩ ዕቃ ማስቀመጫ ሳጥኖችን ይፈትሻሉ። ስለዚህ ዕቃ ማስቀመጫ ፖሊሲ በይበልጥ መረጃ ለማግኘት *የመብቶችና ኃላፊነቶች መመሪያ* ክፍል 4.0ን ይመልከቱ።

በትምህርት ዓመቱ ወቅት ዕቃ ቢጠፋ CPS ኃላፊነት የለበትም። ከመጨረሻው የትምህርት ቀን በኋላም የዕቃ ማስቀመጫ ውስጥ የተተወ ዕቃ ቢጠፋ CPS ኃላፊነት የለበትም። እነዚህ ሕጎችና ደንቦች ከትምህርት ቤቱ ደንቦች ጋር አብረው የተማሪዎችን ጠረጴዛም ይመለከታሉ።

54. የወንጀለኛ መዝገብ መረጃ

CPS ለተማሪዎቹ ደህንነቱ የተጠበቀ መማሪያ አካባቢና ለሠራተኞቹ ደህንነቱ የተጠበቀ መሥሪያ አካባቢ ለማቅረብ ተግቶ ይሠራል። በዚህ መሠረት M.G.L.c. 71, §38R ውስጥ ባሉት አቅራቦቶችና በ Chapter 385 በተሻሻሉት የ2002 ሕጎች መሠረት እንዲሁም በ M.G.L.c. 6, §172I መሠረት CPS በየጊዜውና ቢያንስ በየሶስት (3) ዓመቱ በወቅታዊና የወደፊት ሠራተኞች፣ በኮንትራት የሚሠሩ አገልግሎት ሠጪዎች፣ በፈቃደኝነት ሠሪዎች፣ የትምህርት ቤት መጓጓዣ አቅራቢዎች የታክሲ ኩባንያ ሠራተኞች ላይ ጨምሮ፣ እንዲሁም የባለ ኮንትራት ሠራተኛና በትምህርት ቤት ቅጥር ግቢ ውስጥ የቀን ሠራተኞች ላይ እንዲሁም ሌሎች በቀጥታም ነ ያለቁጥጥር ከልጆች ጋር ሊገናኙ የሚችሉ ሰዎች ላይ መለስተኛ የወንጀለኛ ማጣሪያ (“CORI checks” (“የCORI ማጣሪያዎች”)) ያካሂዳል። የCORI ማጣሪያዎች ወቅታዊና የወደፊት ሠራተኞች ላይ እንዲሁም አገልግሎት ሠጪዎች ላይ ከመቀጠራቸው እና/ወይም ኮንትራት ከመጀመራቸው በፊትና እና ማንኛውም በፈቃደኝነት የሚሠራ ሰው ከመጀመሩ በፊት ላይ ይደረጋሉ።

በተጨማሪም በስቴት ሕግ መሠረት በአሻራ ላይ የተመሠረተ የስቴትና ብሔራዊ የወንጀል ታሪክ መዝገብ ማጣሪያ ውስጥ ወቅታዊና የወደፊት ሠራተኞች ይታያሉ።

55. ትምህርታዊ ጉዞዎች

የኬምብሪጅ ትምህርት ቤት ኮሚቴ ከትምህርታዊ ጉዞዎች የሚገኙ ቀጥተኛ ተሞክሮዎች ለመማር ይበልጥ ውጤታማና ጠቃሚ እንደኑ ይገነዘባል፣ ስለዚህ የኬምብሪጅ ትምህርት ቤት ኮሚቴ ትምህርታዊ ጉዞዎችና በትምህርት ቤት ድጋፍ የሚደረጉ ጉዞዎች ከአጠቃላይ የትምህርት ቤት መርሃ ግብርና ሥርዓተ ትምህርት ጋር የተያያዙ ከፍተኛ ትምህርታዊ ዋጋ ያላቸው እንዲኑ ያበረታታል። በተጨማሪም ትምህርታዊ ጉዞዎችና በትምህርት ቤት ድጋፍ የሚደረጉ ጉዞዎች ከፍተኛ ትምህርታዊ ዋጋ ስላላቸው ተማሪዎች ሁሉ መሳተፍ እንዲችሉና እኩል መካፈል እንዲችሉም ያበረታታል።

ከዚህ ግብ ተነስቶ፣ የትምህርት ቤቶች ዋና ተቆጣጣሪ ለትምህርታዊ ጉዞዎችና በትምህርት ቤት ድጋፍ ለሚደረጉ ጉዞዎች መመሪያዎች መሥርቷል። እነዚህ መመሪያዎች ተሳታፊዎች ሁሉ ጤናቸው፣ ደህንነታቸውና ደህንነታቸው እንዲጠበቅ አግባብ ያለው እርምጃ መወሰዱን ለማረጋገጥ፣ እንዲሁም ከፍተኛ የትምህርት መቋረጥ አለመኖሩንና ትምህርታዊ ዋጋቸውን ለመለካት እንዲቻል ትምህርታዊ ጉዞዎችና በትምህርት ቤት ድጋፍ የሚደረጉ ጉዞዎችን ማጣሪያ፣ መገምገሚያና ፈቃድ መስጫ ሂደቶችን የያዙ ናቸው። በተጨማሪም እነዚህ መመሪያዎች ተማሪዎች ትምህርታዊ ጉዞዎችና በትምህርት ቤት ድጋፍ የሚደረጉ ጉዞዎች ላይ ከመሳተፍ ከዚህ በፊት ተማሪው ቅጣት ያገኘበትን ባሕርይ በድጋሚ ትምህርታዊ ጉዞ ላይ አትሳተፍም ብሎ በቅጣት መልክ እንዳይከለከል አቅራቦት ይዘዋል። አንድ ተማሪ ከትምህርታዊ ጉዞና በትምህርት ቤት ድጋፍ ከሚደረግ ጉዞ እንዲቀር ሊደረግ የሚችለው የትምህርት ቤት ደንብ ወይም *በመብቶችና ኃላፊነቶች መመሪያ* ውስጥ ያለ ደንብ ጥሶ በቅጣት ምክንያት ከትምህርት ቤት እንዲወጣ የተደረገበት ቀኖች ከጉዞው ጋር አንድ ዓይነት ከኑ ወይም በተቆጣጣሪው/የከፍተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ዋና ኃላፊው ውሳኔ መሠረት ተማሪው ጉዞው ላይ ቢገኝ ባሕርዩ ጉዞው ላይ ተሳታፊ ለኑ ተማሪዎች እና/ወይም ሠራተኞች ደህንነትና ጤንነት አስጊ ይናል ካለ ብቻ ነው። መመሪያዎቹ በተጨማሪም ትምህርታዊ ጉዞዎችና በትምህርት ቤት ድጋፍ የሚደረጉ ጉዞዎች አዳር ከኑና ከስቴት ወይም ከአገር ውጪ ከኑ አስቀድመው በዋና ተቆጣጣሪው እና/ወይም ፈቃድ ማግኘት አለባቸው። እንዲሁም መመሪያዎቹ የሚከተሉትን ለማረጋገጥ የተመሠረቱ ሂደቶች አሏቸው፦ (1) ተማሪዎች ሁሉ ከወላጅ/አሳዳጊ/ተንከባካቢ ለጉዞዎች ፈቃድ ያስፈልጋቸዋል፣ (2) ጉዞዎች ሁሉ ተገቢ ክትትል ይደረግላቸዋል፣ (3) ሁሉም የደህንነት ጥበቃ ጥንቃቄ ተወስዷል፣ (4) ተማሪዎች ሁሉ ትምህርታዊ ጉዞዎችና በትምህርት ቤት ድጋፍ የሚደረጉ ጉዞዎች ላይ እኩል መሳተፍ እንዲችሉ ልዩ ዓይነት ማመቻቸት ያስፈልግ እንደነ ለማወቅ ፋይላቸው ታይቷል፣ (5) ጉዞዎች ሁሉ ትምህርታዊ ጥቅም አላቸው፣ (6) ተማሪዎች ትምህርታዊ ጉዞዎች እና/ወይም በትምህርት ቤት ድጋፍ የሚደረጉ ጉዞዎች ላይ ከመሳተፍ ተከልክለው እንደነና ምክንያቱ ምን እንደነበር አውራጃው ክትትል ያደርጋል፣ (7) ተማሪዎች ትምህርታዊ ጉዞዎች እና/ወይም በትምህርት ቤት ድጋፍ የሚደረጉ ጉዞዎች ላይ ከመሳተፍ ከተከለከሉ ወላጆች/አሳዳጊዎች ይግባኝ የሚሉባቸው ሂደቶች አሉ።

ትምህርታዊ ጉዞዎች ፈቃድ የሚያገኙት እንደ ሁኔታው ነው። ሰው ሰራሽም ነ የተፈጥሮ ሁኔታዎች ተቀያይረው ለተማሪዎች ወይም ለ CPS ሠራተኞች ደህንነት ሲባል ጉዞውን መሰረዝ ግዴታ ቢን፣ ለትምህርታዊ ጉዞ የተሰጠው ፈቃድ ሊሰረዝ ይችላል።

ይህ ጉዞ ሲታቀድ ለወጡ ወጪዎች ወይም ጉዞው በመሰረዙ ምክንያት መመለስ ለማይቻሉ ክፍያዎች፣ ወይም ጉዞው በታቀደበት ወቅት ተማሪው ለጊዜው ከትምህርት ቤት እንዲወጣ በመደረጉ ወይም በመባረሩ ምክንያት ወይም ጉዞው ላይ እንዳይሳተፍ በመደረጉ ለሚጠፋ ገንዘብ CPSና የኬምብሪጅ ትምህርት ቤት ኮሚቲ ኃላፊ አይኑም።

ጉዞው እንደሚካሄድ መጀመሪያ በሚነገርበት ጊዜ ተማሪዎች ለመሳተፍ ማሟላት ያሉባቸውን ደንቦችና የምግባር ሕጎች

ለወላጆች/አሳዳጊዎች/ተንከባካቢዎች እና ለተማሪዎች መሰጠት አለበት። ጉዞው እንደሚካሄድ መጀመሪያ በሚነገርበት ጊዜ እና ጉዞው ከታቀደበት ቀን ቢያንስ ከስድስት ሳምንት በፊት ተገቢዎቹ የትምህርት ቤት ሠራተኞች ተማሪዎችን ለማስተናገድ ልዩ ማመቻቸት ወይም ማስተካከል ያስፈልግ እንደነ ለማወቅ የተማሪዎችን መዝገቦች ሁሉ ማየት አለባቸው። አስፈላጊ ከነ ጉዞው እንደሚካሄድ መጀመሪያ በሚነገርበት ጊዜ እና ጉዞው ከታቀደበት ቀን ቢያንስ ከስድስት ሳምንት በፊት የ Team ስብሰባ ተደርጎ ተማሪው የታቀደው ትምህርታዊ ጉዞ ላይ ለመሳተፍ ስለሚያስፈልጉት ልዩ ማመቻቸቶች ወይም መስተካከሎች መወያየት ያስፈልጋል።

በትምህርት ቀን ከሚካሄድ ትምህርታዊ ጉዞ (ማለትም አዳር ያልነ ጉዞ) ላይ ክፍያ የማድረግ አቅም ስለሌለው ተብሎ ማንም ተማሪ ጉዞው ላይ ከመሳተፍ ሊከለከል አይችልም። በትምህርት ቤት ድጋፍ ይደረግ ብለው ተማሪዎች ሐሳብ ላቀረቡበት ትምህርታዊ ጉዞ እያንዳንዱ ከበብ፣ Team ወይም ቡድን ለጉዞው የሚያስፈልገውን ገንዘብ ሁሉ የማሰባሰብ ኃላፊነት አለበት። በትምህርት ቤት ድጋፍ የሚደረግ ትምህርታዊ ጉዞ መጀመሪያ ፈቃድ እስከሚያገኝ ደረስ ምንም ዓይነት ገንዘብ ማሰባሰብ ወይም ሌላ ዓይነት ዝግጅት ማድረግ አይቻልም። ለአዳር፣ ከስቴት ውጪ ወይም ከአገር ውጪ ለሚደረጉ ጉዞዎች CPS ወይም የኬምብሪጅ ትምህርት ቤት ኮሚቴ ምንም ዓይነት የገንዘብ እርዳታ አያደርግም።

አንድ ተማሪ አግባብ የሌለው ባሕርይ በማሳየቱ ምክንያት አንድ አጃቢ ከታቀደው የመመለሻ ጊዜ አስቀድሞ ወደ ቤት ቢመልሰው CPS እና የኬምብሪጅ ትምህርት ቤት ኮሚቴ ለሚኖረው ወጪ ኃላፊነት አይኖራቸውም። ቴል፣ የኪራይ ቦታዎች ወይም የግል ንብረት ላይ ጉዳት ቢያደርሱ ተማሪዎችና ወላጆች/አሳዳጊዎች/ተንከባካቢዎች ኃላፊነቱን ይወስዳሉ። ወላጆች/አሳዳጊዎች/ተንከባካቢዎች ልጃቸው ለሚያደርሰው ጉዳት ካሳ ለመክፈል መስማማት አለባቸው እና/ወይም ለካሳው አስፈላጊውን ገንዘብ ለማሰባሰ የትምህርት ቤት ሹሞችን ለመርዳት መስማማት አለባቸው።

ለሁሉም መጓጓዣ ለሚያስፈልጋቸው ትምህርታዊ ጉዞዎች፣ መጓጓዣ መቅረብ ያለበት በአንድ ዓይነት አገልግሎት አቅራቢ ሲን፣ እሱም በማሳቹሴትስ ኮመንዌልዝ ውስጥ የንግድ ፈቃድ ያለውና ተሳፋሪ ለማመላለስ ከ Federal Motor Carrier Safety Administration (ፌዴራል የሞተር አገልግሎት ሰጪ ደህንነት አስተዳደር) ፈቃድ ያለው ወይም ፈቃድ ያለው የ CPS ተሸከርካሪ ወይም እንደ MBTA፣ አውቶቡስ፣ ባቡር ወይም ሌላ ዓይነት የሕዝብ መጓጓዣ ውስጥ መን አለበት። ለትምህርታዊ ጉዞ የሚውሉ የኪራይ ተሽከርካሪዎች በሙሉ በአንድ ዓይነት አገልግሎት አቅራቢ መቅረብ ያለበት ሲን፣ እሱም በማሳቹሴትስ ኮመንዌልዝ ውስጥ የንግድ ፈቃድ ያለውና ተሳፋሪ ለማመላለስ ከ Federal Motor Carrier Safety Administration (ፌዴራል የሞተር አገልግሎት ሰጪ ደህንነት አስተዳደር) ፈቃድ ያለው መን አለበት። ለትምህርታዊ ጉዞዎች መጓጓዣ የሚያቀርቡ ንግዶች አሽከርካሪያቸው ተሽከርካሪውን ለመንዳት በማሳቹሴትስ ኮመንዌልዝ ውስጥ ፈቃድ እንዳለው ማሳየት አለባቸው። የመጓጓዣ ነጋዴዎች ሁሉ ቢያንስ በየክስተቱ የ $500,000 (አምስት መቶ ሺህ ዶላር) የአካላዊ ጉዳት የኃላፊነት ዋስትና ሊኖራቸው ይገባል። "በምናልባትነት ላይ የተመሠረተ" ወይም "አጥጋቢ ያልነ " የሚል ደረጃ በFederal Motor Carrier Safety Administration (ፌዴራል የሞተር አገልግሎት ሰጪ ደህንነት አስተዳደር) የተሰጠው የመጓጓዣ አገልግሎት ሰጪ ለትምህርታዊ ጉዞዎች ማመላለሻ አይውልም። ይህ የትምህርታዊ ጉዞ ፖሊሲ ተማሪዎች በእግር እንዳይሄዱ አይከለክልም።

የተረጋገጠ ድንገተኛ ሁኔታ ካልተከሰተ በስተቀር የግል ተሽከርካሪ ወይም የኪራይ ኩምቢ መኪናዎች ተማሪዎችን ከ ወይም ወደ ትምህርታዊ ጉዞዎች፣ የስፖርት ዝግጅቶች ወይም በትምህርት ቤት ድጋፍ የሚካሄዱ ጉዞዎች ላይ ማመላለስ በጥብቅ የተከለከለ ነው። የተረጋገጠ ድንገተኛ ሁኔታ መኖሩን የሚወስነው ተቆጣጣሪው/የከፍተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ዋና ኃላፊው እና/ወይም እሱ ከሌለ የጉዞው መሪ ይናል። የግል ተሽከርካሪያቸውን የሚጠቀሙ ሠራተኞች ወይም ወላጆች/አሳዳጊዎች/ተንከባካቢዎች ተማሪ በተሽከርካሪያቸው ውስጥ ኖ ጉዳት ቢደርስበት ኃላፊነቱ ይወስዳሉ።

ደህንነታቸው የተጠበቀ የአዳር ማረፊያዎች አስቀድሞ መዘጋጀት አለባቸው፣ እንዲሁም ከተቻለ ከእኩለ ሌሊት እስከ ጠዋቱ 6 ሰዓት ባለው ጊዜ መካከል ጉዞ መኖር የለበትም፣ የጉዞ ዕቅዶች በፌዴራል የአገልግሎት ሰዓት መስፈርቶች መሠረት ለአሽከርካሪዎች የእረፍት ጊዜ መተውና በአየር መለዋወጥ፣ በመንገድ ጭንቅንቅ ወይም ባልታሰቡ ነገሮች ምክንያት መዘግየት ሊኖር እንደሚችል ታስቦ መታቀድ አለባቸው።

የትምህርታዊ ጉዞዎች ልዩ መመሪያዎችን ለማየት የድህረ ገጻችን ፖሊሲ ገጽን ይጎብኙ፡- www.cpsd.us

56. ክትባቶች

የስቴቱ ሕግ ተማሪዎች ትምህርት ቤት ከመመዝገባቸው በፊት የዲፍቴሪያ፣ ፐርተሲስ (ዉፒንግ ኮፍ)፣ ቴታነስ፣ ሚዝልስ፣ ሩቤላ (ጀርመን ሚዝልስ)፣ መምፕስ፣ ፖሊዮሚዬላይተስና ሄፐታተስ ቢ ክትባትና ሌሎችም የጤና ጥበቃ ሚኒስቴር በየወቅቱ የሚያሳውቃቸው ተላላፊ በሽታዎች ክትባቶች እንዲወስዱ ያስገድዳል። ወላጆች/አሳዳጊዎች/ተንከባካቢዎች የክትባት መዝገብን ወቅታዊ አድርገው የማቆየት ኃላፊነት አለበቸው።

57. የቤተሰብ ተሳትፎ

ቤተሰቦች የልጆቻቸው የመጀመሪያ አስተማሪዎች እንደኑ CPS ይገነዘባል። እያንዳንዳችን ለቤተሰባችብንና ለባሕላዊ ልዩነታችን አክብሮት እንደምንፈልገው ሁሉ፣ እያንዳንዱ ተማሪ፣ የቤተሰብ አባልና አስተማሪ በትምህርት ቤት ማህበረሰብ ውስጥ በሙሉ ሰብዓዊ ልዩነታችንን እንዲያከብር CPS ያበረታታል። ቤተሰቦች የሚከተሉትን እንዲያደርጉ ይበረታታሉ፡- (ሀ) ልጃቸው ስለሚማረው ነገር አስተዋይ መን፣ (ለ) ስለ ልጃቸው ትምህርት ጥያቄ መጠየቅ፣ (ሐ) የልጃቸውን ትምህርት ድጋፍ መስጠት። በ CPS ውስጥ የቤተሰብ ተሳትፎ ዓላማ ልጆች ለዕድሜ ልክ ስኬታማ ትምህርት ቀሳሚ እንዲኑ በቤትና በትምህርት ቤት መሃል አጋርነት ማጎልበት ነው። የCPS የቤተሰብ ተሳትፎ ፖሊሲ ቅጂ ለማግኘት ተቆጣጣሪውን/የከፍተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ዋና ኃላፊውን ይገናኙ።

58. የማሳለፍና የማቆየት ፖሊሲ

እያንዳንዱ ልጅ ማህበራዊ፣ ስሜታዊና የአእምሮ እድገት የሚያሳየው በተለያየ ፍጥነት እንደነና እያንዳንዱ ልጅ በትምህርት ቤት ውስጥ የግል እድገቱን በሚያመቻች ሁኔታ እድገት መቀጠል እንዳለበት የኬምብሪጅ ትምህርት ቤት ኮሚቴ ይገነዘባል። ተቆጣጣሪው/የከፍተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ዋና ኃላፊው ከትምህርት ቤት ሠራተኞችና ከወላጅ/አሳዳጊ/ተንከባካቢ አስተያየት

ከተቀበለ በኋላ ለአንድ ስኬታማ ለመን   ትግል ላይ ያለ ተማሪ የሚበጀው ወደሚቀጥለው የክፍል ደረጃ ማለፍ መኑን   ከወሰነ ተማሪው ወደሚቀጥለው ክፍል ሊያልፍ ይችላል።

ተማሪዎች ከአንድ ክፍል ደረጃ ወደሚቀጥለው እያልፉ እንዲሄዱ ይጠበቅባቸዋል። አንድ ተማሪ በክፍሉ የሚጠበቅበትን ደረጃዎች ማሟላት ከከበደው፥ የትምህርት ቤት ሠራተኞች፥ ተማሪዎችና ወላጆች/አሳዳጊዎች/ተንከባካቢዎች ተማሪውን ስኬታማ ለማድረግ የሚረዱ ለግሉ የሚኑ   የድጋፍ አገልግሎቶች ያዘጋጁለታል። ወደኋላ ማቆየት እንደመጨረሻ አማራጭ መታየት ያለበት ሁኔታ ሲን፥   በጣም በጥሞና ካገናዘቡትና የወደኋላ ማቆያ መፍትሄ ዕቅድ ከወጣ በኋላ የሚደረግ ነው። በዕድሜያቸው ምክንያት ለሁለተኛ ዓመት እዛው የክፍል ደረጃ መቆየት ከሚችሉ የአጸደ ሕጻናት ተማሪዎች በስተቀር፥ አንድ ተማሪ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ከመግባቱ በፊት ከአንድ ጊዜ በላይ ወደኋላ ሊያቆዩት አይቻልም። IEP ያላቸው ተማሪዎችን በሚመለከት የሚደረጉ ውሳኔዎች ከ IEP Team ግኙቶች ጋር ወጥ መን   አለባቸው። አንድ ተማሪን ወደኋላ ለማቆየት የሚደረግ ውሳኔ በሕንጻው ተቆጣጣሪ/የከፍተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ዋና ኃላፊ፥ ከተገቢዎቹ ሠራተኞችና ወላጆች/አሳዳጊዎች ጋር ከተማከረ በኋላ የሚን   መን   አለበት። አንደኛ ደረጃና ከፍተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ውስጥ ወላጅ/አሳዳጊ/ተንከባካቢ በውሳኔው ካልተስማማ፥ ተቆጣጣሪው/የከፍተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ዋና ኃላፊው የውሳኔ ደብዳቤ ጽፎ የተማሪው አጠቃላይ ፋይል ውስጥ ይከትና በመጨረሻ ግን ወላጅ/አሳዳጊ/ተንከባካቢ የመጨረሻ ውሳኔውን እንዲያደርግ ይፈቅዳል። ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ላይ የ IEP Team የተለየ ግኙት ከሌለው በስተቀር፥ ተማሪው የሚገባበትን ክፍል የሚወስነው የተገቢዎቹ ትምህርት ሰዓት ክምችት ነውAt

አንድ የክፍል ደረጃ ስኬታማ በነ   ሁኔታ የጨረሰ ተማሪ የትርፍ ጊዜ የስፖርት መርሃ ግብሮች ውስጥ መቆየት ወይም ችሎታውን ማሻሻል እንዲችል እንዲችል ተብሎ ወድኋላ ማቆየት አይቻልም።

59. ሐኪም ያዘዘው መድኃኒት አሰጣጥና ለሕይወት አስጊ የኑ   አለርጂዎች ጥንቃቄ በትምህርት ቤት ውስጥ

CPS ለሚሄዱ ተማሪዎች በትክክልና ጥንቃቄ በተመላ መንገድ ሐኪም ያዘዘውን መድኃኒት ለመስጠትና ለሕይወት አስጊ ከኑ አለርጂዎች ጋር የተያያዙ ችግሮችን በትምህርት ቤት ውስጥ ለመቅረፍ CPS የሂደቶች ፖሊሲ በሥራ ላይ አውሏል። ይህንን ፖሊሲ የሚደግፉት ሂደቶች በሚከተለው ድህረገጽ ይገኛሉ፦ bit.ly/CPSPolicies። ልጅዎ በትምህርት ቀን ውስጥ ሐኪም ያዘዘው መድኃኒት መውሰድ የሚያስፈልገው ከነ   ወይም ለሕይወት አስጊ የነ   የምግብ አለርጂ አያያዝ ዕቅድ የሚያስፈልገው ከነ   እባክዎን የትምህርት ቤቱን ተቆጣጣሪ/የከፍተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ዋና ኃላፊ ይገናኙ።

60. የጤንነት ፖሊሲ

የኬምብሪጅ ትምህርት ቤት ኮሚቴ በተማሪ ጤንነትና ስኬታማነት መካከል ያለውን ግንኙነት እንዲሁም የአጠቃላይ የአውራጃ ጤንነት ፖሊሲ አስፈላጊነትን ይገነዘባል።

የጤንነት ምክር አገልግሎት

የትምህርት ቤት ኮሚቴው የትምህርት ቤቶች ዋና ተቆጣጣሪንና የዋና ተቆጣጣሪ ተወካዮችን ከዚህ ፖሊሲ ሥራ ላይ መዋልና ግምገማ ጋር በተያያዘ እንደ ግልጋሎት እንዲጠቅም የጤንነት ምክር አገልግሎት እንዲያቋቁሙ ጠቁሟል።

የአመጋገብ መመሪያዎች

የትምህርት ቤት አውራጃው ዓላማ ሁሉም ተማሪዎች በትምህርት ቀን ውስጥ ትምህርት ቤቱ የሚያቀርበው ምሳ ላይ፥ መክሰስና መጠጥ ላይ ጤናማ አመጋገብ እንዲመርጡና በሌላ ጊዜ ደግሞ የጤና ትምህርት ሥርዓት ውስጥ በተዋቀረው በምግብና አመጋገብ ትምህርት፥ የትምህርት ቤት የአትክልት ግቢና ከትምህርት ሰዓት ውጪ በሚደረጉት ዝግጅቶች አማካኝነት አስፈላጊውን ዕድሎች፥ ድጋፍና ማበረታታት ማድረግ ነው።

የትምህርት ቤት አውራጃው የምግብ አገልግሎት መርሃ ግብር ለተማሪዎች የሚከተሉትን ዓይነት የተለያዩ በአቅም ልክ የኑ ገንቢና የሚጋብዙ ምግቦች ያቀርባል፦

* በUSDA ትምህርት ቤት ምግብ ደንቦች መሠረት የተማሪዎችን ጤናና የአመጋገብ ሥርዓት የሚያሟሉ
* የማሳቹሴትስ አመጋገብ ሥርዓት ደንቦችን እንደሚመለከተው የሚያሟሉ
* የተማሪዎችን ኃይማኖታዊ፥ ብሔራዊና ባህላዊ ሕብራዊነት ከግምት ያስገባ የምግብ አዘገጃጀት
* ተማሪዎች ሲበሉ ንጹህ፥ ደህንነቱ ይተጠበቀና አስደሳች ቦታ ማቅርብና በቂ ጊዜ መስጠት፥ ከተቀመጡ በኋላ ቢያንስ ለምሳ 20 ደቂቃ መስጠትና ለቁርስ 10 ደቂቃ መስጠት።
* አንድ ተማሪ ትምህርት ቤት ውስጥ ባለበት ጊዜ አለመራቡን ማረጋገጥ
* ትምህርት ቤቶች ምግብ፥ መጠጥ፥ ምግብ መሸጫ ማሺኖችን ጨምሮ፥ ካፊቴሪያ ውስጥ፥ በትምህርት ቤት ድጋፍ ወይም ከትምህርት ቤት ጋር የተያያዙ ዝግጅቶች ላይ ምግብ ሲያቀርቡ የማሳቹሴትስ የሕዝብ ጤና መምሪያ ያወጣውን የአመጋገብ ሥርዓት ይከተላሉ።
* በተጨማሪም ትምህርት ቤቶች ኪዮስክ ውስጥ፥ ገንዘብ ማሰባሰቢያ ዝግጅቶች ላይና በትምህርት ቤት ድጋፍ ወይም ከትምህርት ቤት ጋር የተያያዙ ዝግጅቶች ላይ ምግብ ሲያቀርቡ ይህንኑ የማሳቹሴትስ መስፈርቶች ተከትለው ነው።

የስፖርት ትምህርትና አካላዊ እንቅስቃሴዎች

የትምህርት ቤት አውራጃው ዓላማ ሁሉም ተማሪዎች በትምህርት ቀን ውስጥ በመደበኛ ሁኔታ በስፖርት ክፍሎች፥ ከትምህርት በፊትና በኋላ በሚደረጉ እንቅስቃሴዎች፥ በመጓጓዣና አካላዊ እንቅስቃሴን የትምህርት ሥርዓት ውስጥ በማዋቀር አካላዊ እንቅስቃሴ የማድረግ ዕድል፥ ድጋፍና መበረታታት እንዲኖራቸው ነው። በተጨማሪም ከአጸደ ሕጻናት እስከ 8ኛ ክፍል ላሉ ተማሪዎች እንቅስቃሴን ያካተቱ ዕለታዊ የእረፍት ጊዜዎች ይኖራሉ።

የጤና፥ የስፖርትና የአትሌቲክስ መምሪያዎች ለተማሪዎች በሙሉ፥ የአካልና የአእምሮ ጉዳት ያላቸውን፥ ልዩ የጤና ጥንቃቄ የሚያስፈልጋቸውንና አማራጭ ትምህርት ውስጥ ያሉትን ጨምሮ፥ የሚከተሉትን የያዙ የተለያዩ የአካላዊ እንቅስቃሴ ዕድሎች ያቀርባሉ፦

- የማሳቹሴትስ አጠቃላይ የጤና ሥርዓተ ትምህርትና የብሔራዊ ስፖርትና የስፖርት ትምህርት መስፈርት የሚያሟሉ
- ተማሪዎች ዕድሜ ልክ የሚጠቅሙ እንቅስቃሴዎች መማራቸውን ማረጋገጥ

- የተለያዩ መርሃ ግብሮች በማቅረብ ተማሪዎች አካላዊ እንቅስቃሴ ላይ የመሳተፍ ዕድል እንዲኖራቸው ማድረግ ለምሳሌ የትምህርት ቤት ውስጥና ከሌሎች ትምህርት ቤቶች ጋር የውድድር አትሌቲክስና ለሁሉም ተማሪዎች በየስልት ደረጃቸው መካፈል የሚችሉባቸው እንቅስቅሴዎች ማቅረብ፥ ለምሳሌ የትምህርት ቤት ውስጥ ስፖርቶችና የስፖርት ክለቦች

- የተማሪውን፥ የሌሎች ተማሪዎችን እና የሠራተኞችን ጤናና ደህንነት ለመጠበቅ ካልነ   እና/ወይም ተማሪዎች በእረፍት ሰዓት ወይም በስፖርት ትምህርት ሰዓት በኬምብሪጅ መንግሥት ትምህርት ቤት *የመብቶችና ኃላፊነቶች መመሪያ* ውስጥ የተጠቀሱትን የምግባር ደንቦች እና/ወይም የትምህርት ቤት ደንቦችን ወይም ሌሎች የኬምብሪጅ መንግሥት ትምህርት ቤቶች ደንቦች (ለምሳሌ ጸረ-ማስፈራራት ፖሊሲ፥ ጸረ-ማዋረድ ፖሊሲ፥ ጸረ-አድሎ ፖሊሲ ወዘተ) ካልጣሱ በስተቀር፥ ወይም ወላጅ/አሳዳጊ/ተንከባካቢ ተማሪው እንዳይሳተፍ ፈቃድ ካልሰጠ በስተቀር ተማሪዎች እረፍት ጊዜ ከመሄድ ወይም የስፖርት ክፍል ላይ ከመሳተፍ አይከለከሉም።

- የስፖርት እንቅስቃሴ ወይም የእረፍት ጊዜ ለቅጣት ተብሎ አይከለከሉም።

- ከአጸደ ሕጻናት እስከ 8ኛ ክፍል ያሉ ተማሪዎች ሁሉ ቢያንስ 20 ደቂቃ የእረፍት ጊዜ ይኖራቸዋል፥ እሱም ሥልጠና ባገኘ ሠራተኛ ቁጥጥር የሚደረግበት፥ ቢቻል ውጪ የሚገኝ ትምህርት ቤቶች ከመካከለዊ እስከ ከፍተኛ አካላዊ እንቅስቃሴ እንዲኖር በአፍ የሚያበረታቱበት ጊዜና ቦታውንና አስፈላጊውን መሣሪያ የሚያቀርቡበት ወቅት ይናል።

- ተማሪዎች ያልተለመደ ሁኔታ አጋጥሞ ካልነ   በስተቀር ከአስተማሪ ጋር ለመሰብሰብ ተብሎ፥ ፕሮጀክት ለመጨረስ ወይም ሥራ ለማካካስ ተብሎ የእረፍት ጊዜ አይከለከሉም።

- ወደ ትምህርት ቤት ሲሄዱ ብስክሌት መንዳትና መራመድ ደህንነታቸው የተጠበቀና የሚስቡ የመጓጓዣ መንገዶች መናቸውን   ለማሳየት በመሥራት ተማሪዎችና ሠራተኞች ከትምህርት ቤት ወደ ቤትና ከቤት ትምህርት ቤት የሚያንቀሳቅስ መጓጓዣ መንገድ እንዲጠቀሙና ከልጅነት ጀምሮ ጤናማና እንቅስቃሴ የተሞላ ሕይወት እንዲመሩ ይበረታታሉ።

የጤናና የአመጋገብ ትምህርት እንቅስቃሴዎች

የትምህርት ቤት አውራጃው የጤናና የአመጋገብ ትምህርት እንቅስቃሴዎች የሚከተሉትን ያካትታሉ፦

- የጤና ትምህርት፥ የአመጋገብ ትምህርትና ማህበራዊና ስሜታዊ ትምህርት በመስጠት ተማሪዎች ጤናማ ባሕርዮችን እንዲከተሉ ይበረታታሉ፥ ድጋፍ ይደረግላቸዋል እንዲሁም ትምህርት ይሰጣቸዋል

- ተማሪዎች ጤናማ ባሕርዮችን ለመያዝና ለማቆየት አስፈላጊዎቹን ስልቶች የሚያስተምር የጤና ትምህርት ያገኛሉ።

- ተማሪዎች ከሁሉም የትምህርት ቤት መርሃ ግብር አቅጣጫ ተመሳሳይና ወጥ የኑ   የጤና መልዕክቶች ያገኛሉ።

- የጤና ትምህርት ሥርዓቶችና መመሪያዎች የአመጋገብና የስፖርት ትምህርትን ከግምት ያስገባሉ።

- አመጋገብ የጤና ትምህርት ሥርዓት ውስጥ የተዋቀረ ነው። የጤናና የአመጋገብ ትምህርት የሚሰጡ ሠራተኞች ተገቢው ሥልጠና ይኖራቸዋል።

- የጤናና የአመጋገብ ትምህርት ሥርዓት ከማሳቹሴትስ አጠቃላይ የጤና ትምህርት ሥርዓት፥ ከብሔራዊ የጤና ትምህርት መስፈርቶችና ከብሔራዊ ጾታዊ ትምህርት መስፈርቶች ጋር የሰመረ ሲን   በጤና ትምህርት፥ የትምህርት ቤት ምግቦችና ተያያዥ የማህበረሰብ አገልግሎቶች መካከል ግንኙነት ያቋቁማል። ከአጸደ ሕጻናት እስከ 5ኛ ክፍል ያሉ ሠራተኞች የአውራጃ ጤና ትምህርት ሥልጠና ያገኛሉ።

- ጥሩ አመጋገብን ማስፋፋት በትምህርት ቤት ካፊቴሪያ የአበላል ልምዶች በኩል የትምህርት ቤት አውራጃው የምግብ አገልግሎት ከኬምብሪጅ የሕዝብ ጤና መምሪያ ጋር በመተባበር ለተማሪዎች የሚያቀርበውን በተፈጥሮ የሚያድጉ ፍራፍሬዎችና አትክልቶች በትምህርት ቤት ግቢዎች ውስጥ የማብቀል፥ መልቀምና የመቅመስ ዕድል ለአመጋገብ ትምህርት ድጋፍ ይሰጣል።

- የሚቻል ከነ   የትምህርት ቤት ግቢዎች ከጤናና አመጋገብ ግልጋሎት ይመደባሉ፥ ሁሉም ግቢዎች የሚበላ ፍራፍሬዎችና አታክልት ይይዛሉ እንዲሁም በተፈጥሮ ማሳደጊያ መንገዶች ይጠቀማሉ።

61. ከስፖርት ጋር የተያያዙ የጭንቅላት ጉዳቶችና ግጭቶች

ሁሉም የ Massachusetts Interscholastic Athletic Association (MIAA) (የማሳቹሴትስ የትምህርት ቤቶች አትሌቲክስ ማህበር) ደንቦች የሚመለከቷቸው ትምህርት ቤቶች በስቴቱ ሕግ መሠረት ተማሪ ስፖርተኞቻቸውና ወላጆቻቸው/አሳዳጊዎቻቸው፥ አሰልጣኞች፥ የአትሌቲክስ ዳይሬክተሮች፥ የትምህርት ቤት ነርሶችና ዶክተሮች የጭንቅላት ጉዳትና ግጭት የሚያመጡትን መዘዞች በስልጠና መርሃ ግብሮቻቸውና በጽሑፍ ኅትመቶች አመካኝነት እንዲማሩ ያስገድዳል። ስፖርተኞችና ወላጆች/አሳዳጊዎች/ተንከባካቢዎች ከዚህ ቀደም ተከስቶ ስለነበር የጭንቅላት ጉዳት አሰልጣኞቻቸውን የወቅቱ መጀመሪያ ላይ እንዲያሳውቁ ሕጉ ያስገድዳል። አንድ ስፖርተኛ ተማሪ በጨዋታ ወይም በልምምድ መሃል ራሱን ቢስት በሕጉ መሠረት ተማሪው ከጨዋታው ወይም ከልምምዱ እንዲወጣ እንዲደረግና ከሕክምና ባለሙያ "ወደ ጨዋታ መመለስ ይችላል" የሚል የጽሑፍ ማረጋገጫ እንድያመጣ ያስገድዳል። በስቴት ሕግ ሥር ያሉ ደንቦች "ማንኛውም በጨዋታ ወይም በውድድር ላይ ጭንቅላቱ የተጎዳ ወይም የተጋጨ ተማሪ፥ ወይም የግጭት ምልክቶች የሚያሳይ፥ ወይም ለአጭርም ጊዜ ቢን   ራሱን ከሳተ ወዲያውኑ ከጨዋታው ወይም ከልምምዱ እንዲወጣ ተደርጎ ያንን ቀን ወደ ጨዋታው ወይም ወደ ውድድሩ ሊመለስ አይችልም" ይላሉ። 105 C.M.R. 201.010(B)።

ማንኛውም የስፖርት መርሃ ግብር ውስጥ የመሳተፍ ዕቅድ ያላቸው ወላጆች/አሳዳጊዎች/ተንከባካቢዎችና ተማሪዎች በነጻ የኢንተርኔት ትምህርትም መውሰድ አለባቸው። ሁለት በነጻ የሚሰጡና ሕጉ የሚያስገድደውን መረጃ የያዙ ትምህርቶች አሉ። የመጀመሪያው የሚገኘው በ National Federation of High School Coaches (ብሔራዊ የሁለተኛ ደረጃ አሰልጣኞች ፌዴሬሽን) በኩል በሚከተለው ድህረገጽ ላይ ነው፦ www.nfhslearn.com

ሁለተኛው የሚገኘው በ Centers for Disease Control and Prevention (በሽታ መቆጣጥሪያና መከላከያ) በኩል በሚከተለው ድህረገጽ ላይ ነው፡- www.cdc.gov/headsup

የጭንቅላት ግጭት ማለት ጭንቅላት ወይም ሰውነት በሚጋጭበት ጊዜ አንጎል በጭንቅላት ቅል ውስጥ ሲናጋ የሚያመጣው የአእምሮ ሁኔታ ለውጥ ነው። ምልክቶቹና ስሜቶቹ ሁልጊዜ ግልጽ ስላልኑ ና የጉዳቱ ኃይለኝነትን ለመገምገም ስለሚያስቸግር የሕክምና ባለሙያዎች ከሚያጋጥሟቸው ጉዳቶች ውስጥ በይበልጥ ውስብስብ ከኑት አንዱ ነው። ከጭንቅላት ጉዳቶች ጋር የተያያዙት ምልክቶች የሚከተሉት ናቸው፡- ራስ ምታት፥ ማዞር፥ ግራ መጋባት፥ አለማስታወስ እና ማቅለሽለሽ። ከጉዳቶች ውስጥ ሁሉ ራስን መሳት የሚከሰተው ከአሥር በመቶ ባነሱ ክስተቶች ላይ ሲን የግጭቱ ኃይለኝነት አመልካች አይደለም። ከጉዳት በኋላ አንድ ስፖርተኛ ለብርሃንና ለድምጽ ተጋላጭነት፥ መርሳት፥ ድካምና እንደ ጭንቀት ወይም ጨለምተኝነት ዓይነት ስሜታዊ ተለዋዋጭነት የመሳሰሉ ሌሎች ዓይነት ችግሮችም ሊኖሩት ይችላሉ።

አብዛኞቹ የጭንቅላት ግጭት የሚያጋጥማቸው ስፖርተኞች ሌላ ግጭት ከማጋጠሙ በፊት አንጎል ሙሉ ለሙሉ እንዲያገግም ጊዜ እስከተሰጡት ድረስ ሙሉ ለሙሉ ይድናሉ፥ ኖ ም አንድ ስፖርተኛ እራሱ በሚያሳውቃቸው ምልክቶች ላይ ብቻ ተደግፎ የማገገምን ሁኔታ መገምገም በቂ አይደለም፥ ምክንያቱም ብዙ ስፖርተኛ ተማሪዎች የጉዳቱን ምልክቶች፥ የጉዳቶቹን ኃይለኝነት ስለማያውቁት ወይም ከአሰልጣኞች፥ ወላጆች/አሳዳጊዎች፥ ቡድን አባሎች ወይም ከሌሎች ወደ ጨዋታው በፍጥነት እንዲመለሱ ግፊት ሊኖርባቸው ስለሚችል። ከነዚህ ሁኔታዎች ውስጥ ቢያንስ አንዱ ጉዳቱን በሚገባ እንዳይመረመር ሊያደርጉና ያለጊዜው ወደ ጨዋታዊ እንዲመለስ ያደርጋሉ። ጥናቶች እንዳሳዩት ጭንቅላታቸው የተጎዱ ወጣቶች አንጎላቸው ሙሉ ለሙሉ ሳይድን ወደ ጨዋታ ከተመለሱ ከግጭት በኋላ የሚመጡ ምልክቶች ይበልጥ ይቆያሉ ወይም አልፎ አልፎ መከረኛ Second Impact Syndrome (ሁለተኛ ተጽዕኖ ሕመም) የሚባል የነርቭ ችግር ሊያስከትል ይችላል። ስለዚህ አንድ ስፖርተኛ ትምህርት ቤት ውስጥ የጭንቅላት ግጭት ሲያጋጥመው CPS የሚከተለውን ጥንቃቄ ያበረታታል፡-

1. ማንኛውም ዓይነት ጉዳት ሲከሰት፥ የተጎዳው ስፖርተኛ ውዲያውኑ ጉዳቱን ለአሰልጣኙና ለትምህርት ቤት ነርሱ ማሳወቅ አለበት።
2. ማንኛውም ዓይነት ጉዳት ሲከሰት፥ የጭንቅላት ጉዳትን ጨምሮ፥ ወይም የጭንቅላት ጉዳት ምልክቶች ሲታዩ፥ ወይም ራስን መሳት ካለ፥ ወላጅ/አሳዳጊ/ተንከባካቢ እንዲያውቅ ይደረግና የተጎዳው ተማሪ ወደ አካባቢው ስፒታል ድንገተኛ ክፍል መሄድ ወይም ዋና ዶክተሩ ሁኔታውን አይቶ ድንገተኛ ሕክምና አለማስፈለጉን ማረጋገጥ አለበት።
3. መነጋገር ወሳኝ ነው።
ከተጎዳው ስፖርተኛ ዋና ሐኪም፥ ወላጆች/አሳዳጊዎች እንዲሁም የ CPS አሰልጣኝ፥ የትምህርት ቤት ነርስ፥ አስተማሪዎች፥ ዋና አሰልጣኝና የአትሌቲክስ ዳይሬክተር የተውጣጣ የእንክብካቤ ቡድን የጉዳቱን ምልክቶች መከታተል አለበት።
4. ስፖርተኛው የተለያዩ ምርመራዎች እንዲያደርግ ማድረግ፥ የራስን ምልክቶች ማሳወቅ፥ የሚዛንና የነርቭ እውቀት ምርመራዎችን ጨምሮ። የተቀላቀለው ግምገማ የጭንቅላት ግጭቱን ተጽዕኖዎች በይበልጥ ጥንቃቄ የተሞላበትና ትክክለኛ በነ መንገድ ለመመርመር የሚያስችልና ስፖርተኛው መቼ ወደ ጨዋታ መመለስ እንደሚችል ለመገምገም በይበልጥ ይረዳል።
5. ማረጋገጫ ፈቃድ ያለው የ CPS አሰልጣኝ ስፖርተኛው ወደ ጨዋታ መመለስ ይችላል ብሎ እስከሚፈቅድ ድረስ ስፖርተኛው ወደ ጨዋታ ወይም ወደ ልምምድ መመለስ አይችልም።

62. የኤችአይቪ/ኤድስ ፖሊሲ

CPS በኤችአይቪ/ኤድስ ላይተመስርቶ ወይም የኤችአይቪ/ኤድስ ካለው ሰው ጋር ባለው ግንኙነት ላይ ተመስርቶ አድሎ አያደርግም። መገኘትንና በ CPS ውስጥ ትምህርት ላይ መሳተፍን በተመለከተ ኤችአይቪ/ኤድስ ያለባቸው ልጆች ሌሎች CPS ትምህርት ቤቶች ከሚሄዱ ልጆች ጋር አንድ ዓይነት መብቶችና አንድ ዓይነት ልዩ ጥቅሞች አሏቸው። ኤችአይቪ/ኤድስ ያለባቸው ሠራተኞች እና/ወይም ተማሪዎች ኤችአይቪ/ኤድስ እንዳለባቸው የማሳወቅ ግዴታ የለባቸውም። ይህን ዓይነት ማሳወቅ የሚደረገው ግለሰቡ በጽሑፍ ስምምነት ሰጥቶ ወይም ግለሰቡ ዕድሜው ከአሥራ ስምንት (18) ዓመት በታች ከነ የግለሰቡ ወላጅ/አሳዳጊ/ተንከባካቢ በጽሑፍ ፈቃድ ሰጥቶ መን አለበት። ዓለማቀፍ የኢንፌክሽን ቁጥጥር መመሪያዎችን ሁልጊዜ ከተከተሉና ሠራተኞች በሙሉ በትምህርት ቤት ውስጥና በሁሉም የትምህርት ሰዓታት ላይ ዓለማቀፍ ጥንቃቄ እንዲወስዱ ከተገደዱ በትምህርት ቤት ውስጥ ኤችአይቪ የማስተላለፍ ዕድሉ በጣም ዝቅተኛ ነው። የትምህርት ቤት አውራጃው ሙሉ የኤችአይቪ/ኤድስ ፖሊሲ የትምህርት ቤት አውራጃው ድህረገጽ ላይ ተለጥፎ ይገኛል።

63. ተማሪዎችን ስለ አደንዛዥ ዕጾች፥ አልኮል መጠጥ፥ ትምባና ዕጽ ማብዛትን መከላከል ማስተማር

የኬምብሪጅ መንግሥት ትምህርት ቤቶች ለዕድሜ አግባብ ያለው፥ ከእድገት ጋር የሚመጥን የአደንዛዥ ዕጾች፥ አልኮል መጠጥ፥ ዕጽ ማብዛትን መከላከል በሚመለከት በሁሉም የክፍል ደረጃዎች ትምህርት ይሰጣል። የዚህ ትምህርታዊ መርሃ ግብር ዓላማ ተማሪዎችን ዕጽ መጠቀምና ማብዛት የሚያመጣውን መዘዝና የአልኮል መጠጥ፥ ትምባና ሌሎች ዕጾች ሕጋዊ፥ ስሜታዊ፥ ስነ ልቦናዊና ማህበራዊ መዘዞች ማስተማር ነው። ትምህርታዊ መርሃ ግብሩ ተማሪዎች መረጃ የተመላ ውሳኔ መውሰድ እንዲችሉ፥ ስሜታዊ ጭንቀት ሲኖር መቋቋሚያ ስልቶች እንዲኖሯቸው፥ እንዲሁም አልኮል መጠጥን፥ ትምባንና ሌሎች ዕጾችን በተመለከተ የኢጋር ግፊትን መቃወም እንዲችሉ መርዳት ነው። የትምህርት ቤት አውራጃው ሙሉ ፖሊሲ የትምህርት ቤት አውራጃው ድህረ ገጽ ላይ ይገኛል።

64. SBIRT (ማጣሪያ፥ ጊዜያዊ ድጋፍ እና ወደ ሕክምና መላክ)

ተማሪዎች ከመጀመሪያውም ዕጾች እንዳይጠቀሙ ወይም ገና መጠቀም ሲጀምሩ ድጋፍ መስጠት እንዲቻል፥ የኬምብሪጅ መንግሥት ትምህርት ቤቶች በቃለ ምልልስ ላይ የተመሠረተ አልኮል መጠጥን፥ ማሪዋናንና ሌሎች ዕጾችን በተመለከተ SBIRT

የተባለ ማጣሪያ ከሰባተኛ እስከ ዘጠነኛ ክፍል ላሉ ተማሪዎች ይጠቀማል። ማጣሪያዎቹ ወደ አምስት ደቂቃ የሚፈጁ ሲኑ በምስጢራዊነት ተይዘው የትምህርት ቤት ነርሷ ወይም ከሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት አማካሪ መምሪያ ውስጥ ስልጠና ያገኘ ሠራተኛ በግል የሚሰጡት መጠይቅ ነው።

ማጣሪያውን የሚያካሂደው ግለሰብ ለማንኛውም ዕጽ እንደሚጠቀም የሚያሳውቅ ተማሪ ወይም ወደፊት ዕጽ የማብዛት ስጋት ያለበትን ተማሪ አጭር ግብረ መልስ ይሰጥና ሁሉም ማጣሪያው ላይ የሚሳተፉ ተማሪዎች ትምህርታዊ ኅትመትና የግልጋሎቶች ዝርዝር ይሰጣቸዋል። አስፈላጊ ከነ ተማሪው የትምህርት ቤት ነርሷ ጋር ወይም የቡድን አባል ጋር ሄዶ ተጨማሪ ምርመራ እንዲደረግለት ይደረጋል።

የማጣሪያው ውጤቶች የተማሪው የትምህርት ቤት መዝገብ ውስጥ አይገቡም፥ እንዲሁም አጣሪው ባገኛቸው ውጤቶች ላይ ተመሥርቶ የሚሰጥ ምንም ዓይነት ቅጣት አይኖርም፥ የማጣሪያው ውጤቶች ከ SBIRT ቡድን ውጪም ለማንም ለሌላ የትምህርት ቤት ሠራተኞችም አይካፈሉም።

አጣሪው ማጣሪያውን ከመስጠቱ በፊት የተማሪዎች ወላጆች/አሳዳጊዎች/ተንከባካቢዎች በጽሑፍ ማስታወቂያ ይደርሳቸዋል፥ ልጃቸው ማጣሪያው እንዳይሰጠውም የማድረግ መብት አላቸው።

65. የትምህርት ሥርዓት ግምገማዎች

የኬምብሪጅ መንግሥት ትምህርት ቤቶች የተማሪውን የመረዳት ችሎታ ማስረጃና ትምህርታዊ ውሳኔዎችን ለማሳወቅ የሚያስችለው የተለያዩ ግምገማዎች በትምህርት ዓመት ውስጥ ይጠቀማል። አስተማሪዎች ከትምህርታዊ ግቦች ጋር የተያያዘ ዕለታዊ ግምገማ የሚጠቀሙ ሲን፥ የኬምብሪጅ መንግሥት ትምህርት ቤቶች ተማሪዎች ሁሉ በአንድ ርእስ ላይ በድምር እንዴት እየሠሩ እንደነ ለመገምገም የሚያስችል እንዲሁም ንዑስ ቡድኖች በሌሎች ተማሪዎች አንጻር እንዴት እየገፉ እንደነ ለማወቅ እንዲቻል፥ በተጨማሪም ስለ ትምህርታዊ ክፍተቶችና ሙያዊ አስፈላጊ ትምህርቶችን ማወቅ እንዲቻል MCAS 2.0 እና መደበኛ የአውራጃ መገምገሚያዎችን ይሰጣል።

ከአጸደ ሕጻናት እስከ 5ኛ ክፍል፥ ከ6ኛ እስከ 8ኛ ክፍልና ከ9ኛ እስከ 12ኛ ክፍል ስለ ግምገማ የጊዜ ሰሌዳ በይበልጥ ዝርዝር ያለው መረጃ ለማግኘት የትምህርት ቤት አውራጃው ድህረገጽ ላይ በ bit.ly/CPSci ይጎብኙ፥ እንዲሁም ከልጅዎ ትምህርት ቤት ተቆጣጣሪ/የከፍተኛ ደረጃ ዋና ኃላፊ ሊገኝ ይችላል።

66. በትምህርት ቤት ውስጥ ትምባ የመጠቀም ክልከላ

ሠራተኞች፣ ተማሪዎች ወይም ማንም ሰው ትምባ ማጨስ፣ ማኘክ ወይም ማንኛውም ዓይነት የትምባ አጠቃቀም በትምህርት ቤት አውራጃ ሕንጻዎች ውስጥ በሙሉ ክልክል ነው። “የትምባ ምርቶች” ማለት በማንኛውም መልኩ የሚቀርብ ትምባ ማለትም ሲጋራን፣ ሲጋርን፣ ሱረትን፣ የሚታኘክ ትምባን፣ ኤሌክትሪክ ሲጋራን፣ ኒኮቲን ማትነኛን፣ ጭስ የሌላቸው የትምባ ምርቶችንና ሌሎች ተመሳሳይ ምርቶችን ያጠቃልላል። ይህ ፖሊሲ የሚመለከተው ሁሉን በትምህርት ቤት ድጋፍ እና/ወይም ከትምህርት ቤት ጋር የተያያዙ ዝግጅቶችን፣ የስፖርት ጨዋታዎችን፣ እነዚህ ዝግጅቶች በትምህርት ቤት አውራጃው ንብረትና ቅጥረ ግቢ ውስጥ ቢኑም ባይኑም ነው። የትምህርት ቤት ንብረት እና/ወይም ቅጥረ ግቢ ማለት እያንዳንዱ ትምህርት ቤት ዙሪያ እስከሚገኘው የእግረኛ መንገድ ድረስ ያለው መሬት ነው። በተለይም የኬምብሪጅ ሪንጅና ላቲን ትምህርት ቤት ቅጥረ ግቢ፣ ከትምህርት ቤት ቅጥረ ግቢ ክፍል ኖ የሚቆጠረውን የኬምብሪጅ መንግሥት መጽሐፍት ቤት ቅጥረ ግቢን ያካትታል ስለዚህም የተማሪ ፖሊሲዎች ይመለከቱታል።

ይህንን ፖሊሲ ተላልፎ የተገኘ ሠራተኛ የቅጣት እርምጃ ይደርስበታል።
የነዚህን መስፈርቶች እንደ ጥሰቱ ዝርዝር ሁኔታ አንድ ተማሪ ቅጣት ሊደርስበትና ወደ ተገቢው የትምባ እርዳታ እና/ወይም ዕጽ ማብዛት የከተማ/ጤና ትምህርት መርሃ ግብር ሊላክ ይችላል።

በተጨማሪም በኬምብሪጅ ከተማ “ማጨስ የተከለከለበት ዞን” የሚሉ በማዘጋጃ ቤቶች ዙሪያ የሚገኙ ቦታዎችን ከማቋቋም ጋር በተያያዘ በኬምብሪጅ ትምህርት ቤቶች ሁሉ ከሁሉም መግቢያዎች ውጪ፥ የአየር ማስገቢያዎችና የሚከፈቱ መስኮቶች ውጪ እስከ ሃያ (20) ጫማ ርቀት ውስጥ “ማጨስ የተከለከለበት ዞን” ተብለው ይሰየማሉ።